# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### ስምንተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ግንቦት

፲፱፻፺ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፮ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት


<u>አድራሻ</u>፡-

ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ

ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org



www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው
ስልክ፡- 0911350439

## ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም  በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ፡፡ በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም፡፡

## መታሰቢያነቱ



አባታዊ ምክራቸው ዘወትር ላልተለየኝ፣ በአቃቂ መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መደበኛ ሰባኬ ወንጌል ሆኜ ሳገለግል የልጅነት ግብዣዬን ተቀብለው ባለመሰልቸት ለዓመታት በየሳምንቱ እሁድ እየተመላለሱ ላገለገሉ ዛሬ በግሪክ አገር በምትገኘው የኢ/ኦ/ተ ቤተ ክርስቲያናችን አስተዳዳሪ ለሆኑ ለንቡረ ዕድ ኃይለ ልዑል ወልደ ገሪማ ይሁንልኝ፡፡

www.zoorthodox.org

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል፡፡

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | ፍትሕ | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ፍቅር | 4 | | ሁለተኛ | |
| 3. | ሙስና | 8 | | ሦስተኛ | |
| 4. | ሰላም በክርስትና | 11 | | አራተኛ | |
| 5. | በቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ክፍፍል | 13 | | አምስተኛ | |
| 6. | ሰማዕታት | 16 | | ስድስተኛ | |
| 7. | ያሬዳዊ ዜማዎች | 18 | | ሰባተኛ | |
| 8. | የእግዚአብሔር መገለጥ በብሉይ ኪዳን | 20 | | ስምንተኛ | |
| 9. | ዕጣን በቤተ ክርስቲያን | 22 | | ዘጠነኛ | |
| 10 | ቅዱሳት ሥዕላት | 24 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | ምስጢረ ቁርባን (አንድ) | 26 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | ምስጢረ ቁርባን (ሁለት) | 29 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | መጽሐፈ ዕዝራ | 31 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | መጽሐፈ ኢያሱ | 33 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | ግዝረት | 35 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ጓደኞቻችንን እንዴት እንምረጥ? | 37 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | የጓደኝነት ተጽዕኖዎች | 39 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ቅዱስ ባስልዮስ | 41 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መምህራን | 43 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (አንድ አምላክ) (፩) | 46 | | ሃያኛ | |
| 21. | የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (የክርስቶስ አምላክነት) (፪) | 50 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ መንፈስ ቅዱስ) (፫) | 53 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ ቤተ ክርስቲያን) (፬) | 55 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ መንፈስ ቅዱስ) (፭) | 58 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ሐሜት | 61 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | የምስንኩስና ሕይወት | 63 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ንጉሥ ሳኦል | 65 | | ሃያ ሰባተኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ. ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | ነቢዩ ንጉሥ ዳዊት | 67 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ድሃ | 70 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | የሃገር ፍቅርና መንፈሳዊ ሕይወት | 73 | | ሠላሳኛ | |
| 31. | የጸሎት ቤት | 75 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | ሰውን አታምልክ | 78 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | አልአዛር | 80 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | የኤማሁስ መንገደኞች | 83 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ቅዱስ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ | 85 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ታየ | 88 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | የመንፈስ ቅዱስ ሥራ | 91 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | የጸጋ ስጦታዎች | 93 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | የዮሐንስ ራእይ (አንድ) | 95 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | የዮሐንስ ራእይ (ሁለት) | 98 | | ዐርባኛ | |
| 41. | ሰሙነ ሕማማት | 100 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | የድንግል ማርያም ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን | 103 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | ቀናተኛው ነህምያ (አንድ) | 107 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | ቀናተኛው ነህምያ (ሁለት) | 109 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ንዴት | 111 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | ምስክርነት | 113 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | መጽሐፈ ሩት | 115 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | የቤተ ክርስቲያን አባቶች | 119 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | ውበት | 122 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | የአካል ብቃት እንቅስቃሴ | 125 | | ሃምሳኛ | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል። ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል።

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሥራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ። ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ። አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ። በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው።

www.zeorthodox.org

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል።

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል፡፡ በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ፡፡

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኀትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ፡፡

*"እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል፡፡" ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪*

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል፡፡

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል፡፡ በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል፡፡ ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው፡፡

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# ፍትሕ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ፍትሕ ምንነት ይገነዘባሉ፤ በቃልና በሥራ እየተጉ በጽድቅ ሥርዓት በፍትሐዊነትም ሕይወታቸውን እንዴት መምራት እንዳለባቸው ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ፍርድ እንደ ውኃ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ" አሞፅ.፭÷፳፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** አሞፅ ፭÷፲-፲፭፣ ሚክ. ፮÷፰ እና ሮሜ. ፲፪÷፲፱-፳፩

## መግቢያ

ፍትሕ በትክክል የተተረጎመ ሕግ አድልዎና በደል በሌለበት ሁኔታ በተግባር የሚረጋገጥበት፣ መብት እውነትን መሠረት አድርጎ የሚከበርበት ሥርዓት ነው፡፡ ፍትሕ ሳይዛባ የእውነተኛውን ዳኛ የእግዚአብሔርን ሕግጋት አክብሮ ከሰፈነ የሰው ልጆች ሁሉ ዋስትና ነው፡፡ ሆኖም ዓይኖቻችንን ገልጠን ዙሪያችንን ስንቃኝ ፍትሕ በማጣት የሚያለቅሱ የፍትሕ ረኃብተኞችን፣ ፍርድ አጓድለው ድሃን የሚበድሉ ዳኞችንና በኢፍትሐዊነት ኑሯቸውን ያቀኑ ወንጀለኞችን እናያለን፡፡ በፍትሕ እጦት የሚመጡ ችግሮቻችንን ከምንጫቸው በመንቀል መፍትሔ ለመስጠት ወጣቶችን በጽድቅ ሥርዓት ማሳደግ አለብን፡፡ ወጣቶች በጽድቅ የሚፈርደውን አምላክ የሚያስደስት ማንነት እንዲኖራችሁ ይህንን ትምህርት በሚገባ ተከታትላችሁ በመረዳት በተግባር ልትተረጉሙት ይገባል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ፍትሕ ማለት "ፈትሐ" ፈረደ ከሚል የግእዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን ፍርድ (ብያኔ) ማለት ነው፡፡ የፍትሕ መሠረቱ ሕግ ነው፡፡ ያለ ሕግ ፍትሕ ሊኖር አይችልም፡፡ ሰው ቢበድል የሚከሰሰው (የሚጠየቀው)በደል ቢደርስበት የሚከሰው (የሚጠይቀው) በሕግ ነው፡፡ ሕግ በሦስት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡-

www.zeorthodox.org

፩. ሕገ እግዚአብሔር (ፍትሕ መንፈሳዊ)

፪. ሕገ መንግሥት (ፍትሕ ሥጋዊ) እና

፫. ሕገ ሕሊና (የሞራል ሕግ) ናቸው፡፡

ፍትሕ ሥጋዊ በምድራዊ አስተዳደር ሹማምንት ይዳኛል፡፡ ፍትሕ መንፈሳዊ ደግሞ በመንፈሳዊ መሪዎች ይታያል፡፡ የሁለቱም ሚዛን ኀሊና ሲሆን በዳኞች ዳኛ በእረኞች አለቃ በእግዚአብሔር ፍትሕ ሁሉም ይመረመራል፡፡

ከስሕተት ተቆጥቦ፣ ከፉን ተፀይፎ፣ በማስተዋልና በእውነት የሚኳዝ ሰው ፍትሐዊ ይባላል፡፡ የተከለከለውን የሚያደርግ፣ ባልዋለበት የሚያጭድ፣ በክፋት የሚኖር፣ በደልና ዐመፃን የሚያበዛ ሰው ደግሞ ኢ-ፍትሐዊ ይባላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው በሦስቱም ሕጎች ፊት ወንጀለኛ ነው፡፡ በምድርም በሰማይም ተጠያቂ ነው፡፡

ፍትሕ ለሰው ጥቅም የሚበጅ የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡ እግዚአብሔር በእውነት የሚፈርድ ፍትሐዊ አምላክ ነው፡፡ የሰውን ፊት አይቶ አያዳላም፡፡ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ነው፡፡ ድሃን ስለድህነቱ አይራራለትም፡፡ ሃብታምንም ስለሃብቱ አያፍረውም፡፡ ኢፍትሐዊነትን የምድሩም የሰማዩም ሕግ አይደግፍም፡፡ ኢፍትሐውያን በገዛ ኅሊናቸው ፊት እንኳ የተራቆቱ ናቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የፍትሕ መጽሐፍ ነው፡፡ ሰው ከክፉ ተለይቶ በጽድቅ ሥርዓት እንዲኳዝ፣ በጸጋው ተደግፎ የአምላኩን ሕግ እንዲፈጽም፣ በማስተዋልና በጥንቃቄ በመራመድ የምድርንም ሕግ እንዲጠብቅ ያዝዛል፡፡ የነቢያት አገልግሎት ኢፍትሐዊነትን የሚያወግዝ ነው፡፡ ነቢዩ አሞፅ የፍትሕ ጠበቃ ነበር፡፡ ሰሎሞን በጥበብ እንደፈረደ ተጽፎአል፡፡ **፩ነገ. ፫÷፲፮-፳፰፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ሀብትን እኩል** ስለማካፈል፣ ሰው የድካሙን ዋጋ እንዲከፈልና ማንም በማንም ላይ ግፍ እንዳይሠራ በማዘዝ ስለ ፍትሐዊነት አስተምሯል፡፡ ሉቃ. **፫÷፱-፲፬፡፡ ያዕቆብ በንጹሐን ላይ በሐሰት** መፍረድና የሠራተኞችን ደመወዝ ማስቀረት የሚያስከትለውን ፍርድ በመግለጽ ኢፍትሐውያንን አስጠንቅቋል፡፡ ያዕ. **፭÷፩-፮፡፡**

ሃይማኖት የፍትሕ አባት ነው፡፡ በሃይማኖት የሚኖሩ ሁሉ ፍትሕን በማክበር አርአያ መሆን አለባቸው፡፡ ወጣቶች ከአድሏዊነት፣ ከዘረኝነት፣ ከርኩሰት፣ ከዐመፀኝነትና ከኃጢአት ሁሉ በመራቅ የሕይወት መንገዳችንን ቃሉን በመጠበቅ ልናነፃ ይገባል፡፡ አለመታመን፣ በወዳጅነትና በዝምድና ሰበብ ከፍትሐዊነት መንሸራተት ፍሬው መራራ ነው፡፡ የኢፍትሐዊነት ደመወዝ በምድር ማረሚያ ቤት፤ በሰማይ የዘላለም ቅጣት ነው፡፡ ፍትሐዊ መሆን፣ ፍትሕ ስለተጓደለባቸው ድሆች መቆርቆር፣ ከወንጀለኞች ጋር በክፋት አለመተባበር ለኅሊና በመታመን መኳዝ በረከተ ሥጋ ወነፍስ ያስገኛል፡፡

## ማጠቃለያ

ፍትሕ ለሰው ጥቅም የቆመ የጽድቅ ሥርዓት ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ኢፍትሐዊነት ሕይወትን ወደ ሞት የሚያደርስ የዓመፀኞች መንገድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በጽድቅ የሚፈርድ አምላክ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የፍትሕ መጽሐፍ ነው፡፡ ሃይማኖት የፍትሕ አባት ነው፡፡ በሃይማኖት የምንኖር ሁላችን መገለጫችን ፍትሐዊነት መሆን አለበት፡፡ ራሳችንን በመግዛት ፍትሕ መንፈሳዊና ፍትሕ ሥጋዊን መጠበቅ አለብን፡፡ የነገው መንገዳችን የሚቀናው በዛሬው መልካምነታችን ነው፡፡ ነገ ብሩህ ተስፋ ሰንቆ እየጠበቀን ነውና በኢፍትሐዊነት እንዳናጨልመው በማስተዋልና በጥንቃቄ እንኳዝ፡፡ በጽድቅ ሥርዓት እንመላለስ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ፤ ተማሪዎችዎ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተዘጋጅተው በክፍል እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- ኢፍትሐዊነትን አስወግዶ ፍትሐዊነትን ለማስፈን የወጣቶች ድርሻ ምንድን ነው?

✍ ፍትሐዊነት የሚገለጽባቸው የወጣትነት ሥራዎች ምንድን ናቸው?

***ጥያቄዎች***

1. **ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው?** የቃሉን ትርጉም በማስቀደም እያብራራችሁ ግለጹ፡፡
2. **ኢ ፍትሐዊነት ማለትስ ምን ማለት ነው?**
3. የሕግ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
4. ፍትሕ ሥጋዊ የሚዳኘው እና ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረገው በማን ነው?
5. ፍትሕ መንፈሳዊ የሚታየውና የሚዳኘው በማን ነው?

www.zeorthodox.org

# ፍቅር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በሥራና በእውነት በመዋደድ በፍቅር መኖርን ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ" ፩ዮሐ. ፫÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፲፫÷፩-፲፫ እና ፩ዮሐ. ፬÷፯-፳፩

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ፍቅር ማለት "አፈቀረ" ወደደ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን መውደድ ልብን መስጠት ማለት ነው፡፡ ፍቅር ፍጹምነት፣ ርኅራኄና ቅድስና የሚገለጡበት አደባባይ ነው፡፡ ፍቅር የታላላቆችን ምስክርነት ያገኘ፤ የኃያላንን ጉልበት ያንበረከከ፤ ወልድን ከዙፋኑ የሳበ ሕያውና ኃያል ነው፡፡ ፍቅር፤ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ (ሰብእ) ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### 1. የእግዚአብሔር ፍቅር (Agape)

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ጊዜ አይሽረውም፤ ሁኔታ አይወስነውም፤ ወረት አይለውጠውም፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊና ሕያው ነው፡፡ እግዚአብሔር የዘመናችን ሁሉ ወዳጅ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ሁኔታ አይመሠረትም፡፡ እግዚአብሔር እንዲሁ ወደደን፡፡ ዮሐ. ፫÷፲፮፡፡ **እንዲሁ የሚባል ፍቅር ከፀሐይ** በታች የለም፡፡ የዓለም ፍቅር በሁኔታዎችና በተፈቃሪው ማንነት ይመሠረታል፡፡ እግዚአብሔር ግን ያለ ቅድመ ሁኔታ ወደደን፡፡ አብ አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ያደረሰው፤ ኃያል ወልድን ከዙፋኑ ስቦ ለመስቀል ሞት እንዲታዘዝ ያደረገው ለሰው ልጆች ያለው ፍጹምና ዘላለማዊ ፍቅር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቹ ሳለን ለእኛ መሞቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳያል፡፡ ሮሜ. ፭÷፰፡፡ ስለዚህ አስቀድመን በፍጹም ልባችንና በፍጹም ነፍሳችን ልንወደው ይገባል፡፡ ሉቃ. ፲÷፳፯፡፡

### 2. የሰው ፍቅር

www.zeorthodox.org

ይህ ፍቅር በሦስት ይከፈላል፡፡ እነርሱም፡-

2.1. የባልንጀራ ፍቅር (Filia)

2.2. የጾታ ፍቅር (Eros) **እና**

2.3. የቤተሰብ ፍቅር **ናቸው፡፡**

#### *2.1. የባልንጀራ ፍቅር*

ይህ ፍቅር በተፈጥሮ እኩያነት ባልንጀራ፣ በሃይማኖት ዝምድና ወንድም የሆኑንን የሰው ዘርን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ አራት

ባልንጀራህን፣ ወንጌል ጠላትህንም ውደድ ይሉናል፡፡ የሚወዱንን ብቻ ሳይሆን የሚጠሉንንም በመውደድ የክርስትናችንን ብልጫ ማሳየት አለብን፡፡ ማቴ. ፭÷፵፯፡፡

የማናየውን እግዚአብሔርን መውደዳችንን የምናስመሰክረው የምናየውን ወንድማችንን በመውደድ ነው፡፡ **፩ዮሐ. ፬÷፳፡፡ ባልንጀራችንን የማንወድ ከሆነ** እግዚአብሔርን አውቃለሁ ማለት አንችልም፡፡ **፩ዮሐ. ፬÷፰፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ በሽምግልና** ወራቱ በሰው ታግዞ ወደ አማኞች ጉባኤ ሲመጣ በትምህርቱ መክፈቻ ቃል፤ "ልጆች ሆይ በክርስቶስ እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ" በማለት ይመክራቸው ነበር፡፡ አማኞቹም "ይህን ቃል ለምን ትደጋግማለህ?" አሉት፡፡ ዮሐንስም "ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ የመልካምነት ድምዳሜ ነው፡፡" አላቸው፡፡ እውነት ነው ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው፡፡ ሮሜ ፲፫÷፲፡፡ **ፍቅር የፍጻሜ ማሠሪያ ነው፡፡** ቆላ. ፫÷፲፬፡፡ **ፍቅራችን ያለ ግብዝነት ይሁን፡፡** ሮሜ. ፲፪÷፱፡፡ **ፍቅር የልብ ነገር እንጂ በአንደበት ብቻ የሚወሰን በንግግር ብቻ የሚገለጽ** አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው "በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ" ያለው፡፡ የምድሪቱ ርኃብ ፍቅር ነው፡፡ የምድር ቁስል እንዲፈወስ ከፈለግን ትንሽ ትልቅ ሳንባባል በፍጹም ፍቅር መዋደድ አለብን፡፡ ባልንጀራን መውደድ እግዚአብሔርን የመውደዳችን ማስመስከሪያ ነው፡፡ መዋደድ የክርስትና መታወቂያ ነው፡፡ ዮሐ. ፲፫÷፴፭፡፡ **ፍቅር የኃጢአትን ብዛት** ይሸፍናል፡፡ **፩ጴጥ. ፬÷፰፡፡**

### *2.2. ጾታዊ ፍቅር*

ይህ ፍቅር ከመንፈስ አንድነት አልፎ የሥጋ ጥምረትን ይጨምራል፡፡ የሁለት ተቃራኒ ጾታዎችን መፈላለግ ፣ መቀራረብ፣ መግባባት፣ መዋደድ፣ በልብ መጣመርና በነፍስ መተሳሰር ያጠቃልላል፡፡ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም ስላይደለ እግዚአብሔር የምትመች ረዳት ፈጠረለት፡፡ አዳምም "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋዋም ከሥጋዬ ነው፡፡" ብሎ በደስታ ተቀበላት፡፡ አዳምና ሔዋን በገነት ጋብቻ ፈጸሙ፡፡ የጋብቻው ዓላማ ዘርን ለመተካት፣ ለመረዳዳትና ከሥጋዊ መሻት ለመዳን ነው፡፡ አዳም ግን ሚስቱን በሥጋ ሩካቤ ያወቃት ከገነት ከተባረሩ በኋላ ነው፡፡

ወጣቶች ወደዚህ የከበረ ሥርዓት በክብር ለመድረስ ራሳቸውን ገዝተው በንጽሕናና ቃሉን በመጠበቅ የጎልማሳነት መንገዳቸውን በንጽሕና ሊመሩ ይገባል፡፡ በተቃሪኒ ጾታ ፍቅር መሳብ ጤናማነት ነው፡፡ የመፈላለግና የመዋደድ ፍላጎት በልባችን ያስቀመጠ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ ስሕተቱ ምንድን ነው? ስንል ያለጊዜያችን መሰናከላችን፣ በጊዜያዊ ፍቅር መነደፋችንና በጋብቻ ሳንወሰን ለርኩሰት መጋለጣችን ነው፡፡ እውነተኛ በሆነ ልባዊ ፍቅር ስትወድቁ በቃል ኪዳን በመተሳሰብ ወደ ዓላማችሁ ፍጻሜ መድረስ አለባችሁ፡፡ ርካሽ ከሆነ መዋደድና ርኩሰትን ከሚያበረታታ ጊዜያዊ ፍቅር በመራቅ በንጽሕና ወደ ራእያችን ፍጻሜ መገስገስ አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

ጾታዊ ፍቅር የሁለት ተቃራኒ ጾታዎችን (ፍቅረኞችን) የልብ ጥምረት፣ የዓላማ ጽናት፣ የመንፈስ ኅብረትና በትክክለኛው ጊዜና ቦታ የሆነ የንጹሕ ስሜትን መሠረት አድርጎ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ ወደ ጋብቻ ያመራል፡፡

### *2.3. የቤተሰብ ፍቅር*

ይህ ፍቅር በደም የተከፈሉና በአንድ ቤት ያደጉ ቤተሰቦችን ይመለከታል፡፡ የአባት፣ የእናት፣ የእኅት፣ የወንድም፣ የልጆችና ሌሎች የሥጋ ዘመዶች ፍቅር በዚህ ይጠቃለላል፡፡ የተገኘንበትን ቤተሰብ በደስታ መቀበል ማክበርና ትክክለኛ የፍቅር ምላሽ

መስጠት ግዴታችን ነው፡፡

## 3. የፍቅር ባሕርያት

ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው፡፡ ፍቅር የተሰበሩት የሚጠገኑበት ከርቤ፣ የራቁት የሚቀርቡበት መዓዛ፣ የወደቁት የሚነሡበት ክንድ፣ የተበተኑት የሚሰበሰቡበት አደባባይ ነው፡፡ ፍቅር የእምነት መገለጫ ነው፡፡ ፍቅር በዘርና በቀላም በቋንቋና በወገን በትልቅነትና በትንሽነት አይወሰንም፡፡ ያለ ድንበር እንደ ወንዝ ውኃ ይፈሳል፡፡

ፍቅር ያለ መሰሰት ቸርነት ያደርጋል፡፡ የማይገባውን አያደርግም፡፡ ፍቅር በደልን አይቆጥርም፡፡ የራሱን አይፈልግም፡፡ ፍቅር ሁሉን ይታገሳል፡፡ በእውነት ደስ ይለዋል፡፡ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፡፡ አይቀናም፡፡ ተስፋ ያደርጋል፡፡ አያስታበይም፡፡ **፩ቆሮ. ፲፫÷፩-፲፫**፡፡

## ማጠቃለያ

ፍቅር የክርስቲያኖች ተግባራዊ ሕይወት መገለጫ፣ በዘመን ሁሉ የሚሠራ ሕያውና ኃይል ነው፡፡ ፍቅር የፍጻሜ ማሠሪያ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው፡፡ ፊተኛዋ ኪዳን ባልንጀራህን አዲሷ ኪዳን ጠላትህን ውደድ ይሉናል፡፡ ጠላታችንን በመውደድ የፍቅርን ራስ በሕይወታችን በመግለጥ የክርስትናችንን ብልጫ እናሳይ፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎን፣

✍ ያለ ጊዜው የሚፈፀም የወጣትነት ፍቅር ጎድቶን እንዳያልፍ ምን እናድርግ? በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

- ☞ ፍቅር ምንድ ነው?
- ☞ የፍቅር ዓይነቶች ስንት ናቸው? ምን ምን ይባላሉ?
- ☞ እውነተኛ ፍቅር እንዴት ይታወቃል?
- ☞ ስለ ፍቅር መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ማስረጃ ጥቅሶች በማቅረብ ግለጹ
- ☞ የእግዚአብሔር ፍቅር ሲባል ምንድ ነው? አብራሩ፡፡
- ☞ የፍቅር ባሕርያት ምን ምን ናቸው? ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሙስና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ማኅበረሰባዊ ችግሮችን ለይተው የክፉዎችን መንገድ በመገንዘብ፣ ራሳቸውን በመጠበቅና ሕገ እግዚአብሔርን በማክበር ሕይወታቸውን በትክክል መምራትን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእጃቸው ተንኮል አለባቸው፤ ቀኛቸውም መማለጃ ተሞልታለች" መዝ. ፳፭÷፱-፲፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፳፭÷፱-፲፩፣ ምሳ. ፳፰÷፲፯ እና ሉቃስ ፫÷፲-፲፬

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሙስና ማለት "አማሰነ" አጠፋ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ‹‹ጥፋት›› ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ለሥጋዊ ዝምድና፣ ለወዳጅነትና ለተቀበለው መማለጃ (ጉቦ) ብሎ ሕግ ሲተላለፍ፤ ድሃ ሲበድል፤ የማይገባውን ሲያደርግ ሙስና ሠራ ይባላል፡፡ ጥፋቱ ብዙዎችን ያጠፋልና ዳዊት፤ "አቤቱ ከኃጢአተኞች ጋር ነፍሴን ከደም ሰዎች ጋር ሕይወቴን አታጥፋት በእጃቸው ተንኮል አለባቸው፤ ቀኛቸው መማለጃን ተሞልታለች" አለ፡፡

ሰው አምላኩን የሚመስል ፍጡር ነው፡፡ በከበረ ሥፍራ፤ በቅዱሳን ከተማ፤ በሕያዋን ምድር፤ ይኖር ነበር፡፡ ያልተፈቀደለትን በመብላቱ አጠፋ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰው ለኃጢአት ተገዥ ሆነ፡፡ ከኃጢአት ሥራዎች መካከል አንዱ ሙስናን መማለጃ ብሎ ይጠቅሰዋል፡፡ በጥንታዊው አማርኛ ‹‹ጉቦ›› ሲባል በዘመናዊው አማርኛ ‹‹ሙስና›› በሚል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሙስናን ይቃወማል፡፡ "ማማለጃን አትቀበል! ማማለጃ የዓይናማዎችን ሰዎች ዓይን ያሳውራልና፤ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና፡፡" ዘፀ. ፳፫÷፰፡፡ "የንጹሑን ሰው ነፍስ ለመግደል ጉቦ የሚቀበል ርጉም ይሁን" ዘዳ. ፳፯÷፳፭፡፡

www.zeorthodox.org

የእግዚአብሔር ቃል፡- ሙስና የአድሏዊነትን መንፈስ እንደሚከተል፤ የዳኞችን ዓይን እንደሚያሳውር፤ ፍርዳቸውንም እንደሚያጣምም በማስረዳት፤ ጉቦ የሚቀበል የተረገመ ይሁን በሚል የጸና ቃል ያወግዛል፡፡

ሰው መማለጃ (ሙስና) የሚያቀርበው የሚፈልገውን ነገር በፍትሐዊነት እንደማያገኘው አውቆ ትክክለኛ ባልሆነው የኢፍትሐዊነት መንገድ የራሱ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ሙስና ተቀባዩም ፍትሕ የሚፈቅድላቸውን የተገባቸውን ሰዎች በድሎ ለማይገባው ሰው ስለ ጥቅሙ ይሰጠዋል፤ ይፈርድለታልም፡፡ ይህ ትልቅ ጥፋት ነው፡፡

የእኛ ያልሆነን ነገር አላአግባብ መጠቀም፣ ለሌሎች የሚገባውን በአግባቡ አለመስጠት፣ ወዳጅነትና ዝምድናን ተጠቅሞ የድሆችን መብት መጋፋት፣ በገንዘብና ሥልጣን ተከልሎ የማይገባንን የራሳችንን ማድረግና ተገቢውን ነገር በተገቢው ጊዜ

አለመፈጸም ሙሰኝነት ነው፡፡ ሰዎች መማለጃ (ጉቦ) በመስጠትና በመቀበል፡-

- ሥልጣናቸውን አለአግባብ ይጠቀማሉ፡፡
- ፍርድ ያጓድላሉ፤ ሕግ ይተላለፋሉ፡፡
- አለአግባብ ይበለጽጋሉ፡፡
- ድሃ ይበድላሉ፤ ይገድላሉም፡፡
- ግፍና ዐመፃን ያበዛሉ፡፡
- ሰውንም እግዚአብሔርንም ያሳዝናሉ፡፡

ሙስና በብዙ መንገድ በሁሉም ስፍራ ይፈጸማል፡፡ ለምሳሌ፡- በትምህርት ቤት ተማሪዎች ወዳጅነትን በመጠቀም ትምህርቱን አጥንቶ በሚገባ ከተዘጋጀው ተማሪ በመኮረጅ ያልደከሙበትን ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ይህ ትክክል ያልሆነ እግዚአብሔርም የማይወደው ተግባር ነው፡፡ ተገቢውን ነገር ለተገቢው ሰው ለማድረግ፤ አድሏዊነትን ለማስወገድ ሙስናን እንዴት መዋጋት ይቻላል?

- የማይገባንን ነገር አለመፈለግና ለተገቢው ሰው እንዲሆን በማድረግ፡፡
- ከራስ ወዳድነት በመንፃት ለሌሎች በጎ በማድረግ በመፍቀድ፡፡ ፊልጵ. ፪፥፩-፯፡፡
- የምንፈልገውን ነገር በፍትሐዊነት ለማግኘት በመጣር፡፡
- ሰዎች ስለ ሙስና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማስተማርና
- ግፈኞችን ለሕግ በማቅረብ ከዚህ የጥፋት ጎዳና ሰዎችን መጠበቅ ማስቆም እንችላለን፡፡

ሲሞን ገንዘቡን መማለጃ አድርጎ በመቅረብ የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊገዛ ሲፈልግ ቅዱስ ጴጥሮስ ገሠጸው፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስን አርአያነት መከተል ይጠበቅብናል፡፡ ሐዋ. ፰፥፲፰፡፡

## ማጠቃለያ

ሙስና በዘላለማዊ አምላክ በእግዚአብሔርም ሆነ በምድራዊው መንግሥት አደራና ሓላፊነት የተሰጣቸውን የዳኞችን ዓይን ያሳውራል፤ ፍርዳቸውን ያጣምማል፡፡ የሀገርና የሕዝብ ሀብት እንዲባክን ያደርጋል፤ ድሆች እንዲበደሉ፤ ንጹሐን ያለ አግባብ ግፍ እንዲደርስባቸው የሚያደርግ የጥፋት መንገድ የከፋት ጎዳና የኃጢአት ትግባር ነው፡፡ ሙስና ተገቢው ነገር ለተገቢው ሰው በተገቢው ሰዓት እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡ ሙስና በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ኃጢአት ነው፡፡ ገንዘብ ለማግኘት ብሎ ሰውን የሚገድል ቅጥር ነፍሰ ገዳይና ጽሃ የሚበድል ዳኛ የተረገመ ይሁን በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያወግዛል፡፡ ሰውና እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ከዚህ ክፉ ኃጢአት ልንርቅና ራሳችንን ልንጠብቅ ይገባናል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ፤ በትምህርት ቤት ሙስና እንዴት ይፈጸማል? እንዴትስ መከላከል ይቻላል? በሚል ርእስ ተዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
- መምህር ለተማሪዎችዎ፤ በሙስና የሚኖሩ ሰዎችን ክፉ ፍጻሜ በመግለጥ በዚህ ክፉ ሥራ እንዳይጠፉ ይምከሯቸው፡፡

### *ጥያቄዎች*

- ሙስና ማለት ምን ማለት ነው? **የቃሉን ትርጉም በማስቀመጥ ስለ ሙስና ምንነት እና መገለጫዎች አብራሩ፡፡**
- ሰዎች መማለጃ(ጉቦ) በመስጠትና በመቀበል የሚያደርሱት በደል ወይም ጉዳት ምን ምንድነው?
- ሰዎች ሙስና የሚፈጽሙት ለምንድን ነው?
- ሙስናን እንዴት መከላከል (መዋጋት) ይቻላል?

www.zeorthodox.org

# ሰላም በክርስትና

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ሰላም ምንነት ተገንዝበው የሰላም መሣሪያ እንዲሆኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ፤ የመምህሩን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል” ፊልጵ. ፬÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሮሜ. ፲፪÷፲፬-፲፰ እና ዮሐ. ፲፬÷፳፯

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰላም ለሰው አስፈላጊ ነው፡፡ ያለ ሰላም መሥራት፣ ወጥቶ መግባት፣ መማማርና ማስተማር አይቻልም፡፡ ሰላም በክርስትና የበለጠ ትርጉም አግኝቷል፡፡ ስለዚህ የክርስትና ሰላም ከዓለም ሰላም ይለያል፡፡ ጌታ ኢየሱስ “ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ግን ዓለም እንደምትሰጠው ሰላም አይደለም” ብሏል፡፡ ዓለም ሰላም አላት፤ ሰላሟ ግን ጊዜያዊ ነው፡፡ የክርስቶስ ሰላም አእምሮን ሁሉ ያልፋል፤ በመከራ የማይጠወልግና በጦርነት የማይደፈርስ ነው፡፡ ከዙፋኑ ወደ አማኞች ልብ የሚፈስ እውነተኛ ሰላም ነው፡፡ ይህ ሰላም የክርስትና ሰላም ይባላል፡፡ የክርስትና ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው፡፡ ገላ ፭÷፳፪፡፡ **መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ከሚያፈራው ፍሬ አንዱ ነው፡፡** የክርስትና ሰላም ሰው በእግዚአብሔር ላይ ተማምኖ በመቆም እንዲያርፍ ያደርጋል፡፡ ሰው ይህን አስተማማኝ ሰላም ለማግኘት፡-

1. ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር ሰላም መሆን አለበት፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሲሆን ከሚያገኛቸው ጥቅሞች አንዱ አስተማማኝ ሰላም ነው፡፡ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ ሰላሙ ደፈረሰ መንፈሱ ታወከ፣ ፍርሃት ነገሠበት፡፡ ሰው በኃጢአት ሲወድቅ ሰላም ያጣል፡፡ በሰላም ለመኖር ከኃጢአት ርቆ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር አለበት፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ከራሱ ጋር ሰላም መሆን አይችልም፡፡ አዳም በክርስቶስ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ፡፡ ሰላማችን ክርስቶስ የጥልን ግድግዳ ሲያፈርስ ከአእምሮ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔር ሰላም አገኘን፡፡ የሰላም አለቃ የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስን የሚያምን ይህን ጸጋ ያገኛል፡፡

www.zeorthodox.org

2. ከሰዎች ጋር ሰላም መሆን አለበት፡፡ ሰው ቢቻለውስ ከሰዎች ሁሉ ጋር ሰላም መሆን አለበት፡፡ ሮሜ ፲፪÷፲፰፡፡ **ነገር ግን ሰው ይህን ዘንግቶ** በጣቶቹ የጦር መሣሪያ ይሠራል፤ የወገኑን ደም ያፈሳል፡፡ ሰው ሰላማዊ እንቅስቃሴ በማድረግ፤ በሰላምና በመግባባት ተከባብሮ መኖር አለበት፡፡ ለሌሎች ደኅንነት ሊጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ክርስቲያኖች የሰላም አርአያዎች ናቸው፡፡ ንጉሣችን ክርስቶስ ‹‹በአፉ ተንኮል አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡትም መልሶ አልተሳደበም፤ መከራን ሲቀበል

አልዛተም” ክፉን በመልካም በማሸነፍ የሰላም አርአያ ሆኗል፡፡ እኛም ከሰዎች ጋር በሰላም በመሆን የሰላም ተምሳሌትነታችንን ማረጋገጥ አለብን፡፡

3. ከራስ ጋር ሰላም መሆን አለበት፡፡ ሰው ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ሰላም ለመሆን ከራሱ ጋር ሰላም መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ ከራሱ ጋር መታረቅ ያስፈልገዋል፡፡ የሚያስጨንቀንን በጸሎት ለእግዚአብሔር ማስታወቅ፣ ከኃጢአት ባርነት መላቀቅና ሰላማዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የራሳችንን ሰላም መጠበቅ ይገባናል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት በማድረግ የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ሰላምን ማፍራትና ለሌሎችም መትረፍ ይጠበቅብናል፡፡ ሰላም በደም መፋሰስ አይመጣም፤ በክርስቶስ መስቀል ነው የሚመሠረተው፡፡ ቆላ. ፩÷፳፡፡ **ሰላም ለሰው ቢያስፈልግም** የሰውን ፈቃደኝነት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሰው ለሰላም በጎ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሞትን እያወጁ ሕይወትን መመኘት፤ ጥላቻ እየዘሩ ፍቅርን ለማጨድ መጠበቅ፤ ጦርነት እያወጁ የሰላምን ፍሬ መናፈቅ ሞኝነት ነው፡፡ የተግባር ፈቃደኝነት ለሁለንተናዊ ሰላም መረጋገጥ ዋስትና ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የክርስትና ሰላም በዓለም ሁኔታዎች የማይመሠረት፣ በመከራ የማይጠወልግ፣ በጦርነት አዋጅ የማይደፈርስ፣ ልብንና አሳብን በክርስቶስ የሚጠብቅ ከአእምሮ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ሰላም ነው፡፡ የክርስትና ሰላም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው፡፡ ሰው ለሰላም የተሠራ መሣሪያ በመሆኑ ለሰላም ተግባራዊ ፈቃደኝነት ማሳየትና ሰላማዊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን ከዚህ በታች በቀረቡት ርእስ ጉዳዮች ላይ ተዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

- ሁለንተናዊ ሰላምን እንዴት ማምጣት ይቻላል? ሰላምን የሚያደፈርሱ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- ሰው እውነተኛ ሰላም ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት?

www.zeorthodox.org

# በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ክፍፍል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ቤተክርስቲያን አንድነት ተገንዝበው፤ በፍቅርና በአንድነት እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸው ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሚያሳድግ **እግዚአብሔር** እንጂ የሚተክል ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም" **፩ቆሮ. ፫÷፯**

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፫÷፩-፱፤ ፩÷፲-፲፯ እና ፊልጵ. ፪÷፩-፯

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሥጋ ለባሾች መካከል እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደሰው ተመላለሰ፡፡ የሕይወትን ቃል የመንግሥቱን ወንጌል እየሰበከ ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትን መረጠ፡፡ በተከታዮቹ የእምነት ቃል ቤተክርስቲያንን መሠረተ፡፡ ከወገንና ከቋንቋ ከሕዝብም ሁሉ በደሙ የዋጃቸው አማኞች በዙ በአንጾኪያም ክርስቲያን ተባሉ፡፡ ያላቸውን በአንድነት አድርገው በጋራ የፍቅር ማዕድ እያካፈሉ መኖር ጀመሩ፡፡ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር፡፡ ሐዋ. ፪÷፵፯፤ ፪÷፵፬-፵፯፡፡

የመከሩ ሠራተኞች በዙ፤ የመንግሥቱ ወንጌል ከአድማስ እስከ አድማስ ደረሰ፤ በየሃገሩ አብያተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ፡፡ በቆሮንቶስ ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን ሰበከ፡፡ የግሪክ አማልክት ከንቱነት የገባቸው የተሰቀለውን ክርስቶስን ለማምለክ ወሰኑ፡፡ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች፡፡ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በአገልጋዮች ስም መከፋፈል ጀመረች፡፡ ሰይጣን በኃጢአት የገነባቸው ከተሞች ሲፈርሱ እያየ ዝም ለማለት አልፈለገም፡፡ የክርስትናውን ጉዞ ለማሰናከል ጠብና ክርክርን፣ ምንፍቅናና ሥጋዊነትን በአማኞች ጉባኤ ዘራ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲሰማ "ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልቦና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ፡፡ እያንዳንዳችሁ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፣ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፣ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ፡፡ ክርስቶስ ተከፍሏልን? ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቅሏልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?" በማለት የግሣጼ መልእክት ጻፈላቸው፡፡ **፩ቆሮ. ፩÷፲**፡፡

የክርስትና ጉዞ በአንድ ልብና በአንድ አሳብ የምንጓዝበት ሕይወት ነው፡፡ ጠብ፣ ክርክር፣ ልዩነት፣ መናፍቅነትና አድመኝነት ዲያብሎስ የሚዘራቸው እንክርዳዶች ናቸው፡፡ የክርስትና ዘር የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው፡፡ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ግን ለአራት ተከፋፍላ የጳውሎስ፤ የአጵሎስ፣ የኬፋ (የጴጥሮስ) እና የክርስቶስ በሚሉ ቡድኖች ተጨንቃ ነበር፡፡ እንደ ባቢሎን ሰዎች አንዱ

የአንዱን አይሰማም ነበር፡፡ አገልጋዮች በፍቅርና በሰላም አብረው ሆነው እግዚአብሔርን በጽድቅ እንዲያመልኩት ቅዱስ ጳውሎስ አስተማራቸው፤ እነርሱ ግን የልዩነት አሳብ ያራምዱ ነበር፡፡ የጳውሎስ ምክር ክርስቶስ አንድ ነው፤ አልተከፈለም፤ በእኔ ስም አልተጠመቃችሁም እኔ አልተሰቀልኩላችሁም የሚል ነበር፡፡ እውነት ነው የተጠመቅነው በሥላሴ ሥም፤ የተሰቀለልን ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ በአገልጋዮች ስም መከፋፈል አይገባም፡፡

የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያንም እንደቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መከራ ከቧታል፡፡ ልጆቿ በዘር፣ በቋንቋ፣ በአገልጋዮች ስምና በአመለካከት ልዩነት ተከፋፍለዋል፡፡ የክፍፍሉ መንሥኤዎች፡-

1. የክርስትናን ኑሮ አለመረዳት
2. የራስ ወዳድነትና የጥቅመኝነት መንፈስ አገልጋዮችን ስለወረሰ
3. የፍቅር መቀዝቀዝና የልዩነት ምኞትን መከተል
4. በእግዚአብሔር ቃል ለመኖር አለመፈለግና መልካም መስሎ የታየንን ማድረግ ናቸው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ “አገልጋዮች ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግሉ፡፡ እኔ ተከልኩ አጴሎስም አጠጣ እግዚአብሔር ግን ያሳድግ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፡፡ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና፡፡” በማለት የፍቅር መልእክት ጻፈላቸው፡፡ **፩ቆሮ. ፫÷፭-፲፬**፡፡ አገልጋዮች እንደተሰጣቸው ጸጋ ያገልግሉ፡፡ ሁላችንን የሚያሳድገውን እግዚአብሔርን በአንድነት እናምልክ፡፡ የእግዚአብሔር ሕንፃ ከሆንን መሠረቱ አንድ ነው፤ ሌላ መሠረት መመሥረት አያስፈልግም፡፡

## ማጠቃለያ

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ነበር፡፡ ዛሬም የክርስትናው ዓለም ትልቅ ውድቀት መከፋፈል ነው፡፡ ክርስትና በአንድ ልብ የምንጓዝበት መንገድ፤ በአንድ አሳብ የምንመራበት ሕይወት፤ በአንዲት ጥምቀት ክርስቶስን የለበስንበት ሃይማኖት፤ አንዱን ጌታ የምናመልክበት እምነት ነው፡፡ ስለዚህ የተሰቀለውን ክርስቶስን በማየት በፍቅርና በሰላም በአንድነት መኖር አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎን፤ በጉባኤ ኬልቄዶን ክርስትና ለምን ለሁለት ተከፈለ? በአማኞች መካከል ያለውን ክፍፍል እንዴት መፍታት እንችላለን? በሚሉ አርእስቶች ላይ ተዘጋጅተው እንዲወያዩ እና የመፍትሔ ሐሳቦችን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት በጋራ እንዲጸልዩ ያድርጉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

- የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተከፋፈለችበት ምክንያት ምንድነው?
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች የገሠጻቸው ምን በማለት ነበር?
- የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ፈተና የሆነው የመከፋፈል ችግር መንሥኤዎችን ምን ምን ናቸው?
    - ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ወጣቶች ማድረግ የሚጠበቅባቸው ድርሻ ምንድነው? **አብራሩ፡፡**

www.zeorthodox.org

# ሰማዕታት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ሰማዕትነትና ሰማዕታት ያውቃሉ፤ ለክርስትና ጉዞ ሰማዕታት የከፈሉትን መሥዋዕትነት ተገንዝበው፤ የሰማዕታትን ጽናትና አርአያነት ይከተላሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፡፡ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ በተራራ፣ በዋሻው በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ" ዕብ. ፲፩÷፴፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ማቴ. ፲፮÷፳፬፤ ዕብ. ፲፫÷፲፫-፲፬ እና ፪ጢሞ. ፪÷፲፩-፲፫

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሰማዕት ማለት ምስክር ማለት ነው፡፡ ሰማዕታት የክርስቶስ ሕይወትና ትምህርት ምስክሮች ናቸው፡፡ ክርስትና የምስክርነት ሕይወት ነው፡፡ ሰው የሚድነው በልቡ አምኖ በአፉ እምነቱን ሲመሰክር ነው፡፡ ሮሜ.፲÷፱፡፡ **ሰማዕታት በልባቸው አምነው ያተሙትን** የክርስትና እውነት፤ የክርስቶስን የማዳኑን ዜና በአንደበታቸው መስክረዋል፤ ምስክርነታቸውን ያልተቀበሉ ተቃወሚቻው፤ በሰይፍም ገደሉአቸው፡፡ ሰማዕታት በሥራቸው ሕያዋን በእምነታቸው የሕይወት መምህራን ናቸው፡፡

ክርስትና የሮምን ድንበር ተሻግሮ አራቱንም ማዕዘናት ያካለለው በሰማዕታት መሥዋዕትነት ነው፡፡ የክርስቶስ ኢየሱስ የማዳኑ ዜና የምስራቹም ድምፅ ለዓለም የደረሰው ለትውልድም የተሻገረው በሰማዕታት ደም ነው፡፡ የሰማዕታት የጸና እምነት ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አምጥቷል፡፡

ሰማዕታት ምቹ ከሆነው ኑሯቸውና ከሞቀ ቤታቸው የወጡት ስለክርስቶስ ፍቅር ነው፡፡ "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፣ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ራብ ወይስ ራቁትነት ፍርሐት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን፤ ሞት፣ ሕይወት፣ ከፍታ፣ ዝቅታ፣ ማግኘት፣ ማጣት ከፍቅሩ አይለየንም" በማለት ደማቸውን ስለ ፍቅሩ አፈሰሱ፤ መራራ ሞትን ስለ መንግሥቱ ታገሡ፡፡ ሮሜ. ፰÷፴፭-፴፱፡፡ ሰማዕታት በአላውያን ነገሥታት እየተሰቃዩ እስከ ሞት ድረስ ሰማዕትነትን የተቀበሉት እምነታቸውን ለመጠበቅ፤ ሃይማኖታቸውን ላለመካድ ሲሉ ነው፡፡ የጸና ተጋድሏቸው ብዙ አማኞችን አፍርቷል፤ ክርስትናንም ለእኛ አድርሷል፡፡ እስከ ሞት ድረስ መታመናቸው የሕይወትን አክሊል አሸልሟቸዋል፡፡ ስለ ምስክሩ ቃል የተገፉ ሁሉ ሰማዕታት ይባላሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ወጣቶች ራስን መግዛት፣ ክፉን በመልካም መመለስ፣ ከኃጢአት እርቆ በጽድቅ ሥርዓት መጓዝና ትክክለኛይቱን እምነት ጠብቆ መኖር የዘመናችን ትልቁ ሰማዕትነት ነው፡፡ በወጣትነት ዘመናችን የምንፈተንባቸውን ነገሮች በድል መወጣት አለብን፡፡ ክፉ

ምኞት፣ ዝሙት፣ ትዕቢትና ፀብ በወጣትነታችን ወቅት የሚፈታተኑን ናቸው፡፡ እነዚህን ድል ከነሳን ክብር ይጠብቀናል፡፡

ሰማዕታት የዓለምን ክብር፣ የመንግሥታትን ሹመት፣ ገንዘብና ድሎት ንቀው ሁሉን እያጡ መከራንም እየተቀበሉ በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡ ብዙ አማራጮች ቀርበውላቸዋል፡፡ ነገር ግን ምርጫቸው ክርስቶስ ነበር፡፡ ሰማዕትነት ማለት ያለንን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መተው፤ ፈቃዳችንን ለፈቃዱ መሠዋት ማለት ነው፡፡

ሰማዕታት የክርስትናን ኑሮ በሚገባ ኖረውበታል፡፡ በቃልና በሥራ የተገለጠ ሕይወት አላቸው፡፡ ክርስትና ወሬ ሳይሆን ሕይወት ነው፡፡ ለቃሉ በመታዘዝ በእምነት የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን እንምሰል፡፡

## ማጠቃለያ

ሰማዕታት የክርስቶስ የማዳን ዜና የሕይወት ምስክሮች ናቸው፡፡ ክርስትና የሮምን ድንበር ተሻግሮ ለእኛ የደረሰው በሰማዕታት መሥዋዕትነት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ጉዞ የቀጠለው በሰማዕታት የጸና ተጋድሎ ነው፡፡ የወጣትነት ተግዳሮቶችንና ክፉ መሻቶችን ማሸነፍ ትልቅ ሰማዕትነት ነው፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ፤ ስለ አንድ ሰማዕት አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

- ሰማዕት ማለት ምን ማለት ነው?
- ሰማዕትነት በምን ይገለጻል? **አብራሩ፡፡**
- አሁን ባለንበት ዘመን የክርስቲያኖች ሰማዕትነት ምንድነው? **አብራሩ፡፡**
- በወጣትነታቸው ሰማዕት የሆኑ እነማን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ያሬዳዊ ዜማዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ያሬዳዊ ዜማ ምንነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ" ኤፌ. ፭÷፲፱

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፶÷፩-፮፤ ዕብ. ፲፫÷፲፭ እና ያዕ. ፭÷፲፬

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ያሬድ ኢትዮጵያዊ የዜማ አባት ነው፡፡ ያሬድ ከመላእክት የተማረውን ምስጋና ለኢትዮጵያውያን አበርክቷል፡፡ ያሬድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ ያላቸው ድርሰቶችን ጽፏል፡፡ እነርሱም፡- ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋስዕት ይባላሉ፡፡ ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔርን በአዲስ ቅኔ በመላእክተ ዜማ ያመሰገነ ሊቅ ነው፡፡

የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች ግእዝ፣ ዕዝል፣ አራራይ ይባላሉ፡፡ እነዚህን የዜማ ስልቶች የሚመሩ ምልክቶችንም ቀምሯል፡፡ እነዚህም ምልክቶች ደረት፣ ድፋት፣ ጭረት፣ ርክርክ፣ ቅናት፣ ቁርጥ፣ ድረስ፣ ሂደት፣ ይዘት ናቸው፡፡

ያሬዳዊ ዜማ የራሱ የሆነ ስልት ዜማና ምልክት ያለው የተቀመረ ዜማ ሲሆን፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብት ነው፡፡ ያሬዳዊ ዜማ ዓለምን ያስደነቀ የኢትዮጵያውያን ትምክህት ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ ዓመቱን በአራቱ ወቅቶች ከፍሎ፣ ወቅቶቹን በበዓላት ከፋፍሎ፣ ወንጌልን በዜማ አስተምሯል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ አምልኮ የሚመራው በቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው፡፡

የቅዳሴ ሥርዓት በጾም ወራት በግእዝ፣ በበዓላት ጊዜ በእዝል፣ የደብረ ታቦር ደግሞ በአራራይ ይከናወናል፡፡ ሥርዓተ ማኅሌቱ በድጓው ይትበሃል ይመራል፡፡ ሰዓታቱ የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት ሲሆን በያሬዳዊ ዜማ ይቆማል፡፡ በአጠቃላይ የያሬድ ዜማዎች በቤተ ክርስቲያናችን ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ቤተክርስቲያናችን የራሷ ዜማና የዜማ መሣሪያ፣ የራሷ የሆነ የቋንቋና የዘመን መቁጠሪያ ያላት የኢትዮጵያ ውብ መልክ ናት፡፡

www.zoorthodox.org

ይህን መልካችንን እንደ ተዋበ መጠበቅ፤ የተረከብነውን የአበው አደራ ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ ይጠበቅብናል፡፡ በምዕራባውያን ዜማ እየተታለልን ዓለምን ያስደነቀውን የእኛን ዜማ መርሳትም የለብንም፡፡

## ማጠቃለያ

ያሬዳዊ ዜማ የራሱ የሆነ ስልት፣ ዜማና ምልክት ያለው የተቀመረ ዜማ ነው፡፡ ያሬዳዊ ዜማ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት

አምልኮ የሚፈጸምበት ነው፡፡ ያሬዳዊ ዜማ ጆሮ የሚማርክ ልብን የሚያስደስት መንፈስን የሚቀድስ ዜማ ነው፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ ስለ ያሬዳዊ ዜማ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ያሬዳዊ መዝሙሮችን እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ ያሬድ ማን ነው? **ምን አድርጓል**?
- ☞ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ምን ምን ይባላሉ?
- ☞ የዜማ ስልቶቹ ስንት ናቸው? **በዝርዝር ግለጹ**፡፡
- ☞ የዜማ ምልክቶቹ ስንት ናቸው? **በዝርዝር ግለጹ**፡፡
- ☞ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ያላቸውን ጠቀሜታ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የእግዚአብሔር መገለጥ በብሉይ ኪዳን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ እንዴት እንደተገለጠ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም" ዘጸአት ፴፫÷፳

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፩÷፲፰፤ ዮሐ. ፲፬÷፱ እና ዕብ. ፩÷፩-፫

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**የእግዚአብሔር መገለጥ (God's Revelation)**

እግዚአብሔር በመታወቅ የሚመለክ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ በብዙ ዓይነትና ጎዳና ገልጧል፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን መገለጥ (Objective Revelation) **በተፈጥሮና በኅሊና ይረዳል፡፡ ሰው ዓይኖቹን ከፍቶ ተፈጥሮን በማየት እግዚአብሔርን ማመን ይችላል፡፡** ተፈጥሮ እግዚአብሔርን የምናውቅበት ገጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃልና፡፡ ሰው ኅሊናውን አድምጦ ፍሊጋውን ተከትሎ ወደ እግዚአብሔር መድረስ ይችላል፡፡ ሕግና እግዚአብሔርን እንድናውቅ የሚቀሰቅስ ደወል ነው፡፡ ሰው ዓይኑን ጨፍኖ፤ ጆሮውን ደፍኖ "እግዚአብሔር የለም" ቢል የራሱን ስንፍናና ሞኝነት ይገልጻል፡፡ ምክንያቱም ዓይኑን ከፍቶ ተፈጥሮን በማየትና ኅሊናውን አድምጦ ፍሊጋውን በመከተል እግዚአብሔርን ማግኘት ስለሚችል ነው፡፡

ለአማኞች የእግዚአብሔር መገለጥ (Subjective Revelation) **መጽሐፍ ቅዱስና ክርስቶስ ኢየሱስ ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለሚያምኑ መገለጡን ይመሰክራል፡፡** "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" ይለናል፡፡ ዕብ. ፩÷፩-፫፡፡ ልጁ የሚለን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡ እግዚአብሔር በልጁ ያደረገው መገለጥ የመገለጦች ሁሉ ዘውድ ነው፡፡ የማይታየው አምላክ ክርስቶስ በሚታየው ሥጋ ተገልጧል፡፡ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ የተሰቀለውን ክርስቶስን በማየት የእግዚአብሔርን መገለጥ ያውቃሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ "እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፡፡ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው" ይለናል፡፡ ዮሐ. ፩÷፲፰፡፡ **እግዚአብሔርን በአንድ ልጁ በክርስቶስ አይተነዋል፡፡ በልጁም** ተረካ አውቀነዋል፡፡፡ ጌታ ኢየሱስን ፊልጶስ "አብን አሳየንና ይበቃናል" አለው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቁኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል" አለው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ያየ እግዚአብሔርን አይቷል፤ እርሱ እግዚአብሔር ነውና፡፡

### *የእግዚአብሔር መገለጥ በብሉይ ኪዳን*

**እግዚአብሔር መገለጥ የጀመረው ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ ነው፡፡** አዳምን “ወዴት ነህ?” እያለ ጠራው፡፡ ዘፍ. ፫÷፰፡፡ **እግዚአብሔር ለአባታችን ለአብርሃም በአረጋዊ ሰው አምሳል ተገልጧል፡፡** ዘፍ. ፲፰÷፩-፲፯፡፡ እግዚአብሔር በሚታገል ጎልማሳ አምሳል ለያዕቆብ ተገልጧል፡፡ ዘፍ. ፴፪÷፳፬-፴፪፡፡ እግዚአብሔር ለሙሴ ከእግሩ በታች እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ሆኖ ተገልጧል፡፡ ዘጸ. ፳፬÷፲፡፡ **እግዚአብሔር ለዳንኤል በአረጋዊ ሰው አምሳል ተገልጧል፡፡ ዳን. ፯÷፲፫-፲፬፡፡** በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን በአረጋዊ ሰው አምሳል፣ በተፈጥሮ፣ በህልምና በራእይ ተገልጧል፡፡ የብሉይ ኪዳን መገለጦች ሁሉ ፍጹም አልነበሩም፡፡ ፍጹም መገለጥ የተገለጠው በሐዲስ ኪዳን ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን መገለጦች ጥላ ናቸው፤ አካሉ ክርስቶስ በዘመን መጨረሻ በሥጋ ተገልጧል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎደና ለአባቶቻችን ተገልጧል፡፡ በብሉይ ኪዳን በሰው፣ በተፈጥሮ፣ በቃል፣ በህልምና በራእይ የተገለጠ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ራሱ ክርስቶስ ተገለጠ፡፡ እርሱም የጥላዎቹ ሁሉ አካል ነው፡፡

## ተግባር

- *መምህር፤ ተማሪዎችዎን በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ የእግዚአብሔር መገለጥ ለእምነታችን ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? አሁን እግዚአብሔርን እንዴት እናየዋለን?*

### *ጥያቄዎች*

- ሰው የእግዚአብሔርን መገለጥ በምንና እንዴት ሊረዳው ይችላል?
- **እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ራሱን የገለጠበት ዓላማ ምንድነው?**
- **እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለነበሩ ወዳጆቹ እንዴት ተገለጠላቸው? ምሳሌዎችን በማስረጃ እያቀረባችሁ አብራሩ፡፡**

www.zeorthodox.org

# ዕጣን በቤተ ክርስቲያን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ዕጣን ምንነትና የቤተ መቅደስ አገልግሎት ያውቃሉ፡፡ ለቤተ ክርስቲያን መብዓ ማቅረብን በተግባር ይለማመዳሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ" ራዕ. ፭÷፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘጸ. ፴÷፴፩-፴፰፤ ማቴ. ፪÷፲፩ እና ራዕ. ፰÷፫-፭

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዕጣን በበረሐ ከሚበቅል የዕጣን እንጨት(ጫፍ) የሚለቀም ሙጫ ሲሆን ከሌላ ሽቱ ጋር ተቀምሞ በእግዚአብሔር ድንኳንና መቅደስ ውስጥ ይታጠን ነበር፡፡ ዘጸ. ፴÷፴፩-፴፰፣ ዘሌ. ፲፮÷፲፫፡፡ **የዕጣን ጢስ የምስጋናና የጸሎት ምሳሌ ነው፡፡ መዝ. ፻፵፩÷፪፡፡ የእስራኤል ሕግ ካህናቶች ብቻ ዕጣን እንዲያጨሱ ይፈቅዳል፡፡** ዘጸ. ፴÷፯-፱፡፡ የቆሬ ልጆች በይገባኛል ጽንሃት አጥተው በማጠናቸው እግዚአብሔር ቀጣቸው፡፡ ዘእ. ፲፮÷፩-፲፩፡፡ **ዕጣን በማዘጋጀት ጥበብ የግብጽና** የዐረቢያ ሰዎች ይታወቃሉ፡፡

የጥበቡ ሰዎች ለክርስቶስ ይዘውት ከመጡት መብዓ አንዱ ዕጣን ነበር፡፡ ማቴ. ፪÷፲፩፡፡ **ለክርስቶስ ክህነት የዕጣን** መብዓ ይቀርብለታል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሊፈታው ያልቻለውን ማኅተም ሊፈታ መጽሐፉንም ሊዘረጋ እንደተገባው መልአኩ በተናገረ ጊዜ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በፊቱ ወደቁ፡፡ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ አመሰገኑትም፡፡ ራእ. ፭÷፰፡፡ **በሰማያውያንና በምድራውያን የሚመሰገነው ጌታ የዕጣን ጢስ በያዙ** አመስጋኞች ነው፤ ዕጣን ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት ይጨመራል፡፡ ራእ. ፰÷፫፡፡ **ዕጣን የዕርገተ ጸሎት ምሳሌ ነው፡፡ ከጸሎታችንም ጋር ወደ** እግዚአብሔር ፊት ይወጣል፡፡ "የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ" ተብሎ እንደተጻፈ፡፡ ራእ. ፰÷፬፡፡ **ዕጣን በቤተ ክርስቲያናችን የአምልኮ ሥርዓት መፈጸሚያና ለአገልግሎት የሚውል መልካም** መዓዛ ያለው መብዓ ሲሆን በዕብራውያን የአምልኮ ሥርዓት የተለመደ፤ በእኛም መቅደስ የተወደደ መዓዛ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ዕጣን መልካም መዓዛ ያለው ከበረሓ ተክል(ዛፍ) የሚገኝ ሲሆን ለክርስቶስ ዘላለማዊ ክህነት የሚቀርብ መብዓ ነው፡፡ የዕጣን ጢስ የምስጋናና የጸሎት ምሳሌ፤ እሳቱ የመንፈስ ቅዱስ መኖር ምልክት ነው፡፡ ዕጣን በዕብራውያን ድንኳንና በእኛ ቤተ መቅደስ የአምልኮ ሥርዓት ውበት ነው፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ገንዘብ አዋጥተው ዕጣን በመግዛት ለገጠር ቤተ ክርስቲያን እንዲያበረክቱ ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

1. ዕጣን ምንድነው? ከየት ይገኛል?
2. ዕጣን ለምን ይጠቅማል? በቤተ መቅደስ ስላለው አገልግሎት በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡
3. ዕጣን እና የቅዱሳን ጸሎት አብረው የተገለጡት እንዴት ነው?
4. የዕጣን ጢስ ምሳሌ ምንድነው? የእሳቱ(ፍህሙ)ስ?

www.zeorthodox.org

# ቅዱሳት ሥዕላት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ቅዱሳት ሥዕላት ምንነት፣ ምሳሌነታቸው፣ ምስጢርና የሚያስተላልፉት መልእክት እንዲሁም ስለ አገልግሎታቸውና አቀማመጣቸው ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የሠራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው፡፡ ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትናፍቃች፡፡" መዝ. ፹፫÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፳፩÷፩፤ እና ዘጸ. ፴፮፣፴፯

## መግቢያ

- የቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎት ምንድን ነው?
- በካታኮምብ ስለነበረው ስዕል ታውቃላችሁ?
- ስለ ቅዱሳት ስዕላት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱሳት ሥዕላት ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ የክርስትና አንደበት ናቸው፡፡ በመጀመያዎቹ ክርስቲያኖች ዘመን ቅዱሳት ሥዕላት ማስተማሪያ ነበሩ፡፡ ቅዱሳት ሥዕላት በጸሎት ጊዜ ሐሳባችንን ሰብስበን በእግዚአብሔር ፊት መቆማችንን አስበን እንድንጸልይ ይረዱናል፡፡ የእግዚአብሔር መገለጫዎች ናቸው፡፡ ለመንፈሳዊው የክርስትና መልእክት መገለጫ የሆኑት ቅዱሳት ሥዕላት ከዓለም ፎቶዎችና ምስሎች ይለያሉ፤ የእግዚአብሔር ኃይሉና ክብሩ ይገለጥባቸዋልና፡፡

www.zeorthodox.org

በቤተ ክርስቲያናችን የቅዱሳት ሥዕላት የአሣሣል ዘይቤና የኀብረ ቀለም ምርጫ ትውፊትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የክርስትናው ትምህርት ማንፀባረቂያ በመሆናቸው ምሳሌዎችን በማመሳጠር ይሣላሉ፡፡ የሰማዕታት በቀይ ቀለም፣ የክርስቶስ በነጭ ቀለም፣ የድንግል ማርያም ነጭ፣ ሰማያዊ እና ቀይ በሆነ የቀለም ምርጫ ይሣላሉ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስን ጋሻ አስይዞና ቅዱስ ሚካኤልን እግሩን አራቁቶ መሣል የቤተ ክርስቲያን ትውፊት አይደለም፡፡

በቤተ ክርስቲያን የሥዕላት አደራደር ክብርንና ምስጢርን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

**ከላይ፡-** የሥላሴና የክርስቶስ ስቅለት

**በግራ፡-** የእመቤታችን ሥዕለ አድኖና የቅዱሳን መላእክት ሥዕል

**በቀኝ፡-** የሐዋርያት፣ የዮሐንስ መጥምቅ፣ የቅዱሳንና የሰማዕታት

በቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ የሰጎን እንቁላልና የመስቀል ምልክት ይደረጋል፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱሳት ሥዕላት የክርስትና ጥልቅ መልእክት ገላጮች ናቸው፡፡ በጸሎት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት መቆማችንን እንድናስተውል ይረዱናል፡፡ በቤተ ክርስቲያን የሥዕላት አሣሣልና አቀማመጥ ትውፊትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት ተጨማሪ ጥናት አድርገው እንዲያቀርቡና በክፍል ውስጥ እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. በቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎት ምንድነው? በምንጸልይበት ጊዜስ?
2. በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘመን የቅዱሳት ሥዕላት አገልግሎት ምን ነበር?
3. በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ቅዱሳት ሥዕላት ሲሳሉ የቀለም አመራረጥና አጠቃቀም ትውፊትን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የሰማዕታት ሥዕል ሲሣል ምን ዓይነት ቀለም መጠቀም እንደሚገባ ግለጹ፡፡
4. በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት ተደርድረው ሲቀመጡ፤ ከላይ፣ ከግራ፣ ከቀኝ የሚቀመጡት ሥዕላት ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ምስጢረ ቁርባን (አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ቅዱስ ቁርባን ምንነንት ተገንዝበው በመቀበል በቅድስና የሚኖሩበትን ዕውቀት ይጨብጣሉ፤ በተግባር ይኖሩበታል፤ መምህሩ የሚሰ ጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ" ፩ቆሮ. ፲፩÷፳፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፲፩÷፲፯-፴፬፤፲÷፲፭-፲፯ እና ዮሐ. ፮÷፶-፶፱

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በቤተ ክርስቲያናችን ሰባት ምስጢራት አሉ፡፡ እነዚህ ምስጢራት በሚታይ አገልግሎት የማይታየውን የእግዚአብሔር ጸጋ ያሰጣሉ፡፡ **በጥምቀት** ልጅነትን፤ **በሜሮን** የልጅነት ጸጋን፤ **በቁርባን** የዘላለም ሕይወት፤ **በንስሐ** የኃጢአት ስርየትን፤ **በቀንዲል** ፈውስን፤ **በተክሊል** አንድነትን እናገኛለን፡፡ በክህነት አገልጋዮች የአገልግሎት ሥልጣንን ተቀብለዋል፡፡

ምስጢራትን በመፈጸም አርአያችን የምስጢራቱ ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ተብለን መንፈሳዊውን ዓለም የተቀላቀልነው በምስጢረ ጥምቀት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን በሜሮን መንፈስ ቅዱስ አትሞ ለቤዛ ቀን አጭቶናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እያደረግን ለመኖር ደግሞ ቅዱስ ቁርባን መቀበል አለብን፡፡

ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ምስጢረ ቁርባን ነው፡፡ ምስጢር የተባለው ላመኑና ለተጠመቁ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ስለሆነ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን ከእግዚአብሔር ጋር ላለን የማይታይ ቃል ኪዳን የሚታይ የቃል ኪዳን ምልክት ነው፡፡

የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት መሥራች ራሱ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቁርባኑም የእርሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው፡፡ የመጨረሻውን እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በቀረበ ጊዜ "እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው፡፡ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች በኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡" አላቸው፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳፮-፳፱፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ ይህን አስታውሶ "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፤ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ" አለ፡፡ **፩ቆሮ. ፲፩÷፳፮**፡፡

ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉና እንዲያቀብሉ ሥርዓት ሠርቶ በማስተማር አዟል፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያትም በዘመናቸው ሁሉ ይህን ቅዱስ ሥርዓት በመፈጸም ሞቱንም በመናገር የጌታን ትእዛዝ ፈጽመዋል፡፡ እኛም ታዝዘን ቃሉን በመጠበቅ የኅልማሳነት መንገዳችንን ልናነፃ ይገባል፡፡

በክርስቶስ ያመነ ሰው ወደዚህ የሕይወት ማዕድ መድረስ አለበት፡፡ አንድ አማኝ ቅዱስ ቁርባን ሲቀበል እምነቱ ያድግለታል፡፡ የኃጢአት ስርየት አግኝቶ የክርስቶስን ጽድቅ ለብሶ መንግሥቱን ይወርሳል፡፡

- ቅዱስ ቁርባን ለምን እንቀበላለን?
- የኃጢአት ስርየት (የእግዚአብሔርን ይቅርታ) ለማግኘት፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳፯
- ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ጠብቀን ለማቆየትና ግንኙነታችንን ለማሳደግ፡፡ ዮሐ. ፮÷፶፯
- እምነታችንን በመጠበቅና በማሳደግ የዘላለም ሕይወት ለማግኘት፡፡ ዮሐ. ፮÷፶፫
- የጌታን ሞት ጌታ እስኪመጣ ለመናገር (ለመመስከር)፡፡ ፩ቆሮ. ፲፩÷፳፮፡፡
- በትንሣኤ ሙታን ፊተኛ ሆኖ ለመነሣት፡፡ ዮሐ. ፮÷፶፬፡፡
- የጌታን ትእዛዝ ለመፈጸም፡፡ ማቴ. ፳፮÷፳፮፡፡

**ቅዱስ ቁርባን ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ እንጂ ከሰው ለእግዚአብሔር የቀረበ አይደለም፡፡ ቅዱስ ቁርባን ከክርስቶስ ጋር ጽኑ ኅብረት የምንመሠርትበት ምስጢር ነው፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም "ቅዱስ ቁርባን ስንቀበል ከክርስቶስ ጋር በፍጹም ቃል ኪዳን እንተሳሰራለን፡፡ የመለከቱ ባሕርይ ተካፋዮች እንሆናለን" በማለት የኅብረቱን ጽኑነት ይነግረናል፡፡**

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቁርባን ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት የሚታይ የቃል ኪዳን ምልክት ነው፡፡ የሞትን ባሕር ቀዝፈን የሕይወት ደጆችን የምናንኳኳበት በደሙ የተሰጠ ሥልጣን በዚህ ምስጢር እንቀበላለን፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ለማሳደግ ቅዱስ ቁርባን በዘመናችን በመቀበል ሞቱን መናገር አለብን፡፡

## ተግባር

- በብሉይ ኪዳን የቅዱስ ቁርባን ምሳሌዎችን በማጥናት በአጭር ጽሑፍ መምህሩ እንዲያቀርቡ ያድርግ፡፡

www.zoorthodox.org

***ጥያቄዎች***

- በቤተ ክርስቲያናችን ሰባት ምስጢራት አሉ፡፡ ምን ምን ናቸው? የምናገኝባቸው መንፈሳዊ ጥቅም ምንድነው?
- ቁርባን (ቅዱስ ቁርባን) ምንድነው? አብራሩ፡፡
- ቅዱስ ቁርባን የሚሰጠው ለማን ነው?
- የቅዱስ ቁርባን መሥራች ማን ነው? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ግለጹ፡፡
- ቅዱስ ቁርባን የምንቀበለው ለምንድነው? በማብራራት ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ምስጢረ ቁርባን (ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ቅዱስ ቁርባን ሰፊ ዕውቀት ያገኛሉ፤ የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፈጻሚዎች (ተከታዮች) ሆነው የክርስቲያናዊ ሕይወት መንገዳቸውን በበረከት ይጓዛሉ፡፡ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ዮሐ. ፮፥፶፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፮፥፵፰-፶፱፣ ፩ቆሮ ፲፩፥፲፱-፴፬፣ ፩ቆሮ. ፲፥፲፭-፲፯፣ ምሳ. ፱፥፩ እና ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፯

## መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ከምትፈጽምባቸው፤ በረከት ከምታካፍልባቸው አገልግሎቶች አንዱ ቅዳሴ ነው፡፡ ቅዳሴ በትምህርት ራሳችንን የምንገሥፅበት፣ በጸሎት ጥያቄያችን መልስ የሚያገኝበት፣ በዜማ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበትና በቃል ኪዳኑ ምልክት (በሥጋ ወደሙ) የምንታተምበት አገልግሎት ነው፡፡ ቅዳሴ ትምህርት፣ ጸሎት አምልኮትና ባርኮትን ያካተተ የሥርዓተ አምልኮ ክፍል ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ተዘጋጅተን ቅዳሴ ማስቀደስ አለብን፡፡ ስለተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች በጋራ የምንጸልየው፤ በነገር ሁሉ የረዳንን እግዚአብሔር በዜማ የምናመሰግነው በቅዳሴ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ምስጢረ ቁርባን ላመኑ ሰዎች በቅዳሴው ፍጻሜ ይሰጣል፡፡ ለዓለም ዓለም ምስጉን የሆነውን አምላክ እያመሰገንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በመቀበል ለኃጢአታችን ስርየት እናገኛለን፤ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት እናጠናክራለን፡፡ ቅዱስ ቁርባን በቀራንዮ ስለእኛ የተከፈለልንን የክርስቶስ ኢየሱስን መከራ የምናስታውስበት አእምሮ ነው፡፡ ደግሞ እስኪመጣ ስለእኛ መሞቱን የምንናገርበት አንደበት ነው፡፡ ቅዱስ ቁርባን የአንድነታችን ማኅተም የኅብረታችን ማረጋገጫ ነው፡፡ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር፤ የምንቆርሰውም እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት አለው፡፡፡ አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፡፡" ፩ቆሮ. ፲፥፲፮-፲፯፡፡

እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ምድረ ርስት ከነዓንን እስኪወርሱ ድረስ የዕለት ውኃ ይጠጡ የሰማይ መና ይመገቡ ነበር፡፡ እኛም ሰማያዊት ርስት ኢየሩሳሌምን እስክንወርስ ድረስ ቅዱስ ቁርባን እንቀበላለን፡፡ እነርሱ ሞተዋል፤ እኛ ግን በልተን እንዳንሞት ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ ክርስቶስን አመንን፡፡ "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፡፡ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡" ዮሐ. ፮፥፶፡፡

የእስራኤል መናና የኦሪት መስዋዕቶች የቅዱስ ቁርባን ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ዕውቀት ለጎደላቸው እውቀትን የሚሰጥ ለሚች

www.zoorthodox.org

*ሥጋ ዘላለማዊነትን የሚያረጋግጥ የጥበብ ማዕድ በመቅደሱ አለ፡፡ ጥበብ በመገረፉ ቁስል የፈወሰን፤ በደሙ በተደረገ ቤዛነት ከሞት ፍርሃት ያዳነን፤ በሥጋው በተደረገ ሞት ያስታረቀን የታረቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሮሜ.* ***፭÷፲፣ ፩ጴጥ. ፪÷፳፭*** *እና ዕብ.* ***፪÷፱-፲፯***፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ቀርባንን የጥበብ ማዕድ ነው፡፡ ጥበብ ክርስቶስ በነፃ ማዕዱን እንድንካፈል በአገልጋዮቹ ጠርቶናል፡፡ በቀራንዮ የተከፈለልንን ውለታ በማሰብ ሞቱን ለመናገርና የኃጢአት ስርየት ለማግኘት ከዚህ የሕያዋን ማዕድ እንካፈል፡፡ ሥጋውን ስንበላ ደሙን ስንጠጣ ሕያው እንጀራ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ዓለምነት እንንቀሳቀሳለን፤ የዘላለም ሕይወትንም ይሰጠናል፡፡

## ተግባር

- *መምህር ተማሪዎችዎን ንስሐ ገብተው ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ያበረታቷቸው፡፡*

***ጥያቄዎች***

- ቅዳሴ ምንድነው? **በተማራችሁት መሠረት አብራርታችሁ ግለጹ፡፡**
- **ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ማሟላት የሚገባን ነገር ወይም ዝግጅት ምንድነው? ምን ማድረግ አለብን?**
- **ቅዱስ ቁርባን በቅዳሴ በየትኛው ጊዜ ወይም መቼ ይሰጣል?**

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ዕዝራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ መጽሐፈ ዕዝራ ያውቃሉ፤ እግዚአብሔር ቃሉን በጊዜው እንደሚፈጽም ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አቤቱ የእስራኤል አምላክ ሆይ አንተ ጻድቅ ነህ" ዕዝ. ፱÷፲፭

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ዕዝራ ፩-፲ እና ዕብ. ፫፤፬

## መግቢያ

እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ምድረ ርስት ከገቡ በኋላ በጠላት ይማረኩ በአሕዛብ ነገሥታት ይወረሩ ነበር፡፡ መጽሐፈ ዕዝራ እስራኤላውያን በናቡከደነፆር ተማርከው ወደ ባቢሎን መውረዳቸውንና እግዚአብሔር ነፃ እንዲያወጣቸው መጮሃቸውን የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡

- እስራኤላውያን፡- ከግብጽ የወጡት በ1440 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ከነዓን የገቡት በ1400 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ሳዖል ንጉሥ ሆኖ የገዛቸው በ1043 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ዳዊት የነገሠላቸው በ1025 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ለሁለት የተከፈሉበት ዘመን በ931 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ሰሜናዊው መንግሥት በስልምናሶር የተወረረው በ722 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- ደቡባዊው መንግሥት በናቡከደነፆር የተወረረው በ586 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- የደቡባዊው መንግሥት የስደት ዘመን 586-538 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- የሰሎሞን ቤተ መቅደስ እንደገና የተሠራው በ516 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡
- የኢየሩሳሌም ቅጥሮች የተገነቡት በ444 ዓ.ዓ ገደማ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፈ ዕዝራ አሥር ምዕራፎች አሉት፡፡ መጽሐፉ የእስራኤልን ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ እንደተመለሱ ቤተ መቅደስም እንደገና እንደተሠራ ይናገራል፡፡ ይህ መጽሐፍ ከ537 አንሥቶ ዕዝራ ራሱ ወደ ኢየሩሳሌም እስከመጣበት እስከ 458 ዓ.ዓ ድረስ ያለውን ታሪክ ይተርካል፡፡ የመጽሐፉ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ ነው፡፡ ዕዝራ በባቢሎን ምርኮኞች መካከል ያደገ ከአሮን ቤተሰብ የተወለደ ፈጣን ጸሐፊ ነበር፡፡ ዕዝ. ፯÷፮፡፡ **ዕዝራ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን** ሕግ እንዲጠብቁ ያስተምር ነበር፡፡ ዕዝ. ፯÷፲፡፡

**የመጽሐፈ ዕዝራ አከፋፈል፡-**

ምዕራፍ ፩፡- ቂሮስ የእስራኤል ሕዝብ ወደተስፋይቱ ሃገር እንዲመለስ መፍቀዱን ይናገራል፡፡

ምዕራፍ ፪፡- ከምርኮ የተመለሰው 42,360 ሕዝብ መመዝገቡን ይመሰክራል፡፡

ምዕራፍ ፫፡- የቤተ መቅደሱ እድሳት መጀመሩን ይዘግባል፡፡

ምዕራፍ ፬፡- ጠላቶች የቤተ መቅደሱን የእድሳት ሥራ መቃወማቸውን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም በቂሮስ ዘመን ቤተ መቅደሱ እንደተሠራና በአርጤክሰስ ዘመን ቅጥሩ እንደታጠረ ይነገራል፡፡

ምዕራፍ ፭-፮፡- በሐጌና በዘካርያስ ቀስቃሽነት ዘሩባቤል የቤተ መቅደሱን ሥራ መፈጸሙን ይገልጻል፡፡

ምዕራፍ ፯-፰፡- ዕዝራ ከወገኖቹ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መመለሱን ይናገራል፡፡

ምዕራፍ ፱-፲፡- ዕዝራ አይሁድ ያላመኑትን (አሕዛብን) እንዳያገቡ መከልከሉን ይመሠክራል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባቢሎን ሰይፍ አትርፎ እንደሚያወጣቸው ቃል ገብቶ ነበር፡፡ በቃሉ የታመነ አምላክ ስለሆነ በጊዜው ከምርኮ ነጻ አውጥቶ የተስፋይቱን ምድር እንዲረግጡ አድርጓል፡፡ ቃል የገባልንን ሳንወርሰው አንቀርም፡፡

## ተግባር

መምህር የእስራኤላውያንን ሕይወት በሚመለከት አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

በስደት ስለሚኖሩት ወገኖች በጋራ እንዲጸልዩ ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

☞ መጽሐፈ ዕዝራ ስለምን የሚተርክ (የሚያስረዳ) መጽሐፈ ነው?

☞ **መጽሐፉን የጻፈው ማነው?**

☞ **መጽሐፈ ዕዝራ ስንት ምዕራፎች አሉት?**

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ኢያሱ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ መጽሐፈ ኢያሱ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸው ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን፤ ድምፁንም እንሰማለን" ኢያሱ ፳፬÷፳፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ኢያሱ ፩-፳፬

## መግቢያ

መጽሐፈ ኢያሱ ከታሪክ መጻሕፍት የመጀመሪያው ሲሆን ሃያ ሦስት ምዕራፎች አሉት። መጽሐፉን የጻፈው ኢያሱ ነው። ሕዝበ እስራኤል በኢያሱ መሪነት ምድረ ርስት ከነዓንን እንደወረሱ የሚተርክ የታሪክ መጽሐፍ ነው።

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ኢያሱ ማለት "እግዚአብሔር አዳኝ ነው" ማለት ነው። ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝበ እስራኤልን የመራ መስፍን ነው። የሕዝቡን ጉዞ ፍጻሜ፣ የርስቱን አከፋፈል፣ የእግዚአብሔርን እርዳታና ምሕረት "መጽሐፈ ኢያሱ" ተብሎ በሚጠራው መጽሐፍ ጽፏል። መጽሐፈ ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ የናፈቋትን ርስት እንደወረሱ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን እንደፈጸመ ይተርካል።

### የመጽሐፈ ዕዝራ አከፋፈል፡-

ምዕራፍ ፩-፬፡- የእስራኤል ሕዝብ የጉዞ ዝግጅት እንዳደረጉና የዮርዳኖስን ወንዝ እንደተሻገሩ ይተርካል።

ምዕራፍ ፭-፯፡- የኢያሪኮ መያዝና የአካን ኃጢአት ተመዝግቦበታል።

ምዕራፍ ፰-፲፪፡- የእስራኤል መዝመትና የከንዓን ነገሥታት ሽንፈት ተገልጾበታል።

ምዕራፍ ፲፫-፳፪፡- እስራኤላውያን ርስትን እንደተከፋፈሉ ይናገራል።

ምዕራፍ ፳፫-፳፬፡- የኢያሱን ስንብትና ምክር ይገልጻል።

መጽሐፈ ኢያሱ ስለ አዲስ ምድር፣ አዲስ ሕይወት፣ አዲስ አምልኮና አዲስ ስጦታ የሚተርክ መጽሐፍ ነው። ሕዝቡ ወደ አባቶቻቸው የተስፋ ፍጻሜ ያደረሳቸውን፣ ብዙዎች የናፈቋትን፣ ሙሴ ሊያያት የተመኛትንና በናባው ተራራ ቆሞ የተሳለማትን አዲስ ምድር ያወረሳቸውን እግዚአብሔርን ሊሰሙና ሊያመልኩ መስማማታቸውን ይዘክራል።

መጽሐፈ ኢያሱ የኢያሱን ጥንካሬ፣ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወቱን፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሆኖ ሕዝቡ ምርጫውን እንዲያስተካክል መምከሩን ይመሰክራል።

www.zeorthodox.org

መጽሐፈ ኢያሱ ከአሪት ዘዳግም የቀጠለ ታሪክ ሲሆን የሕዝቡን ጉዞ እየተከተለ የሚተርክ ዜና ነው፡፡ እግዚአብሔር የጠላትን ግዛት አፍርሶ፣ የኢያሪኮን አጥር ሰብሮ፣ የበላይነቱን በመግለጥና የጠላትን ልብ በማቅለጥ የዓለም ብቸኛ ጌታ መሆኑን በሥራ እንዳሳየ መጽሐፈ ኢያሱ ይገልጻል፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ኢያሱ እግዚአብሔር ወዳሰበው ስፍራ ሕዝቡን በማድረስ የአብርሃምን ቃል ኪዳን መፈጸሙን ይገልጻል፡፡ በደስታ፣ በለውጥና በስኬት የተሞላ ሕይወት ያለው መስፍኑ ኢያሱ ሕዝቡን መርቶ ወደ ርስቱ እንዳደረሰ ይተርካል፡፡ እግዚአብሔርን የመረጠ ሕዝብ ፍጻሜው እንዲህ ያማረ ይሆናል፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ ‹‹አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤልና የርስቱ አከፋፈል›› በሚል ርእስ አጭር ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

☞ ኢያሱ ማለት ምን ማለት ነው?

☞ ኢያሱ ማነው? ሓላፊነቱ ምን ነበር? ምን ሠርቷል?

☞ ‹‹መጽሐፈ ኢያሱ›› ስለ ምን የተጻፈ መጽሐፍ ነው? ምን ያህል ምዕራፎች አሉት? የመጽሐፉን ይዘት በአጭሩ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ግዝረት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ግዝረት ምንነት ተገንዝበው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ያከብራሉ። መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው።" ዘፍ. ፲፯÷፲

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፲፯÷፩-፲፫፣ ዮሐ. ፫÷፩-፲ እና ሮሜ. ፬÷፲፩

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ግዝረት ማለት የዘር ብልትን ሸለፈት መቁረጥ ማለት ነው። ይህም ወንድን ብቻ ይመለከታል። ዘፍ. ፲፯÷፯-፲፬። **አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ።** እግዚአብሔርም ከወዳጁ ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ለማይታየው ቃል ኪዳኑ የሚታይ ምልክት ሰጠው። ይህም ግዝረት ነበር። "በእኔና በአንተ መካከል ከዘርህና በትውልዳቸው የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው። ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገርዛላችሁ። በእኔና በእናንተ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል። የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ" በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም አዘዘው። አብርሃምም ይስሐቅን በወለደ ጊዜ እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛው ቀን ገረዘው። ዘፍ. ፳፩÷፭። **ግዝረት በሙሴ ዘመን ለእስራኤል** ሕዝብ ምልክትና መለያ ነበር። ዘጸ. ፲፪÷፵፫-፵፭። ፩ሳሙ. ፲፯÷፴፮። **ፈሪሳውያን ሕዝባዊና** ሕጋዊ ምልክት አድርገው ቆጥረውት ነበር። ሐዋ. ፲፭÷፩-፭፤ **ገላ.** ፭÷፪-፯።

ግዝረት ሰው ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለማግኘቱ እግዚአብሔርንም አምላኩ ለማድረጉ ምልክት ነበር። ዘፍ. ፲፯÷፱-፲፩። **ግዝረትን የተቀበሉ ክፋትን** ከሕይወታቸው ማስወገድ ነበረባቸው። ዘጸ. ፲÷፲፮፣ **ኤር.** ፬÷፬። **ግዝረትን የፈጸሙ እግዚአብሔር** በእምነት መሠረት ስለተቀበላቸው የጽድቃቸው ማኅተም ነው። ሮሜ. ፬÷፲፩።

በሐዲስ ኪዳን የልብ መለወጥ እንጂ የሥጋ ሸለፈትን መቁረጥ አይጠቅምም። ፊል. ፫÷፫። **የሐዲስ ኪዳን የቃል ኪዳን ምልክት** የግዝረት ምትክ ጥምቀት ነው። ቆላ. ፪÷፲፩-፲፪። **በክርስቶስ አዲስ ሰው መሆን** የአዲስ ኪዳን የጥቅም መንገድ ነው። ገላ. ፭÷፮፤ ፮÷፲፭።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ላደረገው ቃል ኪዳን ምልክቱ ግዝረት ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ አምኖ በመጠመቅ ልጅነትን መቀበል ነው፡፡ ምልክቱ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር የተሳሰርንበት ጥምቀት ነው፡፡

## ጥያቄዎች

- ☞ ግዝረት ምንድነው?
- ☞ በብሉይ ኪዳን ግዝረት የተሰጠው ለምንድነው? ዓላማውን እና አፈጻጸሙን በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡
- ☞ ግዝረት የሚመለከተው ማንን ነበር?
- ☞ በሐዲስ ኪዳን ግዝረት ይጠቅማል? ለምን?
- ☞ በሐዲስ ኪዳን የቃል ኪዳን ምልክት ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# ጓደኞቻችንን እንዴት እንምረጥ?

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ባልንጀራ ምንነት እና አመራረጥ ያውቃሉ፤ ወደ ራእያቸው ስኬት በሚያደርጉት የሕይወት ጉዞ በድካማቸው የሚያግዛቸው መልካም ባልንጀራ እንዴት መምረጥና በመልካም ግንኙነት ከባልንጀራቸው ጋር መዝለቅ እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" ዘሌ. ፲፱÷፲፰

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፲÷፳፯-፴፯

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ባልንጀራ ማለት በዓላማ የሚመስለን፣ በድካማችን የሚያግዘን፣ በሐዘንና በደስታ አብሮነቱ የማይቀዘቅዝ፣ የምስጢራችን ተከፋዩና የመፍትሔያችን አጋር ማለት ነው፡፡ የባልንጀርነት ትርጉም በሃይማኖት የዕድሜ ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ እኩያችን የሆነ ሰውን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ባልንጀራዬ ማን ነው?" ብሎ ሕግ አዋቂው ለጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ፤ የአንተ እርዳታ የሚያስፈልገው ሁሉ ባልንጀራህ ነው፤ የሚል ይዘት አለው፡፡ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ የሆነው ሳምራዊው ነው፡፡ ሳምራዊው ለዚህ ቁስለኛ ምሕረት ያደረገለት ስለሚያውቀው አልነበረም፡፡ የእርሱ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ሲያይ ባልንጀራ ሆነው፡፡ ስለዚህ ባልንጀርነት በመተዋወቅና አብሮ በማደግ ብቻ አይወሰንም፡፡ ሉቃስ ፲÷፳፯-፴፯፡፡

ሙሴ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" የሚል ሕግ ከእግዚአብሔር ተቀብሏል፡፡ ዘሌ. ፲፱÷፲፰፡፡ **ባልንጀራህን በመውደድ ውስጥ** አባትና እናትህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር እና የባልንጀራህ የሆነውን ሁሉ አትመኝ የሚሉት ሕግጋት ተጠቃለዋል፡፡ ሉቃስ ፲÷፳፯-፳፰፡፡

www.zeorthodox.org

ባልንጀራችንን እንደራሳችን ስንወድ እንደራሳቸው የሚወዱን ባልንጀሮች እናገኛለን፡፡ ወዳጅ የማግኛው ብቸኛ መንገድ ወዳጅ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ የዘወትር ጥያቄያችን "መልካም ባልንጀራ ነኝ ወይ?" የሚል መሆን አለበት፡፡ ለባልንጀሮቻችን ጥሩ የምናደርግ ከሆነ ቢዘገይም መልካም የሆነውን ማጨዳችን አይቀርም፡፡ በትምህርት ውጤታማ፣ በኑሮ ፍሬያማ ሆናችሁ ወደ ራእያችሁ ስኬት መድረስ ከፈለጋችሁ በዓላማ የሚመስሏችሁ፣ በሐዘንና በደስታ ከአጠገባችሁ የማይለዩ፣ በጥረታችሁ በሥራችሁ ሁሉ የሚያበረቷችሁ ባልንጀሮች ያስፈልጓችኋል፡፡

የባልንጀርነት (የጓደኝነት) መስፈርቶች ምስጢር ጠባቂነት፣ ዓላማን መጋራት፣ የመከራ ቀን አብሮነት፣ ታማኝነት፣ ታጋሽነትና መልካምነት ናቸው፡፡ ባልንጀራ (ጓደኛ) እንዴት ልምረጥ? የሚለው ጥያቄያችን መልሱ በእጃችን ነው፡፡ ምን ዓይነት ጓደኛ እንፈልጋለን? ጓደኞችን ምን እንዲሆንልን እንፈልጋለን? እኔ ጥሩ ጓደኛ መሆን እችላለሁ? በማለት በመጀመሪያ ራሳችንን እንጠይቅ፡፡

ከዚያ ዓይናችንን ገልጠን ለእኛ በጎ ከሚያስቡት መካከል የተሻለውን እንምረጥ፡፡

ዳዊትና ዮናታን የሚዋደዱ ጓደኞች ነበሩ፡፡ እንደራሳቸው ይዋደዱ ነበር፡፡ ዮናታን የለበሰውን ካባ ለዳዊት ሸለመው፡፡ ዓላማውን ወዶ በድካሙ አገዘው፡፡ የአንዱ ነፍስ በአንዱ ነፍስ ታስራ ነበር፡፡ እነዚህ የልብ ወዳጆች በመልካምነት ተጉዘዋል፡፡ ዮናታን ዳዊት የአባቱን ንግሥና እንደሚወስድ እያወቀ ይንከባከበው ነበር፡፡ **፩ሳሙ. ፲፰፥፩-፬፤ ፳፥፲፪-፲፯፡፡ በጓደኞች መካከል ምቀኝነት** መኖር የለበትም፡፡ አንዱ የአንዱን ስኬት መውደድ አለበት፡፡ ዮናታን ሲሞት ዳዊት “በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበር” እያለ አለቀሰለት፡፡

## ማጠቃለያ

ባልንጀራ የዓላማ አጋር የክፉ ቀን ወዳጅ፣ ምስጢር ተከፋይና አካፋይ ነው፡፡ ባልንጀራ በሃይማኖት የእኛ እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ሁሉ ነው፡፡ መልካም ባልንጀራ ለማግኘት መልካም ሆኖ መገኘት ይጠበቅብናል፡፡ ሁለቱም ኪዳናት ባልንጀራችንን እንድንወድ ያዙናል፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን ባልንጀርነታቸውን እንዲመረምሩና መልካም እንዲሆኑ ይምከራቸው፡፡ በባልንጀሮች መካከል ለትምህርት የሚሆን ገጠመኝ ካላቸው እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

- ባልንጀራ ማለት ምን ማለት ነው? ምንድነው? አብራሩ፡፡
- በክርስትና ሃይማኖት የባልንጀራነት ትርጉም እንዴት ይገለጻል?
- በመጽሐፍ ቅዱስ የደጉ ሳምራዊ (ሉቃ.፲፥፳፭-፴፯) ታሪክን በአጭሩ መነሻ በማድረግ ስለ መልካም ጓደኛነት(ባልንጀራነት) ግለጹ፡፡
- ለመልካም ባልንጀራነት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ግለጹ፡፡
- መልካም ባልንጀራን እንዴት እንመርጣለን?

# የጓደኝነት ተጽዕኖዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ጓደኝነት ተጽዕኖዎች ዐውቀው በጓደኞቻቸው ተጽዕኖ መልካሙን አመላቸውን እንዳያጡና የኃጢአትን መንገድ እንዳይለማመዱ ይጠነቀቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋዋል” ፩ቆሮ. ፲፭÷፴፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፪ሳሙ. ፲፫÷፩-፲

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ባልንጀራ በመልካምም ሆነ በክፉ ተጽዕኖ ሊያደርግብን ይችላል፡፡ ሰው በሚሰማውና በሚያየው ነገር ተጽዕኖ ሥር ይወድቃል፡፡ የባልንጀርነት ጉዟችንም በማስተዋል ካልተጠበቀና በጥንቃቄም ካልተመራ በክፉ ባልንጀራ መልካም ያልሆነ ተጽዕኖ በጥፋት ጎዳና ተጉዘን ፍጻሜያችን ሲኦል ደጃፍ ላይ ይሆናል፡፡

1. **የባልንጀራ (የጓደኛ) አዎንታዊ (መልካም) ተጽዕኖዎች፡- ጥሩ ባልንጀራ መልካም እንድንሆንና መልካም እንድንሠራ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡ በትምህርታችን** ውጤታማ እንድንሆን ተግተን እንድናጠና፤ በቅድስና ሥርዓት እንድንኖር፤ በሃይማኖታችን እንድንጸና፤ በምግባራችን እንድንቀና፤ ከክፉ እንድንርቅና መልካም እንድንሠራ በምክርና በተግባር ተጽዕኖ የሚያደርጉብን መልካም ጓደኞች አሉ፡፡ የእነዚህ ጥሩ ጓደኞች በጎ የሆነ ተጽዕኖ ለጊዜው ከባድና አስጨናቂ ሆኖብን መልካም መስሎ ባይታየንም ፍጻሜው ወደ ስኬት ጫፍ መድረስ ስለሆነ በጸጋ ልንቀበለው ያስፈልጋል፡፡

ፊልጶስ ናትናኤልን ክርስቶስን እንዲያይ ጠርቶታል፡፡ ዮሐ. ፩÷፵፮፡፡ **ጴጥሮስና የዘብዴዎስ ልጆች በጓደኝነታቸው ሳይለያዩ ወደ ክርስቶስ** የመከር ሥራ መጥተዋል፡፡ ሉቃ. ፭÷፲፩ ጓደኛን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ማምጣት፤ ኅብረታችን የእግዚአብሔርን እውነት በእምነት እንዲቀበል፤ አብሮነታችን እግዚአብሔርን ለማክበር እንዲውል ማድረግ መልካም (አዎንታዊ) ተጽዕኖ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

2. **የባልንጀራ (የጓደኛ) አሉታዊ ተጽዕኖዎች፡- ክፉ ጓደኞቻችን ኃጢአትን እንድንለማመድ፣ የሥጋ ፍሬዎችን እንድናፈራ፣ በትምህርታችን ሰነፍ፣** በዓላማችን ልፍስፍስ፣ በሃይማኖታችን ተጠራጣሪና በምግባራችን ጠማማ እንድንሆን፤ በዋዛ ፈዛዛ ጊዜያችንን እንድናሳልፍና ዋልጌ እንድንሆን በመምራት፣ በማለማመድና በማበረታታት ክፉ ተጽዕኖ ሊያደርጉብን ይችላሉ፡፡ እነዚህን ባልንጀሮች በይሉኝታ ቸል ማለት ተገቢ አይደለም፤ ቶሎ ከክፉዎች ድንኳን መራቅና ፈቀቅ ማለት አለብን፡፡ የእነዚህን ባልንጀርነት በጸጋ ተቀብለን ፍለጋቸውን ከተከተልን ወደ ስኬት ጫፍ ሳይሆን ወደ ሞት ምዕራፍ መግባታችን አይቀርም፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋዋል።" በማለት የመከረን ለዚህ ነበር። ክፉ ባልንጀሮች መልካሙን መዓዛችንን ያጠፋሉ። ሳናስበው በክፋት መረባቸው ጠልፈው የማንጠቅም ዜጎች ያደርጉናል። የአምኖንና የኢዮናደብ ባልንጀርነት ምሳሌ መሆን ይችላል። አምኖን እኅቱን ትዕማርን በሰይጣናዊ ፍቅር ወደዳት። ኢዮናዳብ "ታምሜአለሁ ብለህ በአልጋህ ላይ ተኛ አባትህም ሊያይህ በመጣ ጊዜ፡- ትዕማር መጥታ ታስታመኝ በል። ከዚያ የራስህ ልታደርጋት ትችላለህ" ብሎ መከረው። አምኖን የጓደኛውን ክፉ ምክር ተቀብሎ ተገበረው። ትዕማርንም አስነወራት። ከቤት አባረራት። ቀድሞ ከወደዳት ውድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በለጠ። **፪ሳሙ. ፲፫÷፩-፲፱**።

ክፉ ስናስብ ገሥጾ መልካም ከሚያሳስበን እርኩሰት ርቀን በቅድስና እንድንኖር የሚያግዘን መልካም ባልንጀራ ያስፈልገናል። የአሚናዳብን ምክር የሚመክረን፣ ለርኩሰት የሚያመቻቸን ባልንጀራ ግን ጠላታችን ነው። ብዙዎች ባልንጀራቸውን ለማስደሰት ሲሉ እግዚአብሔርን አሳዝነዋል። በአጋጣሚ በክፋት አብሮን የተጓዘ ጓደኛ ካለ ተመካክረን መልካም ወደ መሆን መመለስ አለብን። ጥጦስና ዳክርስ የደም ጓደኞች ነበሩ። ብዙ ወንጀል አብረው ሠርተዋል። እኩል ተፈርዶባቸው በክርስቶስ ግራና ቀኝ ተሰቅለዋል። በመጨረሻው ሰዓት ግን በክርስቶስ መንገዳቸው ተለያየ። ጥጦስ አምኖ በሠራው ጥፋትና የበደል ሥራ ሁሉ ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በደሙ ሥልጣን ተጓዘ። የጥጦስን የመጨረሻ ውሳኔና መንገድ የክፉዎች ፍጻሜ እንዲሆን እንመኛለን።

## ማጠቃለያ

ጓደኞች በክፉም ሆነ በደግ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከባልንጀርነት ክፉ (አሉታዊ) ተጽዕኖ ራሳችንን እንጠብቅ። መልካም የሆነ የጓደኝነት ተጽዕኖዎችን ወደ መልካም መንገድ ስለሚመሩን በደስታ እንቀበል።

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ በጓደኝነት ተጽዕኖ መልካም የሆኑ፤ በክፉ ተጽዕኖ የተጎዱ ወጣቶች የታሪክ አጋጣሚዎቻቸውን (የሕይወት ልምዳቸውን) እንዲያካፍሉ ያድርጉ።

***ጥያቄዎች***

- ☞ ስለ ጥሩ ባልንጀራ (ጓደኛ) አዎንታዊ (መልካም) ተጽዕኖዎች ግለጹ። ምን ምን ናቸው?
- ☞ **የክፉ ባልንጀራ አሉታዊ ተጽዕኖዎችስ ምን ያስከትላሉ?**
- ☞ **ምን ዓይነት ባልንጀራ ያስፈልጋል? ለምን በምክንያት ግለጹ።**

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ባስልዮስ

**የትምህርቱ ዓላማ:-** ወጣቶች ስለ ቅዱስ ባስልዮስ ማንነትና ሥራዎች ያውቃሉ፤ የአባቶችን አሰረ-ፍኖት እንዲከተሉ የሚያስችላቸውን ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ።

**በቃል የሚጠና ጥቅስ:-** "ከዘላለም የተሰወረውን የምስጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠ" ኤፌ. ፫÷፱

**ተጨማሪ ምንባባት:-** ፪ጢሞ. ፬÷፪-፬

## መግቢያ

- ታላቁ ባስልዮስ ማን ነው?
- የቅዱስ ባስልዮስ ሥራች ምንድን ናቸው?
- ስለ ቅዱስ ባስልዮስ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ንገሩ።

## የሳምንቱ ትምህርት:-

ቅዱስ ባስልዮስ በቂሳርያ ከተማ በ329 ዓ.ም ከክርስቲያን ቤተሰብ ተወለደ። የቅዱስ ባስልዮስ ቤተሰቦች በሰማዕትነት፣ በምንኩስናና በመልካም ክርስቲያናዊ ሕይወት ይታወቃሉ። ግብጻውያን የባስልዮስን ቤተሰቦች "የክርስቲያን ወታደሮች" ይሏቸዋል።

ቅዱስ ባስልዮስ ከአትናቴዎስ ቀጥሎ የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት የእምነት ጠበቃ ነበር። ጎርጎርዮስ ዘኑሲስና ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ጓኞቹ ነበሩ። በምስጢረ ሥላሴ ትምህርታቸው ታዋቂ ስለነበሩ "ሦስቱ የቀጵርስ አባቶች (The Three Cappadocians)" ይባሉ ነበር። ቅዱስ ባስልዮስ በሶርያና በግብጽ ገዳማት በምንኩስና ሕይወት ተዘዋውሯል። ድሆችን ይንከባከብ ነበር።

ታላቁ ባስልዮስ በሥነ-ጽሑፍና ሳይንስ የትምህርት ዘርፎች ችሎታ ነበረው። በተለይ ለሕክምና ልዩ ፍቅር ነበረው። "የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት" በሚለው መጽሐፉ ይህ ፍቅሩ ተንፀባርቆበታል። በሥነ-ተፈጥሮ ጥናት ከአርስጣጣሊስ (አርስቶትል) የተሻለ መሆኑን በዚህ መጽሐፍ ባቀረባቸው ግኝቶች አስመስክሯል። ቅዱስ ባስልዮስ የምንኩስና ሕይወትን ሥርዓት ሠርቷል። እኅቱ የሴቶች ገዳም እመምኔት ነበረች። ምንኩስና ትልቅ ሕይወት እንደሆነ በሥራ በማሳየት መነኮሳት ጊዜያቸውን በጸሎት፣ በጾም፣ በልማት፣ በጥናትና ምርምር፣ በሥራ እንዲያሳልፉ ሥርዓት ሠርቷል።

በ370ዓ.ም የቂሳርያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የተሾመው። ቅዱስ ባስልዮስ ትልቅ የቅዳሴ ድርሳን ደርሷል፤ የቅዳሴ መጽሐፉም

www.zeorthodox.org

በቤተክርስቲያናችን ከአሥራ አራቱ ቅዳሴያት አንዱ ሆኖ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ የመዝሙረ ዳዊት አንድምታ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ የስድስቱ ቀናት ፍጥረታትና ሥርዓተ ምንኩስና የሚባሉ መጻሕፍት አሉት፡፡ ለአማኞች የመከረው ምክር፣ በትምህርቱ የሚጸልየው ጸሎትና ወርቃማ አባባሎቹ በተለያዩ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል፡፡

## የቅዱስ ባስልዮስ ጸሎት

*"የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪና የኃይላት ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ዳር ስለሌለው ምሕረትህ እናመሰግንሃለን፡፡ አንድያ ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ እኛ ላክህልን እርሱም ለመስቀል ሞት ታዘዘ በሞቱ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ሻረ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፈፈ፡፡ የክፋትን ኃይል ረገጠ እኛን ኃጢአተኞችን በምሕረቱ ተቀበለ፡፡ የምሕረት ጌታ ሆይ እናመሰግንሃለን፡፡ ሥጋችንን ለፈቃድህ እናስገዛለን፡፡ አንደበታችንን ስለስምህ ከክፉ እንጠብቃለን፡፡ ነፍሳችን ባንተ ፍቅር ታስራለች፡፡ የአንተም የዕውቀት ብርሃን ያበራላታል፡፡ ብርሃንህ ፍጹም ፍጻሜ የሌለው ነው፡፡ በምሕረትህ ስለመተላለፋችን ስርየትን ወደ ፍጹም መልካምነት ማደግን ስጠን፡፡ የዘላለም አባት ከተወዳጅ ልጅህ ከሕይወት ሰጪ መንፈስ ጋር ከዛሬ እስከዘለዓለም ተመስገን፡፡ አሜን"*

## ማጠቃለያ

*የመንግሥቱን ወራሾች፣ የመከሩን ሠራተኞች፣ የቃሉን ነጋሪዎች፣ የማዳኑን ምስክሮች፣ የምሥራቹን ነጋሪዎች፣ የተስፋውን ባለአደራዎችና የክርስትናን ባለራእዮች በእምነት ልንመስላቸው እና ከመልካም ሕይወታቸውም ልንማር ይገባል፡፡*

## ተግባር

*መምህር ተማሪዎችዎ የቅዱስ ባስልዮስ ትምህርቶች አጥንተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡*

### *ጥያቄዎች*

- ☞ ቅዱስ ባስልዮስ የት እና መቼ ተወለደ? ቤተሰቦቹ በምን ይታወቃሉ? ግብጻውያን የቅዱስ ባስልዮስን ቤተሰቦች ምን ብለው ይጠሯቸዋል?
- ☞ ቅዱስ ባስልዮስ ማን ነው? ምን አድርጎአል? ስለማንነቱ እና ሥራው ግለጹ፡፡
- ☞ ‹‹ሦስቱ የቆጵሮስ አባቶች›› በመባል የሚታወቁት እነማን ናቸው? እንዲህ የተባሉበት ምክንያት ምንድነው?
- ☞ ቅዱስ ባስልዮስ ሊቀጳጳስ ሆኖ የተሾመበት ሀገር ማን ይባላል? በስንት ዓመተ ምሕረት ተሾመ?
- ☞ ቅዱስ ባስልዮስ የጻፋቸው መጻሕፍት ምን ምን ናቸው?

www.zeorthodox.org

# ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መምህራን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የታላላቅ ቅዱሳን አባቶችን ማንነትና ታሪክ ያውቃሉ፤ መንገዳቸውንም ይከተላሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል" ኦ. ዘዳ. ፴፪÷፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፫÷፯፣ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ (በሉሌ መላኩ)

## መግቢያ

የክርስትና ትምህርት ተጠብቆ ለትውልድ እንዲደርስ የደከሙ የሃይማኖት ጠበቆች፤ መጽሐፍ ቅዱስን እየተረጎሙ ያስተማሩ መምህራን፤ የዓለምን ፍልስፍናና የመናፍቃንን ትምህርት በጽሑፍ የተቃወሙ ሊቃውንት በቤተ ክርስቲያናችን ይዘከራሉ፡፡ በነገረ ሃይማኖት ትምህርትና ጽሑፍ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ታላቁ ባስልዮስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲሱ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያና ቅዱስ እለእስክንድሮስ ዘእስክንድርያ ይታወቃሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (347-407 ዓ.ም)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳስ ሲሆን ታላቅ የቤተክርስቲያን መምህር ነው፡፡ በማራኪ ስብከቶቹ ምክንያት አፈወርቅ ተብሏል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአንፆኪያ ከሃብታም ቤተሰብ ተወለደ፡፡ ከአባቱ ሞት በኋላ የጥበብ መጻሕፍትን እንዲመረምር እናቱ ታበረታታው ነበር፡፡ በሃያ አምስት ዓመቱ የምንኩስና ሕይወት ጉዞውን የጀመረ ሲሆን ትምህርቱን የሚወዱ ብዙ አማኞች ይከተሉት ነበር፡፡ ለጽጽስና መዓርግ እንዲበቃ የብዙዎች ጥያቄ ነበር፡፡ ይህም ከሆነ በኋላ ዮሐንስ አፈወርቅ የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈቱና ለንስሐ የሚያበቁ ስብከቶችን፣ የመናፍቃንን ሴራ የሚያፈርሱ ጽሑፎችን፣ የግሪክን ፍልስፍና የሚያስረሱ ምርምሮችንና የሃይማኖት መሠረት የሚያሲይዙ ዶክትሪኖችን ጽፏል፡፡ ጥልቅ ዕውቀቱን የገለጸባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አንድምታዎቹ(ትርጓሜዎቹ) (Bible Commentaries) ዛሬ የብዙ መምህራን ማጣቀሻ ናቸው፡፡

### 2. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መምህር ነው፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት እየተባለ

www.zeorthodox.org

ይጠራል፡፡ ከወንጌላዊው ዮሐንስ ቀጥሎ ስለ መለኮት ጥልቅ ትምህርት ያስተማረ አባት ነው፡፡ ከሦስቱ የቀጰዶቅያ መምህራን (የነገረ ሥላሴ መምህራን) አንዱ ነበር፡፡ ስለ ምስጢረ ሥላሴ በሰፊው ጽፏል፡፡

### 3. ታላቁ ባስልዮስ (330-379 ዓ.ም)

ቅዱስ ባስልዮስ በቂሳርያ ከተማ ተወለደ፡፡ በቂሳርያና በአቴንስ የጥበብ ደጆችን አንኳኩቶአል፤ ተከፍተውለታልም፡፡ የቅዳሴ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ የምንኩስና ሕይወትን ያደራጀውና ሥርዓተ ምንኩስናን ያረቀቀው እርሱ ነው፡፡ የምንኩስና ሕይወት በጸሎት፣ በሥራ፣ በምርምርና ሌሎችን በመርዳት ታግዞ ለማኅበረሰቡ እንዲጠቅም አድርጓል፡፡ የሴቶች ሥርዓተ ገዳም በእኅቱ በማቅሪና እንዲመራ አድርጓል፡፡ ከሦስቱ የምስጢረ ሥላሴ መምህራን (Cappadocian Fathers) **አንዱ ነበር**፡፡

### 4. ቅዱስ ዲዮስቆሮስ

የእስክንድርያ ፓትርያርክ የአማኞች መምህር ነበር፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ዓምደ ሃይማኖት ተብሎ ይጠራል፡፡ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የሆነው በ444 ዓ.ም ሲሆን በ449 ዓ.ም አውጣኬን ለማውገዝ ጉባኤ ጠርቷል፡፡ በ451 ዓ.ም የተደረገውን የመለካውያን ጉባኤ ተቃውሟል፡፡ በዚህም ምክንያት ተደብድቧል፡፡ በድብደባው የተነጨ ጺሙንና የወለቁ ጥርሶቹን አሻራ በማድረግ የግብጽ ምእመናን እንዲጽናኑ መልእክት ልኳል፡፡ የክርስቲያን (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) ጠበቃ ነው፡፡

### 5. ቅዱስ አትናቴዎስ

የእስክንድርያ ፓትርያርክ ነው፡፡ የኢትዮጵያን የመጀመሪያ ጳጳስ (ብፁዕ አቡነ ሰላማ ፍሬምናጦስን) የሾመው እርሱ ነው፡፡ አትናቴዎስ አርዮስን ተከራክሮ የረታ፤ የኒቂያውን ጉባኤ ያኮራ፤ ጸሎተ ሃይማኖትን ያረቀቀ፤ ስለ ሃይማኖቱ ብዙ ስደትና መከራን የተቀበለ፤ መሠረታዊ የሃይማኖት ዶክትሪኖችን የጻፈ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መምህር ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

በክርስትና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መምህራን አሉ፡፡ ትምህርታቸው ዘመን ሳይገድበው ለእኛም ደርሷል፡፡ በዘመናቸው የእግዚአብሔርን ሐሳብ አገልግለው የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ አሳክተው ዐርፈዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ "ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ መምህራን" በሚል ርእስ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ማን ነው? የት፣ መቼ ተወለደ? ሥራዎቹን በአጭሩ ግለጹ።
- ☞ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኖ ያገለገለው መቼ ነው? በቤተ ክርስቲያናችን ማን ተብሎ ይጠራል? ከሠራው ሥራ ዋናውን ግለጹ፤ ምን ደረሰበት (የደረሰበት ችግር ምንድነው?)
- ☞ የኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ (ከሣቴ ብርሃን) ሾሞ የላከው አባት ማን ይባላል?
- ☞ የአርዮስን የኑፋቄ ትምህርት ተከራክሮ የረታ፣ በኒቂያ ጉባኤ ታላቅ ሥራ የሠራ፣ ጸሎተ ሃይማኖትን ያረቀቀው የቤተ ክርስቲያን አባት ማን ይባላል?
- ☞ ከወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ቀጥሎ ስለ መለኮት ጥልቅ ትምህርት በማስተማሩ ‹‹ነባቤ መለኮት›› እየተባለ የሚጠራው አባት ማን ነው?
- ☞ ታላቁ ባስልዮስ የተወለደው የት ነው? የጻፈው መጽሐፍ ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (አንድ አምላክ) (፩)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች እግዚአብሔርን በማወቅ በእምነት ይጎለምሳሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡" ዘዳ. ፮÷፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍ. ፩÷፳፮፤፫÷፳፪፣ ኢሳ. ፮÷፫፣ ማቴ. ፳፰÷፲፱፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ትምህርተ ሃይማኖት (በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ)፣ ሃይማኖተ አበው

## መግቢያ

ሃይማኖታችን በጸና ዐለት በማይናወጥ መሠረት ላይ የቆመ ነው፡፡ በፍጹም እምነት ልንመላለስ ይገባል፡፡ በእግዚአብሔር መገለጥ የተገለጡ ዘላለማዊ እውነቶችን አባቶቻችን በዓለም አቀፋዊ ጉባኤያት ደንግገውልናል፡፡ ይህ ድንጋጌ መሠረተ እምነት ወይም ጸሎተ ሃይማኖት ይባላል፡፡ ጸሎተ ሃይማኖት አሥራ ሁለት አንቀጾች አሉት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሰባቱ አንቀጾች በጉባኤ ኒቂያ (325 ዓ.ም) የመጨረሻዎቹ አምስቱ አንቀጾች ደግሞ በጉባኤ ቁስጥንጥኒያ (381 ዓ.ም) የተደነገጉ ናቸው፡፡ ጸሎተ ሃይማኖት የቆምንበት የጸና መሠረት ሲሆን፣ የክርስቲያኖች የጋራ መግለጫ፤ ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ጸሎተ ሃይማኖት አምስቱ አዕማደ ምስጢራትን ቀምሮ የያዘ የአቋም መግለጫ የአምላካችን ማንነት መግለጫ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. ሥላሴ (አንድ አምላክ በሦስት ፍጹማን አካላት)

ሥላሴ ማለት ሦስት፤ ሦስትነት ማለት ነው፡፡ ትምህርተ ሥላሴ የክርስትና መሠረት ሲሆን፡፡ ለአማንያን የመጀመሪያ ትምህርት ነው፡፡ በሌሎች አብያተ እምነቶች የሥላሴ ፅንሰ ሐሳብ የለም፡፡

www.zeorthodox.org

ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት፤ ሦስት ሲሆኑ አንድ፤ በመለኮት፣ በሥልጣን፣ በሕልውና አንድ ሲሆኑ በስም፣ በአካልና በግብር ሦስት ናቸው፡፡ የሥላሴ የስም ሦስትነት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፤ የአካል ሦስትነት ለአብ የራሱ የሆነ ፍጹም መልክ አለው፤ ለወልድም የራሱ የሆነ ፍጹም መልክ አለው፤ ለመንፈስ ቅዱስም እንዲሁ የራሱ የሆነ ፍጹም መልክ አለው፡፡ የሥላሴ የግብር ሦስትነት አብ ይወልዳል፤ ያሰርፃል፡፡ ወልድ ይወለዳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይሰርፃል፡፡ ወልድ ይወለዳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይሰርጻል፡፡ መስረጽ ማለት መውጣት መገኘት ማለት ነው፡፡ ሦስቱ ግብራት ከአንዱ አካል ወደሌላው አካል አይተላለፉም፡፡ የሦስትነት ስማቸውም አይወራረስም፡፡

እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው፡፡ "እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡" ተብሎ እንደተጻፈ፡፡ አንዱ አምላክ እግዚአብሔር ሦስት ፍጹማን አካላት አሉት፡፡ እነዚህ ፍጹማን አካላት ከላይ እንዳየነው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ፡፡

የሥላሴ አንድነት አይበታተንም፤ አይከፋፈልም፡፡ ሦስትነታቸውም አይጠጋጋም፤ አይጠቃለልም፡፡ አንድ አምላክ በሦስት ፍጹማን አካላት ማለታችን ለዚህ ነው፡፡ በጸሎታችንም ስንመሠክር "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ (እግዚአብሔር)" ብለን ነው፡፡ በመዓርግ አይበላለጡምና፤ በዘመን አይቀዳደሙምና፡፡

ሰው በነፍሱ ልብ፣ ቃልና እስትንፋስ አለው፡፡ ሰው በፈጣሪው አርአያና አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ያብራራል፡፡ ሰው አንድ ሆኖ ሳለ ሐሳብ አለው፡፡ ሐሳቡን የሚገልጽበት ቃል አለው፡፡ ቃሉን የሚያስተላልፍበት የሕይወት እስትንፋስ አለው፡፡ በልቡ አብ፣ በቃሉ ወልድ፣ በእስትንፋሱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ፡፡ በሥላሴ መንግሥት ያለው አንድ ልብ ፣ አንድ ቃል፣ አንድ ሕይወት ነው፡፡ በአብ ልብነት ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያስባሉ፤ በወልድ ቃልነት አብና መንፈስ ቅዱስ ይናገራሉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት አብና ወልድ ሕያዋን ይሆናሉ፡፡

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር አንድ አምላክነት በሰፊው ተሰብኳል፡፡ ሦስት ፍጹማን አካላት እንዳሉትም ጥቂት ጠቋሚ መልእክቶች ተንፀባርቀዋል፡፡ ዘፍ. ፩÷፳፯ ፤ ፫÷፳፪ ፤ ፲፩÷፭-፯ ፣ ኢሳ. ፯÷፫፡፡

በሐዲስ ኪዳን የሥላሴ ሦስትነት በሚገባ ተብራርቷል፡፡ አንዱ አምላካችን እግዚአብሔር ሦስት ፍጹማን አካላት እንዳሉት ተገልጦአል፡፡ በጌታ ጥምቀት አብ በደመና ሲናገር ፤ወልድ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ሲገለጥ፤ ምስጢረ ሥላሴ ለዓለም ተገልጧል፡፡ ማቴ. ፫÷፲፯፡፡ **ጌታ ሐዋርያቱን ሲልክ "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም** እያጠመቃችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፡፡" የሚል ትእዛዝ መስጠቱ ሦስትነቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡

## 2. የእግዚአብሔር ስሞች

ስሙ የባሕርይው መገለጫ እንጂ መለያ አይደለም፡፡ ስሙንም ሰው አላወጣለትም፤ ራሱ ነው ለወዳጆቹ የገለጠው፡፡ የእግዚአብሔር ስሞች የባሕርይው መገለጫ፤ የጥያቄዎቻችንም መፍቻ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በዕብራውያን ቋንቋ ኤል፣ ኤሎሂም፣ ኤልሻዳይ፣ ያሕዌና አዶናይ ተብሎ እየተጠራ ተመልኳል፡፡

**ኤል፡-** ማለት ኃያል (አምላክ) ማለት ነው፡፡ መዝ. ፹፩÷፱

www.zeorthodox.org

**ኤሎሂም፡-** ማለት እግዚአብሔር አምላክ ነው፡፡ ዘጸ. ፲፰÷፲፩፡፡

**ኤልሻዳይ፡-** ማለት ሁሉን ቻይ አምላክ ማለት ነው፡፡ ዘፍ. ፲፯÷፩፡፡

**ያሕዌ፡-** ማለት የነበረ ያለና የሚኖር አምላክ ማለት ነው፡፡ ዘጸ. ፫÷፲፫፡፡

**አዶናይ፡-** ማለት ጌታ ማለት ነው፡፡ መዝ. ፴፯÷፫፡፡

**ማስታወሻ፡-** እነዚህ ስሞች ሁሉ የሥላሴ የአንድነት ስሞች ናቸው፡፡ አብም ወልድም መንፈስቅዱስም ይጠሩባቸዋል፡፡

## 3. የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫ

- እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ ዮሐ. ፬÷፳፬፡፡
- እግዚአብሔር ብርሃን ነው፡፡ ፩ዮሐ. ፩÷፭፡፡
- እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ ፩ዮሐ. ፬÷፰፡፡
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው፡፡ ዳን. ፬÷፴፭፡፡
- እግዚአብሔር አይለወጥም፡፡ ሚል. ፫÷፮፡፡
- እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ ኢሳ. ፵፮÷፲፡፡
- እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው፡፡ ዳን. ፪÷፳፡፡
- እግዚአብሔር ቸር ነው፡፡ መዝ. ፻፵፭÷፰፡፡
- እግዚአብሔር መሐሪ ነው፡፡ ኤፌ. ፪÷፬-፭፡፡
- እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፡፡ ዮናስ ፬÷፪፣ ፪ጴጥ. ፫÷፲፡፡
- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡ ኢሳ. ፮÷፬፡፡
- እግዚአብሔር ጻድቅ (እውነተኛ) ነው፡፡ ሮሜ. ፫÷፳፮፡፡
- እግዚአብሔር ታማኝ ነው፡፡ ዮሐ. ፲፬÷፮፡፡
- እግዚአብሔር አይወሰንም፡፡ መዝ. ፻፴፰÷፯-፲፡፡

## 4. የእግዚአብሔር ሥራዎች

- እግዚአብሔር ፈጣሪ ኩሉ ዓለማት (የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ) ነው፡፡ የሚታየውንና የማይታየውን የፈጠረ አምላክ ነው፡፡ ኢሳ. ፵፬÷፯፡፡
- እግዚአብሔር መጋቤ ኩሉ ዓለማት (የፍጥረታት ሁሉ መጋቢ) ነው፡፡ መዝ. ፻፵፬÷፲፭-፲፯፡፡
- እግዚአብሔር ዐቃቤ ኩሉ ዓለማት (የፍጥረታት ሁሉ ጠባቂ/እረኛ) ነው፡፡ መዝ. ፻፳÷፫-፰፡፡

## ማጠቃለያ www.zeorthodox.org

"ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን፡፡" ጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ፩፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ "የእግዚአብሔር አብ ሥራዎች" በሚል ርእስ አብን ብቻ የሚመለከቱ ሥራዎችን ከመጻሕፍት መርምረው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

*ጥያቄዎች*

☞ ‹‹ጸሎተ ሃይማኖት›› ስንት አንቀጾች አሉት? የመጀመሪያዎቹ አንቀጾች ስንት ናቸው? የትና መቼ ተደነገጉ? የመጨረሻዎቹ ወይም ከመጀመሪያዎቹ ቀጥሎ የተደነገጉት አንቀጾች ስንት ናቸው? የት እና መቼ ተደነገጉ?

☞ ‹‹ጸሎተ ሃይማኖት›› ምንድን ነው?

☞ ሥላሴ ማለት ምን ማለት ነው? አንድነት እና ሦስትነታቸውን በተማራችሁት መሠረት አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

☞ በሐዲስ ኪዳን የሥላሴ ሦስትነት የተገለጠበት መቼ ነው? አብራሩ፡፡

☞የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫ ከሆኑት ቢያንስ አምስቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በመጥቀስ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (የክርስቶስ አምላክነት) (፪)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡" ሉቃ. ፩÷፴፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኢሳ. ፱÷፮፣ ዮሐ. ፩÷፩–፫፣ ቆላ. ፩÷፲፭-፲፯ እና ራእ. ፩÷፲፯-፲፱

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበረ፤ ያለ፤ ዘመንን አሳልፎ የሚኖር የዘላለም አምላክ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ እግዚአብሔር ወልድ (ወልደ እግዚአብሔር) ይባላል፡፡ የጸሎተ ሃይማኖት የመጀመሪያው አንቀጽ ስለ እግዚአብሔር አብ የሚናገር ሲሆን ከሁለተኛው ጀምሮ እስከ ሰባተኛው አንቀጽ ድረስ ስለእግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ይመሠክራል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. የወልድ የሥጋዌ ስሞች

ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ሲገለጥ የተጠራባቸው የሥጋዌ ስሞች አሉት፡፡ እነሱም፡-

**1.1. ኢየሱስ፡-** ኢየሱስ ማለት አዳኝ መድኃኒት ማለት ነው፡፡ ይህ ስሙ ቅድመ ዓለም በአብ ኅሊና ታስቦ ይኖር እንደነበር መልክአ ኢየሱስ ይመሰክራል፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ሲያበሥራት "ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ" ብሏታል፡፡ ሉቃ. ፩÷፴፩፡፡ **እመቤታችንና ዮሴፍ** ጌታ በስምንት ቀኑ ወደ ቤተ ግዝረት ሲገባ በመልአኩ እንደተነገራቸው ኢየሱስ ብለው ጠሩት፡፡ ሉቃ. ፪÷፳፩፡፡ **አምልኮ፣ ጸሎት፣ ፈውስና አገልግሎት** የሚከናወነው በዚህ በስሙ ነው፡፡

**1.2. ክርስቶስ፡-** ክርስቶስ ማለት የተቀባ መሲህ ማለት ነው፡፡ አይሁድ የጠበቁት መሲህ ነቢያትና ጻድቃን ሊያዩት የናፈቁት ጌታ የነፍስ ነጻ አውጪ ስለሆነ ክርስቶስ አሉት፡፡ ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ከእግዚአብሔር ተወልዷል፡፡ ፩ዮሐ. ፭÷፩፡፡

**1.3. አማኑኤል፡-** አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው፡፡ ኢሳ. ፯÷፲፬፡፡ **የተዋረደውን አዳምን ለማክበር** ጌታ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጥቷል፡፡ እርሱ አምላካችን የእኛን ሥጋና ደም ስለተካፈለ ከእኛ ጋራ ሆነ

www.zeorthodox.org

"አማኑኤል" ተብሏል፡፡ ማቴ. ፩÷፳፫፡፡

**1.4. መድኃኔአለም፡-** መድኃኔዓለም ማለት የዓለም መድኃኒት ማለት ነው፡፡ አብ ልጁን የላከው የዓለም መድኃኒት እንዲሆን ነው፡፡ ፩ዮሐ. ፬÷፲፬፡፡ **ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን** አዳነ፡፡ እኛም እንደ ሰማርያ ሰዎች መድኃኔዓለም አልነው፤ የሁላችንም መድኃኒት ነውና፡፡ ዮሐ. ፬÷፵፪፡፡

**1.5. የሰው ልጅ፡-** የሰውን ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ ሰው ስለሆነ፡፡ ዮሐ. ፮÷፶፫፡፡

**1.6. የእግዚአብሔር ልጅ፡-** የአብ የባሕርይ ልጅ ስለሆነ አባቱን በመልክ ስለሚመስልና በክብር ስለሚተካከል በዚህ ስም ተጠራ፡፡ ፩ዮሐ. ፭÷፭፡፡

## 2. ኢየሱስ በጸሎተ ሃይማኖት

ጸሎተ ሃይማኖት ከሁለተኛው እስከ ሰባተኛው አንቀጽ ስለ እርሱ ይናገራል፡፡

2.1. ዓለም ሳይፈጠር ከአባቱ ከአብ ጋር የነበረ አልፋ ዘመንን አሳልፎ የሚኖር ኦሜጋ ነው፡፡ "ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ" ዮሐ. ፩÷፩፣ **ራእ.** ፩÷፰፡፡

2.2. የአብ አንድያ ልጅ ነው፡፡ "*የአብ አንድ ልጁ በሚሆን*" ለወልድ ሁለት ልደታት አሉት፡፡ የመጀመሪያው ልደት ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት የተወለደው ልደት ሲሆን ሁለተኛው ልደት ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ያለ አባት የተወለደው ልደት ነው፡፡ ስለዚህ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ይባላል፡፡ ዮሐ. ፫÷፲፮፣ **ሉቃስ** ፪÷፯፡፡

2.3. አንድ ጌታ ነው፡፡ ኤፌ. 4÷4፡፡ "*በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን*"፡፡

2.4. ከእውነተኛ ብርሃን የተገኘ እውነተኛ ብርሃን ነው፡፡ "*ከብርሃን የተገኘ ብርሃን*" ዮሐ. ፰÷፲፪፡፡

2.5. ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ "*ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ*" ሮሜ. ፱÷፭

2.6. የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ ነው፡፡ "*የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ*" ቆላ. ፩÷፲፯፡፡

2.7. በመለኮቱ ከአባቱ ጋር አንድ ነው፡፡ "*በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል*" ዮሐ. ፩÷፩፡፡ **ኢየሱስ ከአባቱ ጋር አንድ ባሕርይ** ነው፡፡

2.8. ሁሉ በእርሱ የሆነለት ሁሉ የተገዙለት ጌታ ነው፡፡ ዮሐ. ፩÷፩-፫፣ **ዕብ.** ፪÷፰-፱፡፡ "*ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነው ያለ እርሱ የሆነ ምንም ምን የለም፡፡ በሰማይም ያለ በምድርም ያለ በእርሱ ሆነ*"

www.zeorthodox.org

2.9. ስለ መዳናችን የወረደ ከድንግል ማርያም የተወለደ ፍጹም ሰው ነው፡፡ "*ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማይ ወረደ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ፡፡*" ሉቃ. ፪÷፯፡፡ **ዕብ.** ፪÷፲-፲፰፡ **ሐዋ.** ፫÷፳፪-፳፮፡፡

2.10. የመዳናችንን ራስ በመከራ የፈጸመ የሕማም ሰው ነው፡፡ "*ሰው ሁኖ በጴንጠናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ፣ ታመመ፣ሞተ፣ ተቀበረ፡፡*" ኢሳ. ፶፫÷፫-፲፪፡፡ **ማቴ.** ፳፯፡፡

2.11. የትንሣኤያችን በኩር ነው፡፡ "*በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፡፡*" **፩ቆሮ.**

፲፰÷፫-፳፬፡፡

2.12. በክብር ያረገ በግርማው ቀኝ የተቀመጠና ደግሞ በጌትነቱ የሚመጣ የዘላለም አምላክ ነው፡፡ *"በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ዳግማኛም ሕያዋንንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፡፡ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፡፡"* ሐዋ. ፩÷፲፩፡፡ ዕብ. ፩÷፫-፬፡፡ ራእ. ፩÷፯፡፡

***ማስታወሻ፡-*** በትምህርተ ጥቅስ ተከልሎ የተሰመረበት ቃል ከጸሎተ ሃይማኖት በቀጥታ የተወሰደ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ልጅ ነው፡፡ በባሕርዩ ከአባቱ ጋር አንድ ነው፡፡ በመልክ አባቱን የሚመስል፤ የአባቱን ፈቃድ ለዓለም ያስተማረ አንድያ ልጁ ነው፡፡ የመዳናችንን ራስ በመከራ ፈጽሞ፤ ሞትን በሞት ሽሮ፤ የሚቃወመንን የዕዳ ጽሕፈት በመስቀሉ ጠርቆ ከመንገዳችን አስወግዶ አድኖናል፡፡ የዘላለም ሕይወት ያለው እርሱን በማመን ነው፡፡ እርሱ ቤዛችን ነው እናምነዋለን፤ አርአያችን ነው ፍለጋውን እንከተላለን፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን፤ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነትና ፍጹም አምላክነት በመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተገልጧል?›› በሚል ርእስ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ እና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጉአቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ሲገለጥ የተጠራባቸው የሥጋዌ ስሞች ማን ማን ናቸው?
- ☞ ኢየሱስ ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት መነሻው ምንድነው?
- ☞ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ተባለ?
- ☞ አማኑኤል ማለት ምን ማለት ነው? የተባለበት ምክንያት ምንድነው? አብራሩ፡፡
- ☞ ‹‹ለወልድ ሁለት ልደታት አሉት›› እንዴት? በተማራችሁት መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አብራሩ፡፡
- ☞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤያችን በኩር ነው፤ የሚለውን በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ መንፈስ ቅዱስ)(፫)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ነገረ መንፈስ ቅዱስን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡" ፪ጴጥ. ፩÷፳፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፮÷፯-፲፣ ሐዋ. ፪÷፩–፳፫፣ ሮሜ. ፰÷፱–፲፯ እና ኤፌ. ፬÷፳፱-፴፪

## መግቢያ

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ሲሆን፡፡ ከአብ የሠረጸ (የወጣ) አካል ያለው መንፈስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሰጭና ምስጢር ገላጭ ነው፡፡ ኃጥአንን ለንስሐ ይቀሰቅሳል፤ ቅዱሳንን ምን እንዲናገሩ ያስተምራል፡፡ የጸሎተ ሃይማኖት ስምንተኛ **አንቀጽ ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል፡፡ መቅዶንዮስ የተባለ መናፍቅ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት** ሲክድ እርሱን ለማውገዝ በተጠራው የቁስጥንጥኒያ ጉባኤ (381 ዓ.ም) የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

"ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ የሠረጸ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፡፡ እንሰግድለት እናመሰግነው ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር፤ እርሱ በነቢያት የተናገረ ነው፡፡" ጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ 2፡፡

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረጸ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የሚሰገድለት የሚመሰገን አምልኮ የሚቀበል ቅድመ ዓለም የነበረ ያለና የሚኖር አካል ያለው መንፈስ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ ቅርጽ አልባዋን ምድር በጥበቡ ያስጌጠ ጌታ ነው፡፡ ውሆችን ለሰው ጥቅም የቀደሰ፡ ለሰው የሕይወት እስትንፋስ የሰጠ፡ ሕይወት ሰጭ ማህያዊ ጌታ ነው፡፡ ዘፍ. ፩÷፫፡፡ **መንፈስ ቅዱስ** መሳፍንቱን በምስፍና ነገሥታቱን በንግሥና ነቢያቱን በሃብት ትንቢት የቀባ አምላክ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሰጭና ምስጢር ገላጭ ነው፡፡ ነቢያት ስላልነበሩበትና ስለማይኖሩበት ዘመን የጻፉት (የተናገሩት) በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ነው፡፡ **፪ጴጥ. ፩÷፳፩**፡፡

መንፈስ ቅዱስ ልብን ያውቃል፡፡ ስለዚህ ማታለል አይቻልም፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ሰዎች በሰው ልብ ያለውን ያውቃሉ፡፡ ሐዋ. **፭÷፫-፭፣ ፩ቆሮ. ፪÷፲-፲፬**፡፡ **የቅዱሳን** ሐዋርያት አገልግሎት የተሳካው በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ፣ ፈውስ፣ ሕይወት፣ አገልግሎትና አምልኮት የለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በድካማችን ሁሉ ያግዘናል፤ እንዴት መኖርና መጸለይ እንዳለብን ያስተምረናል፡፡ ሮሜ. **፰÷፳፮**፡፡ **የቤተ ክርስቲያን** ጉዞ የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመንፈስ ቅዱስ መምጣት ሲናገር "አብ በስሜ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ ሁሉን ያስተምራችኋል" በማለት የመንፈስ ቅዱስን መምህርነት አስረድቷል፡፡ ዮሐ. ፲፬÷፳፮፡፡* ***እንደቃሉም መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ስለ ኃጢአት፣ ስለፍርድና ጽድቅ ዓለምን ወቅሷል፡፡ ዮሐ. ፲፮÷፯፡፡***

*መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ ሕይወት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በውኃ፣ በእሳት፣ በርግብና በነፋስ አምሳል ለዓለም ተገልጧል፡፡ በበዓለ ሃምሳ ለደቀ መዛሙርቱ ቋንቋ ገልጧል፡፡ ሐዋ. ፪÷፩-፲፡፡* ***መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ባመኑ ሰዎች ያድራል፡፡ የመንፈስ ፍሬዎችንም ለክብሩ ያፈራላቸዋል፡፡*** *ሮሜ. ፰÷፱-፲፯፡፡* ***የመንፈስ*** *ቅዱስ ዓለም የሰው ሰውነት ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ እንደሆንን እርሱም የእኛ መኖሪያ እንደሆነ ልናውቅ ይገባል፡፡ ፩ቆሮ. ፮÷፳፡፡*

## ማጠቃለያ

*መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ይሰጣል፤ ምስጢር ይገልጣል፡፡ የነቢያት ትንቢት የሐዋርያትም ስብከት በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ ሕይወት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነው፡፡ ምሪቱን እንከተል፡፡*

## ተግባር

*መምህር ተማሪዎችዎን፤ ‹‹እኛ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ከሆንን እንዴት እናከብረው?›› በሚል ርእስ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡*

***ጥያቄዎች***

- ☞ *መንፈስ ቅዱስ ማነው? በተማራችሁት መሠረት አብራርታችሁ ግለጹ፡፡*
- ☞ *ስለ መንፈስ ቅዱስ ጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ሁለት ምን ይላል?*
- ☞ *መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን በበዓለ ሃምሳ ለሐዋርያት ያደረገላቸው ምንድነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ግለጹ፡፡*
- ☞ *ስለ መንፈስ ቅዱስ ተግባር በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡*

www.zeorthodox.org

# የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ ቤተ ክርስቲያን) (፬)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ነገረ ቤተ ክርስቲያንን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው፡፡ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሞላ የሚሞላ የእራሱ ሙላት ናት" ኤፌ. ፩÷፳፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፮÷፲፰፣ ፩ቆሮ. ፫÷፲፮፣ ሐዋ. ፳÷ ፳፰ እና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ (በአባ ጎርጎርዮስ)

## መግቢያ

- ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
- ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?
- ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?
- ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ትሄዳላችሁ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል "አቅሌሲያ" ከሚለው የፅርዕ ቋንቋ የተገኘ ቃል ሲሆን ‹‹የምርጦች ጉባኤ›› ማለት ነው፡፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የቤተ ክርስቲያንን ዕድሜ ከዓለመ መላእክት ጀምሮ እንቆጥራለን፡፡ የጸኑት መላእክት አንድነትና ከአቤል ጀምሮ የተነሡ ደጋግ ሰዎች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ይባላልና፡፡

www.zeorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን ሲባል ማኅበረ ምእመናንን፣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና እያንዳንዱን አማኝ ያጠቃልላል፡፡ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደምም ከነገድና ከቋንቋ ከሕዝብና ከወገን የተዋጁ ምርጥ ዜጎችን፣ አምልኮ የሚፈጽሙበትን ቅዱስ ስፍራና እያንዳንዱን ምእመን ይመለከታል፡፡ የጸሎተ ሃይማኖት አምስተኛ አንቀጽ ነገረ ቤተ ክርስቲያንን ይመለከታል፡፡

## ቤተ ክርስቲያንን በጸሎተ ሃይማኖት ስንገልጸው፡-

1. **አንዲት ናት፡-** ሁሉም አማኞች አንድ ልብና መንፈስ ሆነው በአንድነት መኳዛቸውን በስፍራና በጊዜ ቢረቁም በመንፈስ ኅብረት መኖራቸውን ያሳያል፡፡ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንም በአፈር ወይም በወርቅ ብትሠራ በዱር (በገጠር) ወይም በከተማ ብትኖር አንዲት መሆኗን ይገልጻል፡፡

2. **ዓለምአቀፋዊት ናት፡፡** ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጌታ አምነው በአንዲት ጥምቀት ልጅነት ያገኙ ምእመናን ባሉበት ሁሉ አለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዘር፣ ቀለምና ቋንቋ አይገድቧትም፤ ዓለማቀፋዊት ናት፡፡

3. **ሐዋርያዊት ናት፡፡** ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ የተመሠረተች ለእነርሱ ትምህርት አንደበት ስለሆነች ሐዋርያዊት ትባላለች፡፡ አማኞችም በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፀው ክርስቶስን የማዕዘን ራስ (የሕይወታቸው ራስ) ስላደረጉ በሐዋርያት ትምህርት ስለሚመሩ ሐዋርያውያን ይባላሉ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እያጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያደርጋል፡፡" በማለት አስተምሯል፡፡ ኤፌ. ፪÷፲፱-፳፪፡፡

4. **ቅድስት ናት፡፡** ቤተ ክርስቲያን በውኃ መታጠብና በቃሉ ስለቀደሳት ቅድስት ናት፡፡ ኤፌ. ፭÷፳፮፡፡ ክርስቶስ ራስ የሆነላት ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፤ ያለ ክርስቶስ ቅድስና የለምና፡፡ ኤፌ. ፩÷፳፫፡፡ ዮሐ. ፲፭÷፭፡፡

ስለዚህ ጸሎተ ሃይማኖታችን "ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰብዋት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን" በማለት ድንጋጌውን ገለጠልን፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን የምርጦች ጉባኤ፤ የነጻ ዜጎች ምድር፤ የቅዱሳን ሰፈር ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት፣ አንዲት፣ ሐዋርያዊትና ዓለምአቀፋዊት ናት፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን፤ በቅድስና በመኖር ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት እንዲጠብቁ፣ ከአማንያን ጋር ኅብረት እንዲያደርጉና ዘወትር በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ወንጌልን እንዲማሩ፣ እንዲያስቀድሱ፣ እንዲጸልዩ፣ እንዲቆርቡ ይምከሯቸው፡፡

## *ጥያቄዎች*

- ☞ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው?
- ☞ ቤተ ክርስቲያን ሲባል ማንን እንደሚያመለክት በዝርዝር(አብራርታችሁ) ግለጹ፡፡
- ☞ በጸሎተ ሃይማኖት አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን፡-

  ሀ. አንዲት ናት

  ለ. ዓለም አቀፋዊት ናት

  ሐ. ሐዋርያዊት ናት

  መ. ቅድስት ናት፤ በፊደል ተራ የተጠቀሱትን እያንዳንዳቸውን በተማራችሁት መሠረት በማብራራት ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የጸሎተ ሃይማኖት ማብራሪያ (ስለ መንፈስ ቅዱስ) (፫)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለሚመጣው ዘላለማዊ ሕይወት፤ ስለሚገለጠውም ክብር ያውቃሉ፤ መምህር የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ" ፩ቆሮ. ፲፭፥፳፪

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፳፬፣፳፭፣ ፩ቆሮ. ፲፭፥፩–፶፯ እና ራእ. ፳፩፥፩–፳፯

## መግቢያ

የጸሎተ ሃይማኖት የመጨረሻ አንቀጽ ተስፋ ትንሣኤን ያስነብበናል፡፡ "የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ የሚመጣውንም ሕይወት እንጠብቃለን፡፡" በማለት የሰው ፍጻሜ በመቃብር በስብሶ መቅረት ሳይሆን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚጠብቀው፤ ይህንንም በተስፋ እንደሚጠብቀው ያስተምራል፡፡ ከአምስቱ አዕማደ ምስጢራትም ትንሣኤ ሙታን አንዱ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ትንሣኤ ማለት "ተንሥአ" ተነሣ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን ‹‹መነሣት›› ማለት ነው፡፡ በዚህ ምድር ከኃጢአት እንቅልፍ በመንቃት የበራውን የክርስቶስን ብርሃን ማየት በብርሃኑም ጸዳል መመላለስ የልቡና ትንሣኤ (ትንሣኤ ልቡና) ይባላል፡፡ ኤፌ. ፭፥፲፬፡፡

በምጽአት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌትነቱ ሲመጣ ሙታን የሚነሡት ትንሣኤ (ትንሣኤ ሙታን) ይባላል፡፡ ትንሣኤ ሙታን የክብር (ዘለክብር) እና የውርደት (ዘለሃሳር) በመባል ይከፈላል፡፡ የክብር ትንሣኤ በክርስቶስ አምነው በደሙ ተዋጅተው የጸደቁትን ጻድቃንን ሁሉ ይመለከታል፡፡ የውርደት ትንሣኤ በዚህ ምድር ከእግዚአብሔር ፍቅር ርቀው በኃጢአት የኖሩ በክርስቶስ ያላመኑ ኃጥአንን ሁሉ ይመለከታል፡፡ ዮሐ. ፭፥፳፱፡፡

www.zeorthodox.org

ሞት በአዳም ኃጢአት ባርነት ገብቶ ወደ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ደረሰ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ሻረ፡፡ አሁን ሞት በክርስቲያኖች ላይ ኃይል የለውም፡፡ የምንሞተው ወደ ዘላለም ሕይወት ለመሻገር ነው፡፡ ሰው ሞቶ አይቀርም፤ ተስፋ ትንሣኤ ስላለው ይነሣል፡፡ ትንሣኤ ሙታን የሚመለከተው ሰውን ብቻ ነው፡፡

ክርስቶስ ደግሞ ሲመጣ የሰው ልጆች ሁሉ እንነሣለን፡፡ ፍርድም እንቀበላለን፡፡ በትንሣኤ የሚነሣው አካል የማይጠፋ፣ የከበረ፣ ጠንካራና የማይበሰብስ ነው፡፡ ፩ቆሮ. ፲፭፥፵፪፡፡ በአሁኑ አካላችንና ወደፊት በምንለብሰው የትንሣኤ

**አካል መካከል ያለው ግንኙነት በዕፀዋትና** በዘሩ መካከል ባለው ግንኙነት ይመስላል፡፡

የምንነሣው በመላእክት አለቃ (በቅዱስ ሚካኤል) ድምፅ የመለከት ድምፅ ስንሰማ ነው፡፡ አልአዛር የጌታን ድምፅ ሰምቶ ከመቃብር እንደተነሣ በመቃብር ያሉት ድምፁን ሰምተው ይነሣሉ፡፡ **፩ቆሮ. ፲፭÷፶፩፣ ፩ተሰ. ፬÷፲፯፣ ዮሐ. ፭÷፳፭-፳፱**፡፡

"የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን፡፡›› የሚለው ከፍርድ በኋላ የምንወርሰውን መንግሥተ ሰማያትንና የምንኖረውን በዕድሜ የማይገደብ የዘላለም ሕይወት ያመለክታል፡፡ ይህን የዘላለም ሕይወት ከክርስቶስ ለይተን ማየት አንችልም፡፡ የሚመጣው ሕይወት ተስፋችን ክርስቶስ ነው፡፡

የመንግሥተ ሰማያትን ደስታና የዘላለም ሕይወት ልንገምተውና ልናስበው አንችልም፡፡ **፩ቆሮ. ፪÷፱**፡፡ **ይህ የማይገመት** ደስታ የማይቆጠር ዘመን የሚሰጠው በክርስቶስ ጸጋና እምነት ነው፡፡ ለዚህ ክብር እንድንበቃ "በእኔ ኑሩ" እንዳለን በእርሱ እንኑር፤ በመምጣቱ በእርሱ ፊት እንዳናፍር፡፡ **፩ዮሐ. ፪÷፳፯-፳፱**፡፡

## ማጠቃለያ

ሰው ተስፋ ትንሣኤ ያለው ፍጡር ነው፡፡ ክርስቶስ ደግሞ ሲመጣ ሙታን ይነሣሉ፡፡ አንዳንዳቹ ለፍርድ ሌሎቹ ለክብር ትንሣኤ ይነሣሉ፡፡ ከፍርዱ በኋላ በክብር ለተነሡት የዘላለም ሕይወት ይጠብቃቸዋል፡፡ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በማይቆጠር ዘመን፣ በማይለካ ደስታና ጨለማ በማይሰሥለጥንባት የበጉ ከተማ ለመኖር በዚህ ምድር ምርጫችንን ልናስተካክል ይገባል፡፡

## ተግባር

- መምህር የዘላለም ሕይወትን እያሰቡ በጽድቅ ሥርዓት እንዲመላለሱ ይምከሯቸው፡፡

www.zeorthodox.org

*ጥያቄዎች*

- የሰው ፍጻሜ በመቃብር በስብሶ መቅረት ሳይሆን አዲስና ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደሚጠብቀው የሚያስረዳው የጸሎተ ሃይማኖት የመጨረሻ አንቀጽ ምን ይላል? ግለጹ።
- ትንሣኤ ማለት ምን ማለት ነው?
- በምጽአት ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌትነቱ ሲመጣ ሙታን የሚነሡት ምን በመባል ይታወቃል?
- ትንሣኤ ሙታን በስንት ይከፈላል? ምን ምን ይባላሉ? እንደየአከፋፈላቸው ማንን እንደሚመለከቱና ምንነታቸውን በማብራራት ግለጹ።
- ሰው ሞቶ አይቀርም፤ ለምን? አብራሩ።
- ‹‹የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን›› በማለት በጸሎተ ሃይማኖት የመጨረሻ ክፍል የተጠቀሰው ምንን ያመለክታል? አብራሩ።
- ይህን ተስፋ ለመጎናጸፍ ምን ማድረግ አለብን? ግለጹ።

www.zeorthodox.org

# ሐሜት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ሐሜት ምንነት ዐውቀው አንደበታቸውን ከክፉ ይጠብቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር፡፡ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ" መዝ. ፻፵፩÷፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፵÷፫፣ ያዕ. ፫÷፪–፲፪ እና ማቴ. ፲፪÷፴፬–፴፯

## መግቢያ

- ሐሜት ምንድን ነው?
- ሐሜት ማንን ይጎዳል?
- ሰውን ለምን እናማለን?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሐሜት ራሳችንን በማጽደቅ ሌሎችን የምንኮንንበት መንገድ ሲሆን የወዳጆችንን ማንነት የምናሳድፍበት የአንደበት ኃጢአት ነው፡፡ ወንድም እኅቶቻትን ወይም ሌሎች የምናውቃቸውም ሆኑ በቅርበት የማናውቃቸው በአጠገባችን በሌሉበት እንዲሁም እነሱ በቦታው ተገኝተው በማያውቁበት ሁኔታ የእነሱን ማንነት በማጥላላት፣ በማናናቅ፣ በማጉደፍ ያላደረጉትን አደረጉ በማለት ለሌሎች መናገር ነው፡፡ ሐሜት የወንድምን ገመና ገልጦ በባዕዳን ፊት ማሳጣት ነው፡፡ ሐሜት የሥራ ፈቶች መዝናኛ ነው፡፡ ሰዎችን ያጋጫል፡፡ ሐሜተኛ ሰው ፈሪ ነው፡፡ በውስጡ ፍርሐት ባይኖር ወንድሙን በግልጽ ፊት ለፊት ይነግረው ነበርና፡፡

በአንደበታችን እግዚአብሔርን ልናመሰግንበት፣ ለሰዎች መልካም የሆነውን ነገር ልንገልጽበት፣ የሰዎችን ተስፋ የሚያለመልምና ልብን የሚያሳርፍ መልካም ቃል ልንናገርበት፣ የምሥራቹን ወንጌል ልንመሰክርበትና መተላለፋችንን ልንናዘዝበት ይገባል፡፡ በአንደበታችን ክፉ መናገር፣ ሰውን ማማት፣ መራገም፣ የሰውን ተስፋ የሚያጨልም፣ የሚያስከፋና ልብንም የሚሰብር ቃል መናገር የለብንም፡፡ ለአንደበታችን ንግግር ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ከመናገራችን በፊት ደግመን ማሰብ ይጠበቅብናል፡፡

www.zoorthodox.org

ንጉሥ ዳዊት "አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር፡፡" በማለት አንደበታችንን እግዚአብሔር እንዲያርምልን ይጸልያል፡፡ ዳዊት ግን በዘመኑ እግዚአብሔርን ያመሰገነ ሰው ነበር፡፡ የአንደበት ጠባቂዎች ማስተዋልና ጥንቃቄ ናቸው፡፡ የምንናገረውን የሚያስተምረን በሰማያት ያለ አባታችን እግዚአብሔር በመልካም ሥርዓት እንዲመራን በጸሎት መጠየቅ አለብን፡፡

ያዕቆብ "አንደበት እሳት ነው፡፡" በማለት አንደበት እንደ ማይገራ ፈረስ እንደሆነብን ይመሰክራል፡፡ ትንሽ እሳት ጫካ እንደምታቃጥል ሁሉ ትንሺ አንደበትም ጦርነት ትቀሰቅሳለች፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሰዎች ስለሚናገሩት ስለከንቱ ነገር ሁሉ

በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ፡፡” በማለት የከንፈራችንን ፍሬ በምጽአት እንደምናጭድ አስረድቶናል፡፡ ማቴ. ፲፪÷፴፬-፴፯፡፡

አንደበታችን መልካም እንዲያወጣ ልባችን መልካም መዝገብ መሆን አለበት፡፡ በልባችን ክፉ ሞልቶ በጎ መናገር አንችልም፡፡ በሌሎች መፍረድ፣ በከንቱ መማል፣ በሐሰት መመስከር፣ ማማት፣ አስጸያፊ ቃላትን ማመንጨት፣ ረብ(ጥቅም) የሌላቸውን ቃላት (ጥቅም የማይሰጥ ንግግር) መናገር፣ መራገም፣ ማማረር፣ ስም ማጥፋት ዛቻና ከንቱ ውዳሴ የአንደበት ኃጢአቶች ናቸው፡፡

የአንደበት ንጽሕናን ለመጠበቅ ከእነዚህ ኃጢአቶች መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ንስሐ መግባት፣ ጸጋውን መፈለግ፣ በመልካም ቃላት መሞላት፣ አስቦ መናገርና ግልጽነት የአንደበታችን ቅድስና ለመጠበቅ ያግዙናል፡፡

## ማጠቃለያ

ሐሜት የሌሎችን ክብር ለማጉደፍ የሚደረግ ዘመቻና ራሳችንን የምናመፃድቅበት ክፉ መንገድ ነው፡፡ ሐሜት ተናጋሪውን፣ ሰሚውንና የሚታማውን ሰው ስለሚጎዳ የአንደበታችንን ቅድስና መጠበቅ አለብን፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎን፤ በአንደበት ንጽሕና የሚታወቁ አባቶችን አብነት በማድረግ ይምከሩአቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ሐሜት ምንድነው? አብራርታችሁ ግለጹ፡፡
- በአንደበታችን ልናደርግበት ወይም ልንጠቀምበት የሚገባን ምንድነው?
- የአንደበታችን ጠባቂዎች ምን ምን ናቸው?
- ከአንደበታችን መልካም ነገር (ቃል) እንዲወጣ ምን መሆን አለበት?
- የአንደበት ኃጢአት የሚባሉት ምን ምን ናቸው? የተወሰኑትን ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የምንኩስና ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ምንኩስና ሕይወት እና ምንነት ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በመመለስ ያብራራሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ብርና ወርቅ የለኝም፤ ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፡፡ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ" ሐዋ. ፫÷፮

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፲፱÷፲፩-፲፪፣ ፩ቆሮ. ፯÷፴፪ እና ‹‹ ማር ይስሐቅ››

## መግቢያ

የምንኩስና ሕይወት ሰው ጌታውን በሙሉ ልብ የሚያገለግልበት፣ ሙሉ ጊዜውን ለቅድስና ሥራ የሚያውልበት፣ ለሌሎች መኖርን የሚለማመድበትና ከጌታ የተቀበለውን በነጻ የሚሰጥበት የተቀደሰ የሕይወት መንገድ ነው፡፡ የምንኩስና ሕይወት የዓለምን ፍቅር ከልብ አውጥቶ ሥጋና መሻቱን ሰቅሎ (ጥሎ) በመንፈስ ፈቃድ የሚመሩበት ሕይወት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የምንኩስና ሕይወት ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ ሕያዋን የምንሆንበት ሕይወት ነው፡፡ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ (ምድረ በዳ) የሄደበት ዓላማ የብሕትውና (የምንኩስና) ሕይወትን ለመባረክ ነው፡፡ ሰው ዓለም ንቃው ሳይሆን ዓለምን ንቆ(ንቆ) መመንኮስ አለበት፡፡ የዓለምን ፍቅር ከልባችን ስናወጣ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ዘልቆ ይገባል፡፡ በረሐው ልባችን በፍቅሩ ወለላ ሲርስ የእግዚአብሔር ፍቅር ይጠራዋል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ያስመንናል፡፡ ፍቅሩ በዓለም ያለንን ኑሮ፣ ሃብትና ንብረት ሁሉ ንቀን እንድንተወው ያደርጋል፡፡ ፍቅሩ እንኳን ኃጢአትን የሥራ መሣሪያችንን፤ መረብን ያስጥላል፡፡ ፍቅሩ የዓለምን ነገር ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት እንድንቆጥር ያደርገናል፡፡ ዮሐ. ፴÷፳፫፣ **ፊልጵ ፫÷፱**፡፡

www.zeorthodox.org

በምንኩስና ሕይወት አባ ጳውሊ፣ አባ እንጦንስና አባ መቃርስ የመጀመሪያዎቹ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ መነኮሳት የቅድስና ሕይወት የተግባር አርአያዎች ሆነዋል፡፡ መነኮሳት የክርስትናን ትምህርት በጽሑፍ አስተላልፈዋል፡፡ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት የገዳማውያን ውጤቶች ናቸው፡፡ መነኮሳት ሙሉ ልባቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ሙሉ የሕይወታቸውን ጊዜ ለፍቅሩ የሰዉ ሰማዕታት ናቸው፡፡

በዘመናችን የመንፈሳዊ ሕይወት ውድቀት በዝቷል፡፡ ሰው ነባቢ እንስሳ እየሆነ ነው፡፡ እንደ ዘመኑ እንጂ እንደቃሉ የማይኖሩ አማኞች እየበረከቱ ነው፡፡ የክርስትና ግብ ምድራዊ ብልጽግና እየሆነ ነው፡፡ ዘለዓለማዊ የሆነውን ሰማያዊ ሃገራቸውን፤ ክርስቶስ

ንጉሣቸውን የረሱ ዜጎች እየተፈጠሩ ነው፡፡ በተግባር በተፈተነ ሕይወት አርአያ የሚሆን፣ በቃሉም በሕይወቱም የሚያስተምር፣ ስለትውልዱ ትንሣኤ የሚጸልይ፣ የዘላለም እውነትን በቃልና በጽሑፍ ለትውልዱ የሚያደርስ፣ የእግዚአብሔር የመልካምነት አሻራ የሚታይበት ሰው ያስፈልጋል፡፡ እንዲህም ለሌሎች መሪና አርአያ በመሆን በቅድስና ሕይወት የሚኖር መነኩሴ ይበላል፡፡

ምንኩስና ብዙ የበጎነት ገፀ በረከቶችን ለምድሪቱ አበርክቷል፡፡ ምንኩስና ለክርስትና መስፋፋትና ለአማኞች መብዛት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ የመንጋው እረኞች ጳጳሳት የምንኩስና ሕይወት ውጤቶች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የብራና መጻሕፍት፣ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት፣ ታሪካዊ ቦታዎችና ድንቅ ቅርሳቅርሶች ሁሉ የምንኩስና ሕይወት ውጤቶች ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

የምንኩስና ሕይወት በሙሉ ልብና በሙሉ ጊዜ እግዚአብሔርን የምናገለግልበትና ለሌሎች የምንተርፍበት ሕይወት ነው፡፡ የጸሎት፣ የነገረ ሃይማኖት፣ የአምልኮ፣ የተመስጦ፣ የትርጓሜያትና የታሪክ መጻሕፍት የምንኩስና ተግባራዊ ውጤቶች ናቸው፡፡

## ተግባር

- *መምህር ተማሪዎችዎን፤ ታላላቅ ገዳማትን እንዲጎበኙ ይምክሯቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡*

### *ጥያቄዎች*

- የምንኩስና ሕይወት ምንድነው? በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡
- የምንኩስና (ብሕትውና) ሕይወትን የባረከው ማነው? እንዴትና የት?
- የምንኩስናን ሕይወት የጀመሩ ናቸው የሚባሉትን ሦስቱን ቅዱሳን አባቶች ግለጹ፡፡
- የምንኩስና ሕይወት ተግባራዊ ውጤት የሆኑትን በመግለጽ ጠቀሜታውንና አገልግሎቱን አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንጉሥ ሳኦል

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ ስለ ንጉሥ ሳኦል ማንነትና ታሪክ ያውቃሉ፤ እግዚአብሔር በተናቀ ሥራ ያሉትን ወደክብር እንደሚያመጣ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል፡፡” ፩ሳሙ. ፲÷፩

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፱፣፲፣፲፪፣፴፩

## መግቢያ

እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ከአስጨናቂዎች መንደር አውጥቶ ወደ ነጻነታቸው ምድር ካመጣቸው በኋላ በመሳፍንት መርቷቸዋል፡፡ የሕዝቡ መሻት ንጉሥ እንዲነግሥላቸው ሲሆን አህያ ጠባቂውን ሳኦልን አነገሠላቸው፡፡ ሳኦል የቂስ ልጅ ሲሆን ቁጥሩ ከነገደ ብንያም ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሳኦል ማለት ከእግዚአብሔር የተለመነ ማለት ነው፡፡ እስራኤላውያን ንጉሥ በፈለጉ ጊዜ እግዚአብሔር በርስቱ ላይ የሾመው የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ ሆነ፡፡ በአንድ ወቅት የአባቱ ሰባት አህዮች ጠፍተው ከብላቴናው ጋር ፍለጋ ወጡ፡፡ በጹፍ ምድር ወዳለው የእግዚአብሔር ሰው ወደ ነቢዩ ሳሙኤል መጡ፡፡ እግዚአብሔር ስለ ሳኦል ለነቢዩ ሳሙኤል አስቀድሞ ነግሮት ነበር፡፡ ሳሙኤል ሳኦልን ሲያየው “በልብህ ያለውን ሁሉ እነግርሃለሁ፤ አህዮችህም ተገኝተዋል፡፡” አለው፡፡

መሥዋዕቱን ባቀረቡ ማግስት ሳሙኤል የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በሳኦል ራስ ላይ አፈሰሰው፡፡ “በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል፡፡ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ትገዛለህ፡፡” አለው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦል ላይ በኃይል ወረደለት፡፡ አሞናውያንንም ድል አደረገ፡፡ www.zeorthodox.org “ሳሙ. ፲፭÷፲፱ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ አልጸናም፡፡ ፍልስጥኤማውያንን ፈርቶ የነቢዩ ሳሙኤልን መምጣት ሳይጠብቅ መሥዋዕት በማቅረቡ እግዚአብሔር ናቀው፤ ክፉ መንፈስ አደረበት፡፡ **፩ሳሙ. ፲፫÷፲፱**፡፡ **እግዚአብሔር ዳዊትን ለንግሥና** እንደቀባው ባስተዋለ ጊዜ በዳዊት ላይ በጠላትነት ተነሣበት፡፡ ብዙ ጊዜ የመግደል ሙከራ አደረገበት፡፡ ዳዊትን አሳደደው፡፡ ዳዊት ግን ሁለት ጊዜ እግዚአብሔር ጠላቱን በእጁ አሳልፎ ሰጥቶት ነበር፡፡ ሆኖም ሳይገለው ራራለት፡፡ ሳኦልም ይህን ባወቀ ጊዜ “እኔ ክፉ በመለስሁልህ ፈንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ” በማለት ዳዊትን አመሰገነው፡፡ **፩ሳሙ. ፳፬÷፲፯**፡፡

ሳኦል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ባደረገው ጦርነት ሲሸነፍ በጊልቦ ተራራ ራሱን ገደለ፡፡ ዳዊት ግን ስለሳኦልና ስለ ዮናታን የሐዘን ቅኔ ተቀኘ፤ ሙሾ አወጣላቸው፡፡ **፪ሳሙ. ፩÷፲፯-፳፯**፡፡

## ማጠቃለያ

በተናቀ ሥፍራ የነበረውን ሳኦልን እግዚአብሔር በከበረ ዙፋን አስቀመጠው፡፡ ሳኦል ግን ላከበረው ለእግዚአብሔር አልታዘዘም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ናቀው፡፡ እግዚአብሔር የከበረ ራእይ በእኛ ላይ አስቀምጧል፤ ራእዩን በመታዘዝ ካልፈጸምንለት መቅረዙን ከእኛ ይወስዳል፡፡ ሳኦል ጸጋው ሲነጠቅ እግዚአብሔር በሾመው ላይ በጠላትነት ተነሣ፤ በመጨረሻም በዳዊት ላይ በወረወረው ሰይፍ ራሱን አጠፋ፡፡ የጥላቻ ፍጻሜ እንዲህ ነው፡፡

## ተግባር

***መምህር ተማሪዎችዎን፤*** ‹‹ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በደስታ አለመቀበል የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?›› በሚል ርእስ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ያድርጉአቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

☞ እስራኤላውያን ንጉሥ በፈለጉ ጊዜ እግዚአብሔር የሾመላቸው የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ማን ይባላል? የስሙ ትርጉም ምን ማለት ነው? ነገዱ ከማን ነው?

☞ ‹‹በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል፡፡›› በማለት የእስራኤላውያን ንጉሥ እንዲሆን በተቀደሰው ዘይት የቀባው ነቢይ ማን ይባላል?

☞ ይህንን የእስራኤላውያንን ንጉሥ እግዚአብሔር የናቀው በምን ምክንያት ነበር?

☞ ከዚህ ንጉሥ ቀጥሎ የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ማነው?

www.zeorthodox.org

# ነቢዩ ንጉሥ ዳዊት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ነቢዩ ንጉሥ ዳዊት ማንነትና ታሪክ ያውቃሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም እንዲያከብሩትና እንዲከበሩ የሚያስችላቸውን ግንዛቤ ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ" መዝ. ፻፱÷፩፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ሳሙ. ፲፮÷፮-፲፫ እና ሐዋ. ፲፫÷፲፯-፳፫፣፴፮

## መግቢያ

ነቢዩ ሳሙኤል ሳኦልን የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ቀባው፡፡ ሳኦል ግን በእግዚአብሔር ፊት ተናቀ፡፡ የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ ነቢዩ ድጋሚ መጣ፡፡ "ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከ መቼ ነው? ከእሴይ ልጆች መካከል ንጉሥ አዘጋጅቻለሁና ወደ ቤተ ልሔም ሂድ" አለው፡፡ ፩ሳሙ. ፲፮÷፩፡፡ ሳሙኤል ወደ ቤተልሔም ወደ ቤተ እሴይ መጣ፡፡ በውጫዊ ቁመና ሊያነግሥ ቀንዱን(ዋንጫውን) ሲያነሣ እግዚአብሔር "ፊቱን የቁመቱን ዘለግታ አትይ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" አለው፡፡ አባቱ የረሳው እረኛው ዳዊት ለንጉሥነት ታጨ፤ እግዚአብሔር "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይ ልጅ ዳዊትን አገኘሁ" አለ፡፡ ነቢዩ ሳሙኤል ዳዊትን ቀባው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ ወረደ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዳዊት ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ታላቅና ተወዳጅ ንጉሥ ነው፡፡ የዳዊት ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ፩ሳሙ. ፲፮ እስከ ፩ዜና ፳፱ ድረስ ተመዝግቧል፡፡ ዳዊት አባቱ እሴይ ቢረሳውም፣ ከወንድሞቹ የሁሉ ታናሽ ቢሆንም እግዚአብሔር አስቦት የሁሉ ታላቅ አድርጎታል፡፡ ዳዊት በዝማሬ ጸጋው እግዚአብሔርን ያከበረ፤ በንግሥና ጸጋው በእስራኤል ፊት ሞገስ ያገኘ፤ በበገናው የሳኦልን ርኩስ መንፈስ ያራቀ ታላቅ ሰው ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ዳዊት ለሠለጠነ ሠራዊት ያስፈራውን ጎልያድን በእግዚአብሔር ስም በወንጭፍ ድንጋይ መትቶ ጥሎታል፡፡ በዚህ ጀብዱ በእስራኤል ቁነጃጅት ሙገሳን አግኝቶ በሕዝቡ ፊት ተወዳጅነትን በሳኦል ፊት ጠላትነትን አትርፏል፡፡ ሳኦል በገዛ ሰይፉ በጊልቦአ እስኪሞት ድረስ ተሠዷል፡፡

ዳዊት በገዛ ዘመኑ ታላላቅ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡ እነሱም፡-

- ከመሳፍንቱ ዘመን ጀምሮ እስራኤልን ሲያጠቁት የኖሩትን ፍልስጥኤማውያንን አሸንፏል፡፡ **፪ሳሙ. ፫÷፲፰**፡፡
- በደቡብ፣ በምሥራቅና በሰሜን ጎረቤት አገሮችን በማስገበር የመንግሥቱን የግዛት ድንበር አስፍቷል፡፡ **፪ሳሙ. ፰**
- ኢያቡሳውያንን በማሸነፍ ኢየሩሳሌም የተባለችውን የተመሸገች ከተማ ወርሮ የመንግሥቱ መናገሻ ከተማ አደረጋት፡፡ **፪ሳሙ. ፭÷፮-፲**፡፡
- ኢየሩሳሌም ለሕዝቡ ሁሉ መንፈሳዊ መሰብሰቢያ ስፍራ ትሆን ዘንድ የቃል ኪዳኑን ታቦት አስቀመጠበት፤ የቤተ መቅደስ መሥሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን አዘጋጀ፡፡ **፪ሳሙ. ፮**
- ብዙ የአምልኮ መዝሙራትን ጻፈ፡፡ መዝሙረ ዳዊት የእርሱ የዝማሬ መጽሐፍ ነው፡፡
- የእስራኤልን የበላይነት አረጋገጠ፡፡
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ በዘመኑ ሁሉ አገለገለ፡፡ ሐዋ. ፲፫÷፴፮፡

ዳዊት ገናና ንጉሥ በመሆኑ መንግሥቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የመሲሁ (የክርስቶስ) መንግሥት ምሳሌ ሆኗል፡፡ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል፡፡ መዝ. ፹፰÷፫-፴፯፡፡ **ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ሥርና ዘር** ተወለደ፡፡ ራእ. ፳፪÷፲፮፡፡ **ክርስቶስ በሚያገለግልበት ዘመን ሰዎች "የዳዊት ልጅ" እያሉ ይጠሩት ነበር፡፡ ማር.** ፲÷፵፯፡፡ **ማቴ.** ፳፩÷፱፡፡ **ዳዊት ታላቅ ነቢይ በመሆኑ የመሲሁን** የኢየሱስን ሕይወት በዝማሬ መጽሐፍ ቀድሞ አመልክቶአል፡፡

## ማጠቃለያ

ዳዊት ያከበረውን እግዚአብሔርን በማክበር ሕዝቡን መራ፡፡ ዳዊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አገልግሎ አንቀላፋ፡፡ እግዚአብሔርን ፈቃዱን በደስታ በመፈጸም ብናከብረው ያከብረናል፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ "ዳዊት እግዚአብሔርን ያሳዘነባቸው አጋጣሚዎች" በሚል ርእስ አጭር ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

- ☞ እግዚአብሔር ‹‹እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ አገኘሁ፤›› ያለውና የእስራኤል ንጉሥ የሆነው ማነው? የማን ልጅ ነው?
- ☞ ይህ ንጉሥ የተሰጡት ጸጋዎች ምን ምን ናቸው?
- ☞ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በወንጭፍ ድንጋይ መትቶ የገደለው ግዙፍና ኃያል ሰው ማን ይባል ነበር? የየት ሀገር ሰው ነው?
- ☞ ይህንን ግዙፍና ኃያል ሰው በእግዚአብሔር ኃይልና ፈቃድ ገድሎ ጠላቶቻቸውን ድል በማድረጉ ምን ሆነ?
- ☞ ይህ የእስራኤል ንጉሥ በዘመኑ ከፈጸማቸው ታላላቅ ሥራዎች ቢያንስ ሦስቱን በማስረጃ ግለጹ፡፡
- ☞ ከዚህ ንጉሥ ሥር እና ዘር የተወለደው ማን ነው? (ራእ.፳፪ ÷ ፲፮፤ማር ÷ ፲ ÷ ፵፮፤ማቴ ÷ ፳፪ ÷ ፱)

www.zeorthodox.org

# ድሃ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በሚችሉት መጠን ድሆችን በመርዳት ለእግዚአብሔር ማበደር መሆኑን ተገንዝበው፤ ድሆችን ይረዳሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ከሁሉ ከሚያንሱት ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት፡፡" ማቴ. ፳፭÷፴፭-፵፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፲፬÷፲፬፤ ፲፮÷፲፱-፴፩፣ ያዕ.፪÷፲፬-፲፯ እና ‹‹ሃብታምና እና ደሃ›› (በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ)

## መግቢያ

ድሃ ማለት የሚያስፈልገው የሌለው ማለት ነው፡፡ የአእምሮ ድሆች፣ የሀብት ድሆችና የመንፈስ ድሆች አሉ፡፡ ክርስትና የአእምሮ ድህነትንና በስንፍና የሚመጣ የሀብት ድህነትን ይቃወማል፡፡ የአእምሮ ድህነት የትምህርት ጉድለት፣ የምርጫ ማጣትና የእውቀት ማነስ ችግር ነው፡፡ የሃብት ድህነት ምግብ፣ መጠለያና ልብስ ማጣት (ሦስቱን መሠረታውያን የሰው ፍላጎቶች) ማሟላት አለመቻል ነው፡፡ በስንፍና የሚመጣው ድህነት "ሊሠራ ከማይወድ ማንነት" የመነጨ ከሆነ "አይብላ" የሚል ትእዛዝ አስከትሏል፡፡ **፪ተሰ. ፫÷፲፡፡ በሁለቱም ድህነቶች የተያዙትን የመርዳትና** ራሳቸውን የማስቻል ሓላፊነት አለብን፡፡ የመንፈስ ድህነት ግን ብልጥግና ነው፤ መንግሥቱን ያወርሳልና፡፡ ማቴ. ፭÷፫፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ድሃ የሚያስፈልገውን ያጣ፣ እንዳይሠራ አቅምና ጤና የሌለው፣ የሰውን እርዳታ የሚሻ ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን አሞፅ፣ በሐዲስ ኪዳን ያዕቆብ፣ በዘመነ ሊቃውንት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የድሃ ጠበቆች ይባላሉ፡፡ አሞፅ "ችግረኛውን የምትውጡ የአገሩንም ድሃ የምታጠፉ እናንተ ሆይ፡- እግዚአብሔር በብርሃንም ምድሪቱን አጨልማለሁ፤ ዓመት በዓላችሁንም ወደ ልቅሶ ዝማሬአችሁንም ወደ ዋይታ እለውጣለሁ፡፡" በማለት ክፉዎችን ገሥጾአል፡፡ አሞ. ፰÷፬-፲፬፡፡

www.zoorthodox.org

ያዕቆብ ደግሞ "የሠራተኞች ደሞዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮሃል፡፡ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል፡፡" በማለት ዓመፀኛ ባለጠጎችን ተቃውሞአል፡፡ ያዕ. ፭÷፩-፮፡፡ **በተጨማሪም "ወላጆች የሌላቸውን ልጆች** ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በእግዚአብሔር አብ ፊት ነውር የሌለበት ንጹሕ አምልኮ ነው፡፡" በማለት እግዚአብሔር ድሆችን በሚጎበኙ የሰውን ደስታ ይገልጣል፡፡ ያዕ. ፩÷፳፯፡፡ **ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "እናንተ ክርስቶስን** ትወዱታላችሁን? አዎ ከሆነ መልሳችሁ

ራቁቱን መንገድ ላይ ወድቆ ለምን አልፋችሁት ወጣችሁ?" በማለት የሰዎችን ልብ የሚነካ ስብከት ሰብኳል፡፡ እግዚአብሔር የሰጠንን በድሆች በኩል ይቀበለናል፡፡ ደግሞ አብዝቶ ይመልስልናል፡፡ ለድሃ የሚራራ ሰው እግዚአብሔር ጸሎቱን ይሰማዋል፡፡ ምሳሌ ፳ ፩÷፲፫፡፡ **ለድሃ የሚሰጥ አያጣም፡፡** ምሳሌ ፳፰÷፳፯፡፡ **በድሃ የሚያላግጥ ፈጣሪውን ይሰድባል**፡፡ ምሳሌ ፲፯÷፭፡፡ **ለድሃ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ያበድራል**፡፡ ለድሃ በእውነት የሚፈርድ ንጉሥ ዙፋኑ ለዘላለም ይጸናል፡፡ ምሳሌ ፳፱÷፲፬፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድሆችን መርዳት እንዳለብን ሲያስተምር "ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ በጻድቃን ትንሣኤ ይመለስልሃልና፡፡" ብሏል፡፡ ሉቃስ ፲፬÷፲፫፡፡ **የአልአዛርና የነዌንም ታሪክ አብነት** በማድረግ በዚህ ምድር ለድሆች ስፍራ የሌላቸው ሰዎች በሰማይ ሥፍራ እንደማይገኝላቸው ገልጿል፡፡ ሉቃስ. ፲፮÷፲፱-፴፩፡፡ **ስለ መጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ሲያስተምር** ድሆችን የሚረዳ ለድሆች ቸርነትን የሚያደርግ ለእርሱ (ለእግዚአብሔር) ማድረግ እንደሆነ ነግሮናል፡፡ እውነት ነው የድሆች ዕዳ ከፋይ፣ የድሆች አባት እርሱ ነው፡፡ ለእኛ የሚደረገውን ለእርሱ እንደተደረገ የሚቆጥር ቸር ፈጣሪ ነው፡፡ ማቴ. ፳፭÷፴፭-፵ ድሆችን ባለን ነገር ሁሉ ልናግዛቸው፣ ልንረዳቸው ይገባል፡፡ የዕውቀት ድሆችን በሚቻለን ሁሉ ልናስተምራቸው፣ ልናስረዳቸው፣ የሃብት ድሆችን ልንደግፋቸው ልንረዳቸው፣ የመንፈስ ድሆችን መልካም አርአያነታቸውን ልንከተላቸው (ልንማርባቸው) ይገባል፡፡

ድሆችን ስንረዳ የበለጠ የምንጠቀመው እኛው ነን፡፡ በመጀመሪያ በገንዘብ የማይተመን ደስታ እናገኛለን፡፡ የእኛ ደስታ በሌሎች ጉድለት ውስጥ ነውና፡፡ በመጨረሻም በትንሣኤ ዘጉባኤ በቀኝ እንቆማለን፤ ለእነርሱ ማድረጋችንን ለራሱ እንዳደረግን በመቁጠር አምላካችን ዋጋ ይከፍለናል፡፡ ስለዚህ ድሆችን የምንረዳው የአምላካችንን ትእዛዝ ፈጽመን ለመሸለም ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ድሆችን በነገር ሁሉ እንደግፋቸው፤ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይደግፈናል፡፡ ለድሆች እንስጥ እግዚአብሔር አብዝቶ ይመልስልናል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ ያላቸውን ገንዘብና የጠበባቸውን ልብሶች ሰብስበው በጋራ ድሆችን እንዲመፀውቱ፣ በትምህርት ቤት በአነስተኛ ኑሮ የሚኖሩትን እንዲደግፉ ይምከሯቸው፤ ያበረታቷቸው፡፡

### ጥያቄዎች

- ☞ ድሃ ማለት ምን ማለት ነው? የአእምሮ ድሃ፣ የሀብት ድሃ፣ የመንፈስ ድሀ የእያንዳ ንዳቸውን ምንነት ግለጹ፡፡
- ☞ በብሉይ ኪዳን፣ በሐዲስ ኪዳን፣ በዘመነ ሊቃውንት የድሀ ጠበቆች የሚባሉት እነማን ናቸው?
- ☞ ድሆችን ስንረዳ የምናገኘው ጥቅም ምንድነው? በተማራችሁት መሠረተ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# የሃገር ፍቅርና መንፈሳዊ ሕይወት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ መንፈሳዊ ሕይወት እና የሀገር ፍቅር ያውቃሉ፤ በሁለቱም ዓለማት ብቁ ዜጋ ሆነው የሚኖሩበትን ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እየሩሳሌም ሆይ ብረሳኝ ቀኜ ትርሳኝ፡፡" መዝ. ፻፴፯÷፭፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፴፯÷፩-፱ እና ነህምያ ፪÷፪-፰

## መግቢያ

መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሔርን የምናከብርበት ሰውን የምናስተምርበት አደባባይ ነው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ለምድራዊ አገራችን አርአያ ለሰማያዊ አገራችን ዜጋ የምንሆንበት ሕይወት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው በሥጋ ለሚኖሩበት ሃገር ሕግ የሚገዛ፣ ሃገራዊ የዜግነት ግዴታውን የሚወጣ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚተጋ እና ለወገን ፍቅር የተሰጠ ማንነት ያለው ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው ለመንፈሳዊው ዓለም የሚያበቃ የእምነት ፍሬ የሚያፈራው በሥጋዊው ዓለም በሥጋ ለባሾች መካከል ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ሃገር በሥጋ የምንኖርበትን ስፍራና ወገንን ያመለክታል፡፡ ሃገር መልክዓ ምድሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ነው፡፡ ሃገርን መውደድ በሥጋዊ ሕይወታችን ለምናደርገው እንቅስቃሴ ይጠቅመናል፡፡ ሃገርን በመውደድ መንፈሳውያን አባቶች አርአያዎቻችን ናቸው፡፡ ዳዊት ኢየሩሳሌምን ይወድ ነበር፡፡ ስለ ኢየሩሳሌም መወረር፣ ስለሕዝቧ መጠቃትና ስለ ቅጥሩዋ መፍረስ አንብቷል (አልቅሷል)፡፡ መዝ. ፻፴፯÷፩-፱፡፡ ነህምያ ስለ ሃገሩ ፍቅርና ስለወገኑ መጠቃት ተጎሳቁሎ ታይቷል፡፡ ነህ. ፪÷፪-፲፡፡

የሃገር ፍቅር መገለጫዎች ሕግን በማክበር አርአያ መሆን፣ በተሰማሩበት መስክ ሁሉ በትጋት በመሥራት ውጤታማ ሆኖ መገኘት፣ የዜግነት ግዴታን መወጣት፣ በፈቃደኝነት ለአገር እድገት የሚበጁ የልማት ሥራዎችን ማከናወን፤ የሃገርን ገጽታ ከሚያቆሽሹ ድርጊቶች መራቅ፣ የአገር ኩራት የሚሆኑ በጎ አሻራዎች ማስቀመጥ(ማኖር) እና ለወገን ጥቅም መቆም ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ክርስቲያን የሁለት ዓለማት ዜጋ ነው፡፡ የሥጋን (የምድርን) ዜግነት በደም፣ የሰማይን ዜግነት በመንፈስ ተቀብሏል፡፡ የምድር ዜጎች የሆንነው በሥጋ ልደት፤ የሰማይም ዜጎች የሆንነው በመንፈስ ልደት ነው፡፡ የሰው ልጆች በመሆናችን የምድር በረከትና ውርስ እንደተገባን ሁሉ፤ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ደግሞ ሰማያዊው ሕይወትና ርስት ይመለከተናል፡፡ ስለዚህ የምትታየውን እና በሥጋ የምንኖርባትን ሃገራችንን በመውደድ በጽድቅ ሥርዓት በመጓዝና አካሂያሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ወደማትታየውና ወደምንናፍቃት ዘለዓለማዊና ሰማያዊት አገር እንሄዳለን፡፡ ዳዊት "ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ" ያለው ለምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ብቻ አይደለም፡፡ በአባቱ በአዳም በደል ጉዞው ስለዘገየ በሕይወቱ ሁሉ እርሷን (ሰማያዊት ርስቱን ነጻ አውጪዋን ኢየሩሳሌምን) በመናፈቅ መኖሩን ያሳያል፡፡ ብረሳሽ ክብሬ ይክዳኝ በማለት ይገልጻል፡፡

መንፈሳውያን ሰዎች ብንሆንም እየኖርን ያለነው በሥጋዊው ዓለም በምድር ነው፡፡ የሥጋዊውን ዓለም መልካም ሕግ ማክበር ይጠበቅብናል፡፡ ምድራዊት አገራችንን "አገሬ ምን አደረገችልኝ? ሳይሆን ለአገሬ ምን አደረኩላት" በማለት ለሀገራችን እና ለሕዝቧ የሚጠቅም ለተተኪው ትውልድ የሚዘልቅ የሚተርፍ ሥራ በመሥራት፣ መልካም አሻራ ልናትምባት ይገባል፡፡ የአገር ፍቅር ከትውልዱ ልብ እየደበዘዘ የብዙዎቻችን ልብ ወደ ሌሎች አገሮች ሸፍቷል፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ ባህል፣ ቋንቋ፣ ፊደልና የዘመን መቁጠሪያ ያላት የረጅም ጊዜ ባለታሪክ አገር ናት፡፡ ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ ከአርባ ጊዜ በላይ በመልካም ተጠቅሷል፡፡ ኢትዮጵያዊነት በብዙዎች ዘንድ ኩራት ነው፡፡ በጎ ገጽታዋን የመገንባት የምትታማበትን ክፉ ገጽታዋን የማጽዳትና ድህነታችንን በሥራ የመፋቅ ሓላፊነት አለብን፡፡

## ማጠቃለያ

በምድር እያለን የማናያት ወደ ሰማያዊቷ አገር ሳንሄድ በፊት ተወልደን ባየናት እና በሥጋ በምንኖርባት አገር በጎ አሻራችንን እናስቀምጥ፡፡ ወገናችንን እንውደድ ፍቅራችን ድንበር ይሻገር፡፡ መንፈሳዊ ሰው ለሥጋዊው ሰው አርአያ ነውና በነገር ሁሉ የበጎነት አርአያዎች እንሁን፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ታላላቅ ሥራዎች ተብለው ከሚጠቀሱት ቀደምት የአባቶቻችን ሥራዎች ውስጥ ለዛሬው ትውልድ መማሪያ አርአያ ይሆናሉ ያሉትን መርጠው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ መንፈሳዊ ሕይወት ምንድን ነው?
- ☞ ሀገር ማለት ምን ማለት ነው? ግለጹ፡፡
- ☞ የሀገር ፍቅር መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
- ☞ ክርስቲያን የሁለት ዓለሞች ዜጋ ነው ሲባል ምን ለማለት ነው? አብራሩ፡፡
- ☞ መንፈሳዊ ሰው በሥጋዊው ዓለም በምድር እንደመኖሩ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

www.zeorthodox.org

# የጸሎት ቤት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ጸሎት ያውቃሉ፤ በዘመናቸው ሁሉ በጸሎት ኃይል የሚኖሩበትን መንገድ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ሳታቋርጡ ጸልዩ” ፩ተሰ. ፭÷፲፯፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፲፰÷፩-፯፣ ማር. ፲፩÷፳፬-፴፮ እና ፩ዮሐ. ፭÷፲፬-፲፭

## መግቢያ

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ጠንካራ ኅብረት የምንመሠርትበትና ግንኙነታችንን አጥብቀን የምንቀጥልበት መንገድ ነው፡፡ ጸሎት ከኃያሉ አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት አንደበት ነው፡፡ ጸሎት የሚታዩና የማይታዩትን የጨለማ ኃይላት የምንቋቋምበት፤ የእግዚአብሔር ታላቅነት በድካማችን እንዲገለጥ ርዳታ የምንጠይቅበት፣ በአምላካችን ክንድ መንገዳችን እንዲቀና የምንማጸንበት መሣሪያ ነው፡፡ ጸሎት እንደ እስትንፋስ የማይቋረጥ የዘመን ሁሉ ድርጊት ነው፡፡ በቤታችን ለምናደርገው የግልና የቤተሰብ ጸሎት የጸሎት ቤት ያስፈልገናል፡፡ የእልፍኞችንን ደጅ ዘግተን በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ስንቆም እርሱ ደግሞ ዘላለማዊ የሆነውን የሰማያዊውን መንግሥት ደጅ ይከፍትልናል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በጸሎት እኛ ብቻ መናገር ሳይሆን እግዚአብሔርንም መስማት አለብን፡፡ እግዚአብሔር እንዲያደርግልን ከመጠየቃችን በፊት የተደረገልንን አስታውሰን ልናመሰግነው ይገባል፡፡ ጸሎታችን ልመናን ብቻ ሳይሆን ምስጋናንም ማጠቃለል አለበት፡፡ ጸሎት ከክብር ወደ ክብር የምንለወጥበት ትምህርት ቤት ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ጸሎት የመንፈሳዊ ተግባራት ሁሉ እናት ናት፡፡ የእግዚአብሔር ባለጠግነት በሕይወታችን እንዲገለጥ፣ ከክፉ አጋጣሚዎች ጥበቃው እንዲከልለን፣ የተሰወረውን የሃብት መዝገብ እንድናይ፣ ዓይናችንን እንዲከፍትልንና በጽድቅ መንገድ እስከ መጨረሻው እንዲመራን ከፈለግን ሳናቋርጥ እንጸልይ፡፡ ጸሎት የሁሉም ነገር ቁልፍ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቸርነት ለማስተዋል በጸሎት እንቁም፡፡

በጸሎታችን ጊዜ የድንዛዜ፣ የድካም ስሜት፣ የእንቅልፍና የሐሳብ መበተን ሲያጋጥመን በስሙ ሥልጣን ዲያብሎስን ልንቃወምና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ለመታገዝ በተማጽኖ መጠየቅ አለብን፡፡ በጸሎት ስንቆም “አባት ሆይ በድካሜ ሁሉ እንዲያግዘኝ እንዴት መጸለይ እንዳለብኝ እንዲያስተምረኝ ኃይሌ ሆኖ እንዲያቆመኝና የመንፈስን ሥራ እንዲያሳየኝ መንፈስህን ላክ” በማለት

ከእግዚአብሔር ጋር የመንፈስ ኅብረት ማድረግ አለብን፡፡

የምንጸልየው በስሙ ሥልጣን በመሆኑ በፍጹም እምነት መቀበላችንን ማመን አለብን፡፡ "የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁ እመኑ ይሆንላችሁማል፡፡" የሚለው ቃል ትዝ ይበለን፡፡ ማር. ፲፩÷፳፬፡፡

የጸሎታችን መልስ ቢዘገይ ከመጠበቂያው ግንብ ሳንወርድ መጠበቅ አለብን፡፡ "በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፤ እርሱ አይዘገይም" የሚለውን የኪዳን ቃል በማሰብ ያለማቋረጥ መጸለይ ይጠበቅብናል፡፡ ዕን. ፪÷፳፫፡፡ **ሃና የልቧን ችግር ለእግዚአብሔር በጸሎት** ከገለጠች በኋላ ፊቷ ሐዘንተኛ መስሎ አልታየም፤ አምና መንገዷን በደስታ ቀጠለች፤ እግዚአብሔርም በመንገዷ መካከል ወንድ ልጅ ሰጣት፡፡ ከጸለይን በኋላ የመልካምነት ጉዟችንን እንቀጥል፤ እርሱ በእርግጥ ይመጣልና የጥያቄያችንን መልስ አንድ ቀን ይሰጠናል፡፡

የጸሎት ቤት የሚያስፈልገን ሐሳባችንን ሰብስበን በጸጥታ እንድንጸልይ ነው፡፡ የጸሎት ቤት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የአማኞች የጋራ ጸሎት በቤተ ክርስቲያን ይከናወናል፡፡ ቅዳሴ፣ ውዳሴና ምስጋና ለአምላካችን የምናቀርብባት ደሴት ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ትበላለች፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቅደስ ገብቶ ሻጮችና ለዋጮችን "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች" ብሏልና፡፡ ማቴ. ፳፩÷፲፫፡፡

## ማጠቃለያ

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት አንደበት፤ እግዚአብሔርም የሚናገረንን የምንሰማበት ጆሮ ነው፡፡ ጸሎት ከክብር ወደ ክብር የምንሸጋገርበት ትምህርት ቤት፤ የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ በስሙ ሥልጣን ሰይጣንን እየረገጥን፤ በምስጋና ቃላት እግዚአብሔርን እያመሰገንን፤ በምልጃና በጸሎት የሚያስጨንቀንን እያስታወቅን መኖር አለብን፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን፤ የጸሎት ሕይወትን እንዲለማመዱ ይምከሯቸው፡፡ መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎች የጸሎት መጻሕፍትን በማንበብ፤ የጸሎት ሕይወትን እንዲማሩባቸውና እንዲጠቀሙባቸው ይንገሯቸው፡፡

www.zeorthodox.org

*ጥያቄዎች*

- ☞ ጸሎት ምንድ ነው?
- ☞ በጸሎት ወቅት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?
- ☞ በምንጸልይበት ጊዜ የድካም፣ የመሰልቸት፣ ሐሳብ የመበታተን ሁኔታ ሲያጋጥመን ምን ማድረግ አለብን?
- ☞ የጸሎት ጥቅም ምንድነው? ግለጹ፡፡
- ☞ የጸሎት ቤት ማን ናት?
- ☞ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጸሎት ቤት የተናገረው እና ያደረገውን በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰውን ሰታምልክ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች በእምነት የሚፈጸም የትክክለኛ አምልኮን ምንነት ያውቃሉ፤ የእግዚአብሔርን መንፈስ በእውነት ያመልካሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡" ዮሐ. ፬÷፳፬፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ. ፮÷፩-፲፰

## መግቢያ

አምልኮ ከልብ የሚመነጭ፤ በተመስጦ የሚከናወን፤ የምናመልከውን ለማወቅ የሚደረግ፤ በመንፈስ የሚመራና በሥራ የሚገለጽ ሕይወት ነው፡፡ አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡ ጸሎታችንን፣ ምጽዋታችንና ጾማችንን እግዚአብሔር እንዲያይልን እንጂ ሰው እንዲያውቅልን እንደ ግብዞች መድከም የለብንም፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ከልዕልናው አገዛዝ ሥር በፍቅር መውደቅ ማለት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

በሃይማኖት የመኖራችን ምስጢሩ አምልኮ ነው፡፡ በዘመናችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ማዕከል አምልኮ ነው፡፡ አምልኮ የምናመልከውን በማወቅ የሚፈጸም፣ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡ እግዚአብሔር በመታወቅ የሚመለክ አምላክ ነው፡፡ የሚያመልኩትም በእውነትና በመንፈስ እንዲያመልኩት ይፈልጋል፡፡ ዮሐ. ፬÷፳፬፡፡ **አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለን መገዛት** ነው፡፡ አምልኮ ብዙ ነገሮች ያካትታል፡፡ ጸሎት፣ ጾም፣ ምጽዋት፣ ስግደት፣ ሙብዓና ምስጋና በአምልኮ ይጠቃለላሉ፡፡ ሰዎች አምልኮ ሲፈጽሙ እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው እንዲያውቅላቸውና እንዲያይላቸው ይደክማሉ፡፡ ሰው አይቶን በውዳሴ ከንቱ ከመጥለፍ በቀር ምን ይጠቅመናል? ከልብ በእውነት የምናደርገውን አምልኮ ዋጋ ከፋዩ እግዚአብሔር ቢያየን ዘለዓለማዊውን ዋጋ በማግኘት እንጠቀማለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የግብዞች የአምልኮ ሕይወት፡-

ግብዞች ከውጭ ሃይማኖተኛ መስለው የሚታዩ ውስጣቸው ግን እግዚአብሔርን የማይመስል ተዋናዮች ናቸው፡፡ "ኒፓክራት" የሚለው የግሪክኛ ቃል ግብዝነት ተገልጾበታል፤ የመድረክ ቲያትረኛ ማለት ነው፡፡ በሕይወት የማይኖሩትን በአደባባይ ይተውናሉና፡፡ ጌታ ኢየሱስ "ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፡፡ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ

የላችሁም፡፡ ምጽዋት ስታደርጉ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፉ፡፡ አንተ ግን ምጽዋት ስታርግ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፡፡ በስውር የሚያይ አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል፡፡ ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፡፡ አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፡፡ ስለዚህ አትምሰሏቸው ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፡፡" በማለት የአይሁድ መምህራንን ግብዝነት በመቃወም አማናዊውን አምልኮ አሳይቶናል፡፡ የግብዝነት መንፈስ ሰውን ማምለክ ነው፡፡ የምናደርገውን በጎ ነገር ሁሉ ሰው እንዲያውቅልን መፈለግና ሃይማኖትን ለክፋታችን መሸፈኛ ማድረግ ሰውን ማምለክ ነው፡፡ ለሚጠፋ እንጀራ መሥራትና በሰው ፊት ክብር ለማግኘት መድከም ዘላለማዊውን ዋጋ አያስገኙልንም፡፡

## ማጠቃለያ

ጾማችንን፣ ጸሎታችንና ምጽዋታችንን ሰው እንዲያውቅልን ሳይሆን በስውር የሚያየን አምላካችን በግልጥ እንዲከፍለን በማመን ማድረግ አለብን፡፡ የግብዝነት መንፈስ ሰውን ማምለክ ነው፡፡ መልካም ነገራችንን ሰው እንዲያይልን መድከም የለብንም፡፡ በሕይወት የማንኖረውን በመድረክ መተወን (ለሰው ብለን ያልሆነውን መሆን) ተገቢ አይደለም፡፡ የአምልኮ ሕይወት ለእግዚአብሔር በትሕትናና በደስታ የምንገዛበት ሕይወት ነው፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን፤ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው እንዲያውቁ የአባቶችን ሕይወት አርአያ በማድረግ ይምከሯቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ በተማራችሁት መሠረት አምልኮ ምንድነው? **ግለጹ**፡፡
- ☞ አምልኮ የሚያካትታቸው መንፈሳዊ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
- ☞ የግብዞች አምልኮ እንዴት ይገለጻል?
- ☞ ትክክለኛና ክርስቲያናዊ አምልኮ ምንድነው? የሚያስገኘው ዋጋስ ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# አልአዛር

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ የትንሣኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ላይ ያለውን ሥልጣን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፡፡ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፡፡" ዮሐ. ፲፩÷፳፭፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፩÷፩-፵፫

## መግቢያ

- አልአዛር ማን ነው?
- የአልአዛርን ሞት ለጌታ ማን ነገረው?
- አልአዛር ስንት ቀን በመቃብር ቆየ?
- ጌታ የአልአዛር ሞት ሲሰማ ምን አደረገ?

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

አልአዛር ማለት "እግዚአብሔር ረድቶአል" ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ስም የሚታወቁ ሦስት ሰዎች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. የአሮን ሦስተኛ ልጅ፡፡ ዘጸ. ፮÷፳፫፡፡
2. ጌታ ከሙታን ያስነሣው የማርያምና የማርታ ወንድም፡፡ ዮሐ. ፲፩÷፩-፳፭፡፡
3. ከሃብታሙ ደጅ የሞተው በአብርሃም እቅፍ የተቀመጠው ድሃ፡፡ ሉቃስ ፲፮÷፲፱-፴፩፡፡

www.zeorthodox.org

የዛሬው ትምህርታችን የሚመለከተው ጌታ ከሙታን ያስነሣውን፣ የማርያምና የማርታ ወንድም የሆነውንና በቢታንያ ይኖር የነበረውን አልአዛርን ነው፡፡ የአልአዛር እኅቶች የጌታ ወዳጆች ነበሩ፡፡ ጌታ በቢታንያ የድሆችን መንደር በጎበኘ ጊዜ በአልአዛር ቤት ያርፍ ነበር፡፡ ማርያም የጌታን ቃል በደስታ ስትሰማ፤ ማርታ የሚመገበውን ለማዘጋጀት በጓዳ ትደክም ነበር፡፡ ሉቃ. ፲÷፴፱-፵፪፡፡ **አልአዛር ጌታን ይወድደው ነበር፡፡ በአንድ** ወቅት አልአዛር ታመመ፤ ማርያምና ማርታ "የምትወደው ታሞአል" ብለው

ወደ እርሱ መልእክት ላኩ፡፡ ጌታ ኢየሱስም "የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም፡፡" አለ፡፡ አልአዛር ሞተ፡፡

አልአዛር በሞተ በአራተኛው ቀን ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቢታንያ መጣ፡፡ በወንድሟ ሞት ያዘነችው ማርታ "ጌታ ሆይ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፡፡" አለችው፡፡ ኢየሱስም "ወንድምሽ ይነሣል" አላት፡፡ ማርታ "በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ፡፡" አለችው፡፡ ኢየሱስም "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" አላት፡፡ ለማርያምም "መምህሩ መጥቶአል" አሏት፡፡ ወጣች ጌታንም አግኝታው "የምትወደው ሞተ አለችው" ከማርያም ጋር የነበሩ ሁሉ አለቀሱ ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ፡፡

አይሁድ "እንዴት ይወደው እንደነበረ እዩ" አሉ፡፡ አንዳንዶቹ "ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን እንዳይሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን?" አሉ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፤ ወደ አልአዛር መቃብር መጥቶ፡፡ "ድንጋዮን አንሡ" አለ፡፡ ማርታ "ጌታ ሆይ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል" አለችው፡፡ በአይሁድ ልማድ እንዲህ ነበርና፡፡ ኢየሱስ "ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታይ አልነገርኩሽምን?" አላት፡፡ ጌታችን እንዳዛዘው በዚያ የነበሩት የመቃብሩን ድንጋይ አነሡ፡፡ ጌታም ወደ አባቱ ጸለየና፡፡ "አልአዛር ሆይ ወደ ውጭ ና" ብሎ ጮኸ፡፡ ሞቶ የተቀበረው አልአዛር እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደተገነዙ ወጣ፡፡ ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበረ፡፡ ኢየሱስም "ፍቱትና ይሂድ ተዉት" አላቸው፡፡ ብዙዎቹ በክርስቶስ አመኑ፡፡

## ማጠቃለያ

የትንሣኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕሙማን ላይ ብቻ ሳይሆን በሞትም ላይ ሥልጣን አለው፡፡ ሕሙማንን መፈወስ ብቻ ሳይሆን ሙታንንም ያስነሣል፡፡ የሁሉ መክፈቻ በመዳፉ ነው፡፡ ሞት በሞቱ ስለተረታ መውጊያም ስለተሰበረ ሞትን አትፍሩ፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ፤ የክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የተገለጠባቸውን ተአምራት እንዲያስታውሱ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

*ጥያቄዎች*

☞ አልአዛር ማለት ምን ማለት ነው?

☞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአልአዛር ስም የሚታወቁ እነማን ናቸው? በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ግለጹ፡፡

☞ ጌታ ከሙታን ያስነሣው አልአዛር ስንት እኅቶች ነበሩት? ማን ይባላሉ?

☞ እኅቶቹ ምን ይሠሩ ነበር? (በምን ሥራቸው ይታወቃሉ?)

☞ አልአዛር ሞቶ በመቃብር የቆየው ለስንት ቀን ነው?

☞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአልአዛርን መሞት ከሰማ በኋላ ምን አደረገ? አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# የኤማሁስ መንገደኞች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የኤማሁስ መንገደኞችን ታሪክ ያውቃሉ፤ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወት ጉዞአችን ሁሉ ከእኛ እንደማ ይለየን ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው፡፡" ዮሐ. ፲፩÷፳፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፲፬÷፲፫-፴፭

## መግቢያ

ኤማሁስ ከኢየሩሳሌም 12 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ የቀለዮጳ ቤት በኤማሁስ ይገኝ ስለነበር ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ተገለጠባት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ክርስቶስን መቃብር ያስቀረው የመሰላቸው ሁለቱ ደቀ መዛሙርት (ሉቃስና ቀለዮጳ) ወደ ኤማሁስ ጉዞ ጀመሩ፡፡ በኢየሩሳሌም የሆነውን እያወሩ ሲመራመሩ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር፡፡ ኢየሱስ "እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው?" አላቸው፡፡

ቀለዮጳ "አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች በዚያ የሆነውን አታውቅምን?" ብሎ መለሰለት፡፡ ጌታም "ይህ ምንድን ነው?" አላቸው፡፡ እነርሱም "በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንዲሰጡትና እንደሰቀሉት ነው፡፡ እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው፡፡ ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፡፡ ሥጋውን ባጡ ጊዜ፡- ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ አየን ሲሉ መጥተው ነበር፡፡ ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደተናገሩት መጥተው አገኙት እርሱን ግን አላዩትም፡፡" አሉት፡፡

ኢየሱስም "እናንተ የማታስተውሉ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን?" አላቸው፡፡ ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የጻፈውን ተረጎመላቸው፡፡ ወደ ኤማሁስም በደረሱ ጊዜ እሩቅ የሚሄድ መሰላቸውና "ከእኛ ጋር እደር ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል" ብለው ግድ አሉት፡፡ ከእነርሱ ጋር ሊያድር ገባ፡፡

www.zoorthodox.org

ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው ቆርሶም ሰጣቸው ዓይናቸውም ተከፈተ፡፡ ዐወቁት፤ ከእነርሱ ተሰወረ፡፡ እርስ በርሳቸው "በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?" ተባባሉ፡፡ በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡

ክርስቶስ አማኞችን በመንገዳቸው ቃሉን እየገለጠ በኑሯቸው እየደገፈ ወደ ሙላቱ ያመጣቸዋል፡፡ በሕይወት ዘመናችን የእርሱ ቃል፣ ፍቅር፣ ጥበቃ፣ ምሕረትና ቸርነት ያስፈልገናል፡፡ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" በሚለው አምላካዊ ቃል ኪዳን መሠረት በጉዞአችን ሁሉ አብሮነቱ አይለየንም፡፡ ማቴ. ፳፰÷፳፡፡ **እርሱን በሚናፍቅ ልብ ቅዱሳት መጻሕፍትን** በማንበብና ቅዱስ ቁርባን በመቀበል "ከእኛ ጋር ሁን ታስፈልገናለህ" በማለት አብሮን እንዲሆን መለመን አለብን፡፡

## ማጠቃለያ

የኤማሁስ መንገደኞች ተስፋ ሲቆርጡ ጌታ በመካከላቸው ተገኝቶ ተስፋቸውን አለመለመላቸው፡፡ ባወቁትም ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡ እርሱን ካወቅንና ካገኘን በኋላ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ መመለስ አለብን፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎቹ ከባለታሪኮቹ ምን እንደተማሩ ይጠይቋቸው፡፡

## *ጥያቄዎች*

- ☞ የኤማሁስ መንገደኞች በመባል የሚታወቁት ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እነማን ናቸው?
- ☞ እነዚህ የኤማሁስ መንገደኞች በጉዞአቸው ላይ ያጋጠማቸው ምን እና ማን ነበር?
- ☞ ከኤማሁስ መንገደኞች ታሪክ የተማራችሁትን (የተገነዘባችሁትን) በአጭሩ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ቅዱስ ዮሐንስ ማንነትና ታሪክ ያውቃሉ፡፡ አርአያነቱን ተምረው በእምነትና በሕይወት እንዴት መምሰልና መኖር እንዳለባቸው ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግስቱን የምካፈል ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ፡፡" ራእይ ፩÷፱፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፫÷፳፫

## መግቢያ

ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው፡፡ ማቴ. ፬÷፳፩፡፡ በቤተሳይዳ ዓሣ በማጥመድ ሥራ ይተዳደር ነበር፡፡ በዚሁ ሥራ ላይ ሳለ ክርስቶስ ጠራው፡፡ ከጴጥሮስና ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ሁሉን ትተው ጌታን ተከተሉት፡፡ ሉቃ. ፭÷፲፩፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ዮሐንስ ከሃብታም ቤተሰብ የተወለደ ወጣት ነበር፡፡ ማር. ፩÷፳፡፡ **ዮሐንስ ረጋ ያለ ሰብእና ያለው አስተዋይ ደቀመዝሙር ነበር፡፡ ዮሐንስ የምስጢር** ሐዋርያ ነው፡፡ ጌታ ወደ ቤተ ኢያኢሮስ ሲገባ ወደ ታቦር ተራራ ሲወጣና በአትክልቱ ስፍራ ለጸሎት በሄደ ጊዜ ዮሐንስ አብሮ ነበር፡፡ ዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር የፋሲካን እራት አዘጋጅቷል፡፡ ሉቃ. ፳፪÷፰፡፡ **ዮሐንስ ተወዳጅ ደቀመዝሙር ስለነበር** የጌታ ወዳጅ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ዮሐ. ፲፫÷፳፫፡፡

www.zeorthodox.org

## የዮሐንስ ስሞች

- ፍቁረ እግዚእ - ጌታ ይወደው ስለነበር
- አቡቀለምሲስ - የራእይ መጽሐፍን ስለጻፈ (ባለራእይ ስለሆነ)
- ታዖሎጎስ (ነባቤ መለኮት) - ነገረ መለኮትን በወንጌሉ ስላብራራ
- ቁጽረ ገጹ - የጌታን መከራ ካየ በኋላ በዘመኑ ሁሉ ፊቱ የተቋጠረ ስለነበር
- ወልደ ነጎድጓድ (ቦአኔርጌስ) - በሰማርያ ክርስቶስ ያላመኑትን እሳት ይብላቸው ስላለ፡፡

ዮሐንስ በንስር ይመሰላል፡፡ ንስር ከሩቅ ያለውን ማየት እንደሚችል ሁሉ ዮሐንስም ርቆ "ቀዳሚሁ ቃል" በማለት ስለጀመረ

በንስር ተመስሏል፡፡ ዮሐንስ ከሦስቱ ወንጌላውያን በበለጠ ሁኔታ ስለ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ጽፏልና፡፡

ዮሐንስ አንድ ወንጌል፣ ሦስት መልእክታትና አንድ የራእይ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በወንጌሉ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን የዘላለም ሕይወት እንደሚገኝ፤ በመልእክቱ ክርስትና በፍቅር የምንመላለስበት ሃይማኖት እንደሆነ፤ በራእዩ የአማኞች ፍጻሜ ምን እንደሚሆን ገልጾአል፡፡ ዮሐንስ የማይታሰር ቃሉን የጻፈው በፍጥሞ ደሴት በእስር ሆኖ ነው፡፡ ዮሐንስ በወንጌሉ ስሙን አልጠቀሰም፡፡

ዮሐንስ በጽሑፎቹ የክርስቶስን ማንነት በብዙ ዓይነት አብራርቶአል፡፡ "የሕይወት ውኃ ሕያው እንጀራ፣ የወይን ግንድ፣ ትንሣኤና ሕይወት፣ መንገድና እውነት፣ መልካም እረኛና የበጎች በር" በማለት ክርስቶስ ስለራሱ የተናገራቸውን በሚገባ ጽፏልናል፡፡ ስለክርስቶስ የዮሐንስ መጥምቅና የደቀ መዛሙርቱን፤ የሳምራዊቷንና የሰማርያ ሰዎችን ምስክርነት መዝግቧል፡፡ ሰባት ተአምራትንም መርጦ ጽፏል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችን ማርያምን በአደራ እናትነት የተሸለመ የመስቀሉ ሥር ሐዋርያ ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም ውጪ የሆነ አገልግሎት የጀመረው ከእመቤታችን ዕረፍት በኋላ ነው፡፡ ዮሐንስ ስለ ወንጌል ዘመኑን ሙሉ የተገፋ ምስክር ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ዮሐንስ ጌታ ይወደው የነበረ የመስቀሉ ሥር ሐዋርያ ነው፡፡ መጻሕፍቱ ስለ ክርስቶስና በክርስቶስ ስለተገለጠው የዘላለም ሕይወትና ፍቅር ያብራራሉ፡፡ ዮሐንስ መስቀሉ ሥር ጸንቶ ስለተገኘ ድንግል ማርያምን ተሸልሟል፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎን በሦስት ቡድን ከፍለው ይመድቧቸው፡፡ ሦስቱን የዮሐንስ መልእክታት ለእያንዳንዱ ቡድን አከፋፍለው ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎች የእያንዳንዱን የመልእክት ጭብጥ አጥንተው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

*ጥያቄዎች*

☞ ዮሐንስ አባቱ ማን ይባላል? ወንድሙስ?

☞ የዮሐንስን ስሞች እና ትርጉማቸውን በዝርዝር ግለጹ።

☞ ዮሐንስ የሚመሰለው በምንድን ነው? ለምን?

☞ ዮሐንስ የጻፋቸው ምን ምን ናቸው? እያንዳንዱ ጸሑፎች የሚገልጹት ስለምንድን ነው?

☞ ዮሐንስ ጽሑፎቹን የጻፈው የት ሆኖ ነው?

☞ ቅዱስ ዮሐንስ የመስቀሉ ሥር ሐዋርያ በመሆን እስከ መጨረሻው ጸንቶ በመገኘቱ የተሸለመው ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ታየ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ተማሪዎች ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ያደረገውን ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡*

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ክርስቶስ ካልተነሣ ስብከታችን ከንቱ ናት፡፡" ፩ቆሮ. ፲፭÷፲፬፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፳፣ ፳፩ እና ፩ቆሮ. ፲፭÷፩-፶፯

## መግቢያ

ክርስቶስ ስለ ሰው መተላለፍ ቆሰለ፡፡ ስለኃጢአተኞች ሞተ፡፡ ሞትን በሞቱ ሽሮ በሞት ፍርሐት የተጠቁትን ነጻ አወጣ፡፡ የሞትን መውጊያ ሰብሮ የድሉን ዜማ አበሠረ፡፡ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፡፡ ከትንሣኤው በኋላ በመከራው የሸሹትንና ተስፋ ቆርጠው የተበተኑትን ሰብስቦ የትንሣኤው ምስክሮች አደረጋቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

### 1. የመላእክት ስብከት

ክርስቶስ ከሞት እንደሚነሣ ቀድሞ የተናገረና ከመሞቱ በፊት ቀጠሮ የሰጠ ጌታ ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ግን ልባቸው ከማመን ዘገየ፡፡ በዚህ ሰዓት የደቀ መዛሙርቱን ልብ በእምነት የሚያጸና፣ የጌታን ቃል በማረጋገጥ ተስፋን የሚያለመልም የመላእክት ራእይ ተገለጠ፡፡ መላእክቱ የትንሣኤው ቀዳሚ ምስክሮች ናቸው፡፡ መላእክት "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ? ተነሥቷል እንጂ በዚህ የለም፡፡ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደተናገረ አስቡ፡፡" በማለት ሰባኪዎችን ሰበኩአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

### 2. የማርያም ፍለጋ

ማርያም ጌታዋን ፍለጋ ወደ መቃብር መጣች፡፡ የመቃብሩ ድንጋይ በመነሣቱ ደንግጣ ለጴጥሮስ ነገረችው፡፡ ወደ መቃብሩ ተመልሳ ቆማ ስታለቅስ የመላእክትን ራእይ አየች፡፡ መላእክቱም "ስለምን ታለቅሻለሽ?" አሏት፡፡ እርሷም "ጌታዬን ወስደውታል፡፡" አለቻቸው፡፡ መላእክቱ "ተነሥቷል" አሏት፡፡ ከመላእክቱ ጋር ተነጋግራ ዘወር ስትል ኢየሱስ ቆሞ አየችው፡፡ እርሷም የአትክልት ጠባቂ መስሏት "ጌታዬን ወስደኸው እንደሆነ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ፡፡ እኔም እወስደዋለሁ፡፡" አለችው፡፡ ጌታም "ማርያም" ብሎ በስሟ ጠራት፡፡ ዐወቀችው፡፡ "መምህር ሆይ" አለችው፡፡ ኢየሱስም "ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ሂጂ ተናገሪ፤ በዚያም

ያዩኛል፡፡" አላት፡፡ ማርያምም ጌታ እንዳላት አደረገች፡፡ ዮሐ. ፳፥፩-፲፰፡፡

## 3. የሳምንቱ ፊተኛ ቀን ምሽት

ከሳምንቱ ፊተኛው ቀን በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፣ አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፡፡ በመካከላቸው ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" አላቸው፡፡ ከእነሱ መካከል ቶማስ አልነበረም፡፡ ዮሐ. ፳፥፲፱፡፡

## 4. የቶማስ ጥርጣሬ

ቶማስ "አይተነዋል፤ ተነሥቷል" የሚሉትን የወንድሞቹን ምስክርነት አላመነም፡፡ "የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካለየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም፡፡" አለ፡፡ ዮሐ. ፳፥ ፳፭፡፡

## 5. ከስምንት ቀን በኋላ (ዳግም ትንሣኤ)

ከሳምንት ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ በተሰበሰቡበት የተጠራጠረው ቶማስም ባለበት ደጆቹ ተዘግተው ሳለ ኢየሱስ መጣና በመካከላቸው ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" አላቸው፡፡ ቶማስን "ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፡፡ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን" አለው፡፡ ቶማስም ጌታ እንዳለው አደረገ፡፡ ጮሆ "ጌታዬ አምላኬም" ብሎ መለሰ፡፡ ኢየሱስ "ስለ አየኸኝ አምነሃል ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው፡፡" አለው፡፡ ዮሐ. ፳፥ ፳፮-፳፱፡፡

## 6. የጥብርያቆስ ድግስ

ደቀ መዛሙርቱ በቀድሞ ሥራቸው በተሠማሩበት በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ ጌታ እንደገና ተገጠላቸው፡፡ "ልጆች ሆይ አንዳች የሚበላ አላችሁን?" አላቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም "የለንም" ብለው መለሱለት፡፡ "መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት" አላቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ እንዳላቸው ሲያደርጉ 153 ታላላቅ ዓሣዎችን አጠመዱ፡፡ ጴጥሮስ ሲገረም ዮሐንስ "ጌታ እኮ ነው" አለው፡፡ ጴጥሮስ ደንግጦ ወደ ባሕሩ ገባ፡፡ ሌሎቹ ግን ዓሣ የሞላውን መረብ እየጎተቱ በጀልባ አወጡ፡፡

www.zeorthodox.org

ጌታም የተጠበሰ ዓሣ መገባቸው፡፡ "ኑ ምሳ ብሉ" አላቸው፡፡ በደስታ በሉ፡፡ ይህ መገለጥ ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገ ነበር፡፡ ምሳ ከበሉ በኋላ መንጋውን እንዲጠብቁ ሓላፊነት ሰጣቸው፡፡ የደቀ መዛሙርቱ ሥራ ምስክርነትና መንጋውን መንከባከብ ነው፡፡ ምስክርነታቸው ያላመኑትን ወደ ፍቅሩ መንግሥት አምጥቶአል፡፡ ጥበቃና እንክብካቤአቸው መንጋውን አጽንቷል፡፡ ዮሐ. ፳፩፥፩-፲፯

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለመላእክት፣ ለሴቶች፣ ለደቀ መዛሙርቱና ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ሰዎች ታየ፡፡ ለደቀ መዛሙርቱ የምስክርነትና የጥበቃ ሓላፊነት ሰጠ፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ "የክርስቶስ ትንሣኤ ማረጋገጫ ማስረጃዎች" በሚል ርእስ አጭር ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

### *ጥያቄዎች*

- ‹‹ክርስቶስ ከሞት እንደሚነሣ አስቀድሞ የተናገረ እና ከመሞቱ በፊት ቀጠሮ የሰጠ ጌታ ነው›› የሚለውን አባባል በመላእክት ስብከት መሠረት አብራሩ፡፡
- ጌታችንን ፍለጋ ወደ መቃብሩ የሄደችው ማን ነበረች? በዚያ ምን አጋጠማት? ማንን አገኘች? ምንስ ተባለች?
- ‹‹ጌታችን ከሞት ተነሥቶአል፤ አይተነዋል›› በማለት ደቀ መዛሙርቱ ሲነግሩት የተጠራጠረው ደቀ መዝሙር ማን ነው?
- በዳግም ትንሣኤ የተደረገውን በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ግለጹ፡፡
- በጥብርያዶስ ባሕር ዳርቻ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጠው ማን ነው? በዚያ ምን ተደረገ?

www.zeorthodox.org

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች፤ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ስለአለው ሚና ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፡፡” ሐዋ. ፩÷፰፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዮሐ. ፲፯÷፯-፲፩፣ ሐዋ. ፪÷፩-፬፣ ኤፌ. ፬÷፴ እና ፩ቆሮ. ፮÷፳

## መግቢያ

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ የሥላሴ አካላት አንዱ ሲሆን፤ አካል ያለው መንፈስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሰጭና ምስጢር ገላጭ የሆነ የእውነት መንፈስ ነው፡፡ ነቢያትን በትንቢት ጸጋ የሾመ ነገሥታትን በምስፍና ቅባት የቀባና የሐዋርያትን አገልግሎት ያሳካ አጋዥ መንፈስ (ጰራቅሊጦስ) ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረጸ ጌታ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መንፈስ ቅዱስ በድካማችን ሁሉ የሚያግዘን የሕይወት መምህር፤ የቤተ ክርስቲያን የማይታይ መሪ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ጉዞና የሕይወት እንቅስቃሴ ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ውጭ ከሆነ ፍጻሜው ሞት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ባመነ ሰው ልብ ያድራል፡፡ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ታቦት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ “ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ (ቤተ መቅደስ) እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፡፡” በማለት ሰው የመንፈስ ቅዱስ ሕያው ቤተ መቅደስ እንደሆነ አረጋግጦልናል፡፡ **፩ቆሮ. ፮÷፳፮፡፡**

መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት እንድንመለስ ለንስሐ እንድንበቃ ይቀሰቅሰናል፡፡ በንስሐ ስንመለስ ከርኩሰታችን ይቀድሰናል፡፡ **፩ቆሮ. ፮÷፲፩፡፡ በእርሱ ፈቃድ መመለስ ስንጀምር እያበረታ** ለክብሩ የሚሆን የመንፈስ ፍሬዎችን ያፈራልናል፡፡ እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነትና ራስን መግዛት ናቸው፡፡ ገላ. ፭÷፳፪-፳፬፡፡

www.zeorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ ዓይኖቻችን በጎውን ዘመን እንዲያዩና ክብሩን እንድንወርስ በጉዟችን ሁሉ ይመራናል፡፡ በሕይወታችን ይደግፈናል፡፡ እውነት የሆነውን ይለይልናል፡፡ **፩ዮሐ. ፪÷፳፯፡፡ መንፈስ ቅዱስ የመንፈስ ሥራ ያስተምረናል፡፡** ሮማ. ፰÷፳፯፡፡ **መንፈስ ቅዱስ በእኛ ዘንድ ሲኖር በመንፈስ** እንጂ በሥጋ አንሆንም፡፡ ከክርስቶስ ወገን መሆናችን የሚረጋገጠው መንፈሱ በእኛ ሲኖር ነው፡፡ ለሚሞተው ሰውነታችን ሕይወት የሚሰጠው በእኛ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ሮሜ. ፰÷፱-፲፯፡፡ **መንፈስ ቅዱስ ለክብሩ የሚሆን በፍሬዎቹ** ያጌጠ ዓለም እንዲያደርገው ሰው በደስታ መፍቀድ አለበት፡፡ ከእርሱ እንዳይርቅም “ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አትውሰድብኝ” እያለ መጸለይ አለበት፡፡ መዝ. ፶÷፲፩፡፡

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ጉዞና እንቅስቃሴ መሪ ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ የሚደረግ ነገር ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለክብሩ የሚያስጌጠን ውበት፣ በድካማችን የሚያግዘን ኃይል፣ እንዴት መጸለይ እንዳለብን የመንፈስን ሥራ የሚያስተምረን የሕይወት መምህር ነው፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎን፤ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር እንዲመቹ ይምከሯቸው፡፡

### *ጥያቄዎች*

- መንፈስ ቅዱስ ምንድነው? **በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡**
- **አንድ ክርስቲያን ምእመን** ‹‹የመንፈስ **ቅዱስ** ታቦት ነው›› **ሲባል ምን ማለት** ነው? **በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ግለጹ፡፡**
- **መንፈስ ቅዱስ ምን ያደርግልናል?**
- **የመንፈስ ፍሬዎች ምን ምን ናቸው?**

www.zeorthodox.org

# የጸጋ ስጦታዎች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ስለ ጸጋ ምንነት ተገንዝበው ጸጋቸውን በማወቅ ያገለግላሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡፡" ፩ቆሮ. ፲፪÷፲፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ቆሮ. ፲፪÷፬-፴፩ እና ሮሜ. ፲፪÷፫-፱

## መግቢያ

ጸጋ ተቀባዩ የማይመጥነው ነጻ ስጦታ ማለት ነው፡፡ የጸጋ ስጦታዎች ልዩ ልዩ ናቸው፤ ሰጪው መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው፡፡ የጸጋ ስጦታዎች የመንፈሰ ቅዱስ የችሮታ ስጦታዎች ናቸው፡፡ የሚሰጡበትም ዓላማ ሰጪውን እግዚአብሔርን ለማክበር ነው፡፡ ከቋንቋና ከወገን ከሕዝብና ከወገን በደሙ በተዋጁ አማኞች ላይ የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች አስቀምጧል፡፡ በሁሉም የጸጋ ስጦታዎች የሚመሰገነው አንዱ እግዚአብሔር ነው፡፡ የጸጋ ስጦታዎች ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት ሠራተኛ እንዲሆን ያቀረቡት መሰላሎች ናቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የጸጋ ስጦታዎች አንዱን ጌታ ለማገልገል የተሰጡ ልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች ናቸው፡፡ መዘመር መስበክ፣ ትንቢት መናገር፣ ራእይ ማየት፣ መምከር፣ ጥበብ ማድረግ፣ አጋንንትን ማውጣት፣ በልሳን መናገር፣ መተርጎም፣ መምራት፣መጻፍ፣ መሣል፣ ማዳመጥና መናገር ልዩ ልዩ ከሚባሉት የጸጋ ስጦታዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ የሁሉም ምንጭና ሰጪ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ዳዊት ሰባት የጸጋ ስጦታዎች ተሰጥተውት በሁሉም እግዚአብሔርን አስደስቷል፡፡ አካል አንድ ሲሆን ብዙ ብልቶች እንዳሉት፤ የአካል ብልቶችም ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ ክርስቶስም እንዲሁ ነው፡፡ እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡፡ የተለያዩ ጸጋዎቻችን የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ናቸው፡፡ በክርስቶስ አካል አንድ እንደሆንን ሁላችንም ለአካሉ እናስፈልጋለን፡፡ በሰውነታችን ልዩ ልዩ አካላት እንዳሉን ሁሉ በተለያየ አገልግሎታቸው ሁሉም ለእኛ አስፈላጊዎቻችን ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

አማኞች ጸጋቸውን ሊያውቁና ሊጠቀሙበት የሌሎችንም ጸጋ ሊያከብሩ ይገባል፡፡ ጸጋን አለማወቅ ድካሙ ብዙ ነው፡፡ በጸጋ አለማገልገል የተገልጋዩን ሕመም ማብዛት ነው፡፡ በሌሎች ጸጋ ደስተኛ አለመሆን ምቀኝነት ነው፡፡ የሁሉም ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ገጽታ የሚዋበው በጸጋ ስጦታዎች ነው፡፡ የተሰጣቸው ጸጋ በአግባቡ ዐውቀው በትክክል አገልግሎት

ላይ ካላዋሉት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ገጽታዋ ይበላሻል፡፡

በጸጋ ስጦታዎቻችን ታምነን በሚገባ ካላገለገልንባቸው ዋጋ ያስከፍላሉ፡፡ የጸጋ ስጦታዎች እግዚአብሔርን ለማክበርና ሰውን ለመጥቀም ያስፈልጋሉ፡፡ ሁሉም ባለጸጋዎች በፍቅር ሲያገለግሉ የአንዱ ጌታ አገልጋዮች መሆናቸውን ያስመሰክራሉ፡፡ የጸጋ ስጦታዎች በትሕትና፣ በፍቅርና በትዕግሥት ይገለጣሉ፤ ይገልጣሉ፡፡

ወጣቶች ጸጋችሁን ፈልጋችሁ በማግኘት (በማወቅ) በጸጋችሁ በማገልገል ወደ በረከት ዳርቻ መምጣት አለባችሁ፡፡ ያለ ጸጋ የተፈጠረ የለም፡፡ ጸጋ እንደ መክሊት ነው፤ ስንሠራበት ያተርፋል፤ ይበዛልናልም፡፡ ጸጋችሁን በማወቅ ስታገለግሉ እግዚአብሔር በእናንተ የሚሞላውን የዓለም ጎደሎ ታውቃላችሁ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ድርሻችሁን ለመወጣት ጸጋችሁን ማወቅና ማገልገል ይጠበቅባችኋል፡፡

## ማጠቃለያ

የጸጋ ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ ሰጭው መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ጸጋዎቻችን አንዱን እግዚአብሔርን ማክበሪያና ሰዎችን ማገልገያ እንጂ የልዩነት ምክንያት አይደሉም፡፡ በአንዱ መንፈስ አንድ አካል መሆናችንን በማሰብ ጸጋችንን አውቀን በጸጋችን በማገልገል ክብርን እንድንወርስ እንትጋ፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ወጣቶች ጸጋቸውን እንዲገልጡ ያበረታቷቸው፡፡

### *ጥያቄዎች*

- የጸጋ ስጦታዎች ምን ምን ናቸው?
- ጸጋን የሚሰጠው ማን ነው?
- ጸጋ የሚሰጥበት ዓላማ ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የዮሐንስ ራእይ (አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የራእየ ዮሐንስን አጠቃላይ ይዘት ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት . . . ጆሮ ያለው ይስማ . . ." ራእይ ፫÷፳፪፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ራእይ ፩፣፪፣፫

## መግቢያ

ራእይ ሳይታወቅ የቀረውንና ሊታወቅ የተገባውን፤ ያለውንና የሚመጣውን እግዚአብሔር የሚገልጥበት የየዘመናቱ መስታወት ነው፡፡ ለዮሐንስ ወንጌላዊ ክርስቶስ ኢየሱስ በመልአኩ በኩል የገለጠው ምስጢር ራእየ ዮሐንስ (የዮሐንስ ራእይ) ተብሏል፡፡ ራእየ ዮሐንስ ፍጻሜያችን የሚያብራራ፤ መድረሻችንን የሚያሳውቅ በሐዲስ ኪዳን ብቸኛው የትንቢት መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ውብ መልኩና አስፈሪ ግርማው የታየበት መጽሐፍ ነው፡፡ አሮጌውን አሳልፎ ሁሉን አዲስ ሊያደርግ ያሰበውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይገልጣል፡፡ በዮሐንስ ራእይ የነበረው ያለውንና የሚመጣው መለከታዊ ድርጊት ተብራርቶበታል፡፡ እግዚአብሔር ለትውልድ ያለው መልእክትም ተሰብኮበታል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የዮሐንስ ራእይ ሃያ ሁለት ምዕራፎች ያሉት የትንቢት መጽሐፍ ነው፡፡ መጨረሻውን ለሚናፍቅ አማኝ ተስፋውን የሚያነብበት የሕይወት ገጽ ነው፡፡

1. **የመጽሐፉ ጸሐፊ፡-** ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ (አቡቀለምሲስ) ነው፡፡

www.zeorthodox.org

2. **ራእዩን ያየበት ቦታ፡-** ከኤፌሶን በስተደቡብ 80 ኪ.ሜ ርቀት በምትገኘው በፍጥሞ ደሴት ነው፡፡ ራእ. ፩÷፲፡፡

3. **ራእዩን ያየበት ዘመን፡-** ከ95-100 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ነው፡፡

4. **የመጽሐፉ ባሕርይ፡-** በብዙ ምሳሌዎች ፣ትንቢቶችና ምስጢራት የተሞላ ነው፡፡ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ከትንቢተ ዳንኤልና ሕዝቅኤል ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሚያስፈሩ አውሬዎችና ምስጢራዊ ቁጥሮች አሉበት፡፡

5. **የመጽሐፉ ጠቀሜታ፡-** ተስፋ፣ ድል፣ ምስጋና፣ የእምነት ፍሬ፣ መጪው ሕይወትና ደስታ የተብራራበት መጽሐፍ በመሆኑ

ለአማኞች የእምነት ጥንካሬ ይሰጣል፡፡ ፍጻሜያችንንም እንድናውቅ ያደርጋል፡፡ ከክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ያለበትን ክብር ይገልጣል፡፡ የወንድሞች ከሳሽ ዲያብሎስ መጣሉን ስለሚያበስር መንገዳችን ሰላም እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

**6. የመጽሐፉ ይዘት፡-** መጽሐፉ የክርስቶስን ግርማና የአማኞችን ድል በስፋት ይተርካል፡፡

ምዕራፍ ፩፡- **የራእዩ ተመልካች ሁኔታ፣ የራእዩ አሰጣጥና** የክርስቶስ መልክ ተንጸባርቆበታል፡፡

ምዕራፍ ፪ እና ፫፡ **የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ጉዞ፣ የተገኘባቸው** ነቀፋ፤ የሚስተካከሉበት ምክርና የሚጠብቃቸው በረከት (ቅጣት) ተገልጾባቸዋል፡፡

***6.1. የክርስቶስ መልክ***

- በሰባቱ መቅረዞች መካከል የሰውን ልጅ የሚመስለውን አየሁ➡**በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ክርስቶስን** ማየቱን ያሳያል፡፡
- እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር፡፡ ➡ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት እንደሆነ ይገልጻል፡፡
- ራሱና የራሱ ጠጉርም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር፤ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፡፡ ➡**ክርስቶስ ዘመን የማይቆጠርለት ጊዜን የማያስረጅ** የዘላለም አምላክ እንደሆነ ያስረዳል፡፡
- ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ፡፡ ➡**ክርስቶስ ኅሊና የሚያራቁት ውስጥን የሚያነብ** ሐሳብን የሚመረምር ሁሉን የሚያይ አምላክ መሆኑን ያብራራል፡፡
- እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስይ መስሎ ነበር፡፡➡ ክርስቶስ በጽድቅ የሚፈርድ ጌታ መሆኑን ይናገራል፡፡
- ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበር፡፡ ➡ ሥልጣኑን ያሳያል፡፡
- በቀኝ እጅ ሰባት ከዋክብት ነበሩት፡፡ ➡**በሥልጣኑ ሰባቱን አለቆች (የአብያተ ክርስቲያናቱን** አስተዳደሪዎች) እንደያዘ ያሳያል፡፡
- ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ወጣ፡፡ ➡**ቃሉን ያሳያል፡፡ ዕብ. ፬÷፲፪**
- ፊቱም በኃይል እንደሚበራ ፀሐይ ነበረ፡፡ ➡**ግርማውን፣ ልዕልናውን ንጽሕናውን ያመለክታል፡፡**

www.zeorthodox.org

**6.2. የሰባቱ መቅረዞች (አብያተ ክርስቲያናት ጉዞ)**

1. ኤፌሶን ራእይ ፪÷፩-፯ የቀደመ ፍቅሯን የተወች መቅደስ ናት

2. ሳምርኔስ. . . . ራእይ ፪÷፰-፲፩ . . . . በመከራ ጸንታ የቆመች መቅደስ ናት፡፡

3. ጴርጋሞን . . . . ራእይ ፪÷፲፪-፲፯. . . . **ከዓለም ጋር የተዛመደች መቅደስ** ናት፡፡

4. ትያጥሮን . . . . ራእይ ፪÷፲፰-፳፱ . . . . በኤልዛቤል መንፈስ የደነዘዘች መቅደስ ናት፡፡

5. ሰርደስ . . . . ራእይ ፫÷፩-፮ . . . . ስም ያላት ሥራ የሌላት ሙታን ጉባኤ የመሰለች መቅደስ ናት፡፡

6. ፊልድልፊያ . . . . ራእይ ፫÷፯-፲፫ . . . . በተከፈተው በር ታምና የምታገለግል መቅደስ ናት፡፡

7. ሎዶቅያ . . . . ራእይ ፫÷፲፬-፳፪ . . . . ለዘብተኛ ሆና ንጉሧን በደጅ ያቆመች መቅደስ ናት፡፡

**ማስታወሻ፡-** ስምርኔስና ፊልድልፊያ ነቀፋ ያልተገኘባቸው መቅደሶች ናቸው፡፡ ሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት በዮሐንስ ዘመን በታናሿ እስያ (የአሁኗ ቱርክ) የነበሩ ሲሆን እስከ ምፅአት የሚነሡትን የአብያተ ክርስቲያናት ሥፍራ ዘመንና መልክ ያሳያሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የዮሐንስ ራእይ የዘመን ፍጻሜ መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ ተስፋችንን እና ድላችንን የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ ለአማኞች ጥያቄ መልስ፤ ለችግራቸውም መፍትሔ ነው፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ ዮሐንስ ራእይ ከ፩ **እስከ** ፫ ያሉትን ምዕራፎች እንዲያጠኑ ይጋብዙአቸው፡፡

### *ጥያቄዎች*

www.zeorthodox.org

- ☞ ራእይ ዮሐንስን የጻፈው ማን ነው?
- ☞ ራእይ ዮሐንስ ምን ዓይነት መጽሐፍ ነው ስለ መጽሐፉ ምንነት፣ አገልግሎት እና ጠቀሜታ አብራሩ፡፡
- ☞ ከራእየ ዮሐንስ ይዘት የመጀመሪያዎቹን ሦስት ምዕራፎች ጭብጥ(ምንነት) ግለጹ፡፡

# የዮሐንስ ራእዩ (ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች የዮሐንስ ራእይን አጠቃላይ ይዘት ያውቃሉ፤ ስለ ዮሐንስ ራእይ ይዘት፣ ጭብጥ እና መልእክት ይገልጻሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ" ራእይ ፳፩÷፭፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ራእይ ፬-፳፪

## መግቢያ

ራእየ ዮሐንስ ምስሎችና ምልክቶች የበዙበት መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ የራእይ መጽሐፍ ፯ ቁጥር ሃምሳ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ሰባቱ ብፁዓን፣ ሰባቱ ምልክቶች፣ ሰባቱ መቅሰፍቶች፣ ሰባቱ ዘውዶች፣ ሰባቱ ተራሮች፣ ሰባቱ ማኅተሞች፣ ሰባቱ ነገሥታና እና ሌሎችም የተጠቀሱ ሲሆን ሰባት ቁጥር የሚወክለው ፍጹምነትን ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለውን አጠቃላይ ይዘት በዛሬው ትምህርታችን እንመለከታለን፡፡

ምዕራፍ ፬-፭፡- ኢየሱስ ክርስቶስ በበግ ተመስሎ በዙፋኑ መቀመጡንና ማኅተሙን ሊፈታ የተገባው የይሁዳ አንበሳ እንደሆነ ይነግረናል፡፡

ምዕራፍ ፮-፰፡- ሰባቱ ማኅተሞች፤

ምዕራፍ ፱-፲፩፡- ሰባቱ መለከቶች፤

ምዕራፍ ፲፪፡- ሴቲቱና ዘንዶው፤

ምዕራፍ ፲፫፡- ሁለቱ አውሬዎች፤

ምዕራፍ ፲፬÷፩-፭፡- በጉና ምርጦቹ፤

ምዕራፍ ፲፬÷፮-፳፡- የአጨዳ ሰዓት፤

ምዕራፍ ፲፯-፲፱÷፭፡ የታላቋ ባቢሎን ውድቀት፤

ምዕራፍ ፲፱÷፮-፲፡- የበጉ ሰርግ፤

ምዕራፍ ፲፱÷፲፩-፳፩፡-፡ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት፤

ምዕራፍ ፳÷፩-፮፡- ሺሕ ዓመት፤

ምዕራፍ ፳÷፯-፲፡- የሰይጣን መጣል፤

ምዕራፍ ፳፥፲፩-፲፭፦ ታላቁ ፍርድ፤

ምዕራፍ ፳፩፥፩-፳፪፥፭፡ **የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም መገለጥ**

ምዕራፍ ፳፪፥፮-፳፩፦ የመደምደሚያ ቃል (የክርስቶስ ዳግሞ መምጣት መናፈቅ)፤

የዮሐንስ ራእይ በበረከት ቃል የተጀመረ በቡራኬም የተደመደመ የራእይ መጽሐፍ ነው፡፡ የዮሐንስ ራእይ ወደፊት በትርጓሜ የምትማሩት የሕይወት መጽሐፍ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የዮሐንስ ራእይ የእግዚአብሔርን የዘላለም ምክር ይገልጣል፡፡ እንባን ሁሉ እንደሚያብስና ሁሉን አዲስ አድርጎ እንደሚያወርሰን ይመሰክራል፡፡ የዮሐንስ ራእይ የድል አድራጊዎች ምስጋና የተመዘገበበት መጽሐፍ ነው፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ወጣቶቹ ራእየ ዮሐንስንና ትንቢተ ዳንኤልን እንዲያነጻጽሩ ያድርጉ፡፡
- መምህር ተማሪዎችዎ ስለ ዮሐንስ ራእይ በተማሩት መሠረት አጠቃላይ ይዘቱን፤ የራእዩን ጭብጥና መልእክት የሚገልጽ ጽሑፍ (በአጭሩ) አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወጣቶች ተማሪዎች ስለ ሰሙነ ሕማማት ያውቃሉ፤ የክርስቶስን መከራ ያስባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" ፩ጴጥ. ፪÷፳፭፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ማቴ ፳፺ እና ‹‹ግብረ ሕማማት››

## መግቢያ

‹‹ሰሙነ ሕማማት›› ማለት የመከራና የሕመም ሰሞን (ሳምንት) ማለት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን በልዩ ሁኔታ ከሚታዩትና ከሚታሰቡት ሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ጊዜያት አንዱ ሰሙነ ሕማማት ነው፡፡ ይህ ጊዜ የዐቢይ ጾም የመጨረሻው ሳምንት ይባላል፡፡ የክርስቶስ መከራ መስቀሉ የሚነገርበት ሳምንት ነው፡፡ ይህ ሳምንት በትንሣኤ ዋዜማ (ከሆሳዕና እስከ ቀዳም ስዑር) ያለው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ሳምንት ግብረ ሕማማት ይነበባል፤ ዳዊት ይስተዛዘላል፤ ስግደት ይሰገዳል፤ ነገረ መስቀሉ ይተረካል፡፡ ሰሙነ ሕማማት የብሉይ ኪዳንን ዘመን ያስታውሰናል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**1. እሑድ፡-** ሆሳዕና

‹‹ሆሳዕና›› ማለት ‹‹መድኃኒት›› ማለት ነው፡፡ ጌታ ከቤተ ፋጌ በአህያ ውርንጭላ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ ይታሰብበታል፡፡ ማቴ.፳፩÷፩-፲፫፡፡ **የክርስቶስ ትሕትና፣ የኢየሩሳሌም ለስላሟ** የመጣውን አለማወቋና የሕዝቡ በጎ አቀባበል ይሰበካል፡፡

**2. ሰኞ፡-** በዚህ ዕለት ጌታ ሁለት ነገሮችን አድርጓል፡፡

www.zeorthodox.org

2.1. ፍሬ ያልተገኘባትን በለስ ረግሟል፡፡ በለስ የእስራኤል ዘሥጋን የደረቀ ማንነት ያመለክታል፡፡ ማቴ. ፳፩÷፲፱፡፡ **ፍሬ አልባ ሕይወት እየመሩ ለክብሩ የሚመጥን** ማንነት እንዳጣባቸው ይገልጻል፡፡ ክርስቶስ አንድ ቀን ወደ እኛ ይመጣል፤ ፍሬ አፍርተን ካልጠበቅነው ይቀጣናል፡፡

2.2. በቤተ መቅደሱ የሥጋ ገበያ የሚገበያዩትን ገሥጹ፡፡ ቤቱ የሽፍቶች ማደሪያ እንዳልሆነ በመግለጽ አባረራቸው፡፡ ልባችን የኢጋንንት መናኸሪያ እንዳይሆን ባለቤቱ እግዚአብሔር ሊነግሥበት ይገባል፡፡ ማቴ. ፳፩÷፲፪-፲፫፡፡

**3. ማክሰኞ፡-** በዚህ ዕለት ጌታ ስለ ሥልጣኑ ተጠየቀ፡፡ የካህናት አለቆች "በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንስ

ሥልጣን ማን ሰጠህ?" አሉት፡፡ ጌታም ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ፡፡ እንዲህ በማለት፡- "እኔ እምጠይቃችሁን ብትነግሩኝ እኔም እነግራችኋለሁ፤ የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነበረች? ከሰማይ ወይስ ከምድር?" አላቸው፡፡ እነርሱም እርስ በርሳቸው "ከሰማይ ብንል ስለምን አላመናችሁበትም ይለናል፡፡ ከምድር ብንል ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ ያዩታልና ሕዝቡን እንፈራለን" አሉ፡፡ ለጌታም "አናውቅም" አሉት፡፡ እርሱም "እኔም በምን ሥልጣን እንዳደርግ አልነግራችሁም፡፡" አላቸው፡፡ ማቴ. ፳፩÷፳፫-፳፯

**4. ረቡዕ፡-** በዚህ ዕለት ይሁዳ ከአይሁድ ገንዘብ ለመቀበል ተስማማ፡፡ ሲነሃድሪን የተባለ ሰባ ሁለት አባላት ያሉት የአይሁድ ሸንጎ ክርስቶስን ለመስቀል መከረ፡፡ ማቴ. ፳፮÷፩-፲፮፡፡

**5. ሐሙስ፡-** ይህ ሐሙስ አረንጓዴው ሐሙስ፣ ጸሎተ ሐሙስ፣ ኅፅበተ እግር ሐሙስ፣ ምሴተ ሐሙስ፣ የነጻነት ሐሙስና የአዲስ ኪዳኑ ሐሙስ እየተባለ ይጠራል፡፡ በዚህ ዕለት ጌታ የመጨረሻውን ራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆርሷል፤ የቁርባን ሥርዓትን ሠርቷል፤ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧል፡፡ ዮሐ. ፲፫÷፩-፳፡፡ **ማቴ. ፳፮÷፳፮-፳፱፡፡**

**6. ዓርብ፡-** ይህ ዓርብ መልካሙ ዓርብ ተብሎ ይጠራል፡፡ ጌታ ዳግም የፈጠረን፤ በሞቱ ሞትን የሻረልን በዚህ ዕለት ነው፡፡ መልካሙ ዓርብ የተባለው ነጻነታችን የታወጀበት ዕለት ስለሆነ ነው፡፡ ማቴ. ፳፯÷፩-፷፮፡፡

**7. ቅዳሜ፡-** ቀዳም ስዑር ጌታ በመቃብር ያደረበትና የዋለበት ዕለት ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱ ሙሽራው ስለተለያቸው የጾሙበት ዕለት ነው፡፡ እኛም በአክፍሎት (በጾም) የምንቆይበት ዕለት ነው፡ በዚህ ዕለት ካህናት በቤተ መቅደስ "ገብረ ሰላመ በመስቀሉ" (በመስቀሉ ሰላምን አደረገ፡፡) እያሉ ቀጤማ ያድላሉ፡፡ የኃጢአት ባሕር መድረቁን ይሰብካሉ፡፡

## ማጠቃለያ

ሰሙነ ሕማማት ደዌን የሚያውቅ የሕማም ሰው ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ መተላለፍ መቁሰሉን የምናስብበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ሳምንት የየዕለቱ አምልኮ በሰዓት ተከፋፍሎ ምንባብና ስግደት ይከናወናል፡፡

## ተግባር

- መምህር ለተማሪዎችዎ የሰሙነ ሕማማትን ሥርዓተ አምልኮ በቤተ ክርስቲያናችን ሲፈጸም የሚያሳዩ፤ የሚያስታውሱ በቪዲዮ የተቀረጹ ፊልሞችን ለወጣቶች ያሣያቸው፡፡ ከሳምንቱ ሥርዓተ አምልኮ ምን እንደተማሩም (እንደተገነዘቡ) ይጠይቋቸው፡፡

www.zoorthodox.org

***ጥያቄዎች***

- ☞ ሰሙነ ሕማማት ማለት ምን ማለት ነው? በቤተ ክርስቲያናችን ሰሙነ ሕማማት በመባል ሥርዓተ አምልኮ የሚፈጸምበት የሚታሰብበት ጊዜ መቼ ነው?
- ☞ በሰሙነ ሕማማት ወቅት በቤተ ክርስቲያን የሚደረጉት ምን ምን ናቸው?
- ☞ በሰሙነ ሕማማት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ባሉት በእያንዳንዱ ቀናት የተከናወኑትን ተግባራት በተማራችሁት መሠረት ግለጹ።

www.zeorthodox.org

# የድንግል ማርያም ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የድንግል ማርያምን ምሳሌዎች ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** “ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡፡” ኢሳ. ፯÷፲፬፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃስ ፩÷፳፮-፶፮፣ ማቴ. ፩÷፳-፳፫ እና ቅዳሴ ማርያም

## መግቢያ

ምሳሌ ማለት የመንፈሳዊ እውነት መግለጫ ማለት ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብዙ ምሳሌዎች አሏት፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የተወሰኑትን እናጠናለን፡፡ “ድንግል ሆይ በማንና በምን እንመስልሻለን?” አባ ሕርያቆስ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊና አባ ሕርያቆስ (ዘብህንሳ) እመቤታችንን በብሉይ ኪዳን በነበሩ መንፈሳዊ ነገሮች መስለዋታል፡፡ አባ ሕርያቆስ “ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋ አንቺ ነሽ፡፡ በግፍ የተገደለ የአቤል የውሃቱ አንቺ ነሽ፡፡ የሴት ቸርነት፣ የኖኅ መርከብ፣ የአብርሃም ድንኳን፣ የይስሐቅ መዓዛ፣ የያዕቆብ መሰላል፣ የሙሴ ጽላት፣ ሐመልማላዊት ዕፅ (ዕፀ ጳጦስ)፣ የአሮን በትር፣ የኢያሱ የምስክሩ ሐውልት፣ የጌዴዎን ፀምር፣ የሳሙኤል የሽቱ ሙዳይ፣ የእሴይ ሥር፣ የአሚናዳብ ሰረገላ፣ የኤልያስ መሶበ ወርቅ፣ የዳዊት መሰንቆ፣ የሰሎሞን አክሊል፣ የውኃ ጉድጓድ፣ የዕንባቆም ተራራ፣ የምሥራቅ ደጅ፣ ኤፍራታ፣ የሲሎንዲስ ዕፅ፣ የናሆም መድኃኒት አንቺ ነሽ” በማለት መስሏታል፡፡

ቅዱስ ኤፍሬም ደግሞ “የመጀመሪያይቱ ምድር፣ የዮሴፍ መዝገብ፣ የምሥራቅ በር፣ የአሮን በትር፣ መሶበ ወርቅ፣ የሙሴ ዕፅ. . . .” በማለት ይጠራታል፡፡

www.zeorthodox.org

## 1. የኖኅ መርከብ

የኖኅ መርከብ የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ የኖኅ መርከብ ሦስት ክፍል ነበራት፡፡ የእመቤታችን ንጽሕና ምሳሌ ነው፡፡ ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስና ንጽሐ ልቡና እንዳላት ያመለክታል፡፡ ኖኅ የጌታ (የልጇ) ምሳሌ ነው፡፡ ኖኅ በገዛ እጁ ወደሠራው መርከብ እንደገባ ሁሉ ጌታም የፈጠራትን እናቱ አደረጋት፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ “ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው፤ እርሱም የፈጠረውን ሥጋ ነሣ” ያለው ለዚህ ነው፡፡ ዘፍ. ፮÷፲፫-፳፬፡፡

### 2. የያዕቆብ መሰላል

ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ በላይዋ ዙፋን ተነድፎባት በዚያ ላይ ንጉሥ ተቀምጦባት በፍኖተ ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ፡፡ መሰላል እመቤታችን፤ የተንተራሰው ድንጋይ የትንቢተ ነቢያት፤ ምሳሌ ነው፡፡ ጌታ ከእመቤታችን ሰው ከሆነ በኋላ መላእክት ለምስጋና ሲወጡና ሲወርዱ ታይተዋልና፡፡ ዙፋን የእመቤታችን ማኅፀን ምሳሌ ሲሆን በዙፋኑ የተቀመጠው (በማኅፀኗ ያደረው) ጌታ ነው፡፡ ዘፍ. ፳፰÷ ፲፪፣፲፫፡፡

### 3. የሙሴ ጽላት

የሙሴ ጽላት በውጭና በውስጥ በወርቅ የተለበጠች ናት፤ የእመቤታችን ንጽሕና ምሳሌ ናት፡፡ ታቦት የእመቤታችን ጽላት፤ የልጇ ብለው ሊቃውንቱ ምስጢር ይስባሉ፡፡ ዘጸ. ፳፭÷፲-፳፪፡፡

### 4. ዕፀ ጳጦስ

ሙሴ በሲና ተራራ ያያት ዕፅ አንቺ ነሽ፡፡ ሙሴ ሃመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ነበልባሉ ሃመልማሉን ሳያቃጥለው አየ፡፡ ድንግልም ማኅደረ መለኮት ስትሆን የመለኮቱ እሳትነት አላቃጠላትምና፡፡ ሰማይና ምድር የማይችሉትን ችላዋለችና፡፡ ዘጸ. ፫÷፪፡፡

### 5. የአሮን በትር

የአሮን በትር ውኃ ሳያጠጧት እንደለመለመችና ፍሬ እንዳስገኘት ሁሉ፤ እመቤታችንም ያለወንድ ዘር በድንግልና የሚበላውን የሕይወት ፍሬ አማኑኤልን ወልዳልናለችና በአሮን በትር ትመሰላለች፡፡ ዘኍ. ፲፯÷፰፡፡

### 6. የኤልያስ መሶበ ወርቅ

ኤልያስ በራበው ጊዜ እግዚአብሔር በመልአኩ መገበው፡፡ የኤልያስ መና የጌታ ምሳሌ ሲሆን የኅብስቱ መሶበ ወርቅ የማርያም ምሳሌ ናት፡፡ ኤልያስ የምእመናን ኅብስት የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ነው፡፡ ፩ነገ. ፲፱÷፮፡፡

### 7. የምሥራቅ ደጅ

ሕዝቅኤል በራእይ ያየሽ የምሥራቅ ደጅ አንቺ ነሽ፡፡ ቀይ ኅልማሳ የጌታ ምሳሌ ሲሆን ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት መውጣቱ ጌታ ሲወለድ ማኅተመ ድንግልናዋን እንዳላጠፋ ያሳያል፡፡ ሕዝ. ፵፬÷፩-፫፡፡

www.zeorthodox.org

### 8. የመጀመሪያይቱ ምድር

የመጀመሪያይቱ ምድር ዘር ሳይዘራባት ገበሬ ሳይደክምባት ፍሬ እንዳስገኘች ሁሉ እመቤታችንም ያለ ወንድ ዘር በድንግልና የሕይወትን ፍሬ (ምግበ ነፍስ) ወልዳለች፡፡

### 9. የጌዴዎን ፀምር

ጌድዎን ከመልአኩ ምልክት በፈለገ ጊዜ ፀምርና ጠሉ ተስማምቶለታል፡፡ ፀምር የእመቤታችን ጠል የጌታ ምሳሌ ነው፡፡ ጠል

ከፀምር መውረዱ ጌታ በእመቤታችን የማደሩ ምሳሌ ነው፡፡ መሳ. ፮÷፴፮-፵፡፡

### 10. የኤልሳዕ ማሰሮ

የኤልሳዕ አዲሲቱ ማሰሮ አንቺ ነሽ፡፡ ኤልሳዕ በአዲስ ማሰሮ ጨው ጨምሮ ውኃውን ፈውሷል፡፡ የሚያስጨነግፈው የኢያሪኮ መራራ ውኃ የኃጢአት ምሳሌ ነው፡፡ ጨው የጌታ ምሳል ነው፤ መራራውን ሕይወት አጣፍጧልና፡፡ አዲሲቱ ማሰሮ የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ የኢያሪኮ ሰዎች የምእመናን ምሳሌዎች ናቸው፡፡ **፪ነገ. ፪÷፳**፡፡

እመቤታችን ማርያምን ሰሎሞን "የተቆለፈ ገነት፤ የታተመች ፈሳሽ፤ ከሊባኖስ የሚፈስ ወንዝ ርግቤ መደምደሚያዬ" ይላታል፡፡ መኃ. ፬÷፲፪፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በአርጋኖን "የተከለለች የአትክልት ስፍራ (የታጠረች ተክል)፤ የሎሚ እንጨት፤ ንጽሕት አንበሳ፤ የመድኃኒት ጉድጓድ" ይላታል፡፡

## ማጠቃለያ

ሊቃውንቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በብዙ ምሳሌና አምሳል መስለዋታል፡፡ አባ ሕርያቆስ "በምንና በማን እንመስልሻለን?" **በማለት ምሳሌዋ ብዙ መሆኑንም መስክሯል**፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ ያልተብራሩ ምሳሌዎችን መጻሕፍትን በመጠቀም እንዲያጠኑ ይጠቁሙአቸው፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

1. የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን አባቶች እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን በብዙ ምሳሌ መስለዋታል፡፡ ከእነዚህ ቅዱሳን አባቶች መካከል፦

   ሀ. አባ ሕርያቆስ (ዘብህንሳ)

   ለ. ቅዱስ ኤፍሬም (ሶርያዊ) ስለ እመቤታችን የገለጹትን ምሳሌዎች ጥቀሱ፡፡

2. የ‹‹ኖኅ መርከብ›› የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡ በተማራችሁት መሠረት ምሳሌውን ግለጹ፡፡

3. እመቤታችን በ‹‹ያዕቆብ መሰላል›› ትመሰላለች፡፡ አብራሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ቀናተኛው ነህምያ (አንድ)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** *ተማሪዎች ስለ ነህምያ ታሪክና ሥራ ያውቃሉ፤ ነህምያን አርአያ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ቀናዒ ታማኝና በጎ አገልጋይ ይሆናሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡*

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** *"መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና* የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ" ነህ. ፪÷፲፯፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** *መጽሐፈ ነህምያ ፩-፬*

## መግቢያ

ነህምያ የፋርስ ንጉሥ የነበረው አርጤክሰስ ጠጅ አሳላፊ የነበረ አይሁዳዊ ነው፡፡ ነህ. ፩÷፪፡፡ **የኢየሩሳሌምን ቅጥር** ***ለመሥራት*** ንጉሡን ያስፈቀደ በሃምሳ ሁለት ቀናት ቅጥርዋን ያሠራ ብርቱ ሰው ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**1. የሕዝቡ መከራ በፋርስ ምርኮ፡-** የፋርሱ ንጉሥ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሰብሮ ሕዝቡን ማረካቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ወደ ፋርስ በባርነት ተወሰዱ፡፡ ነህምያ ከምርኮኞቹ መካከል አንዱ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም ሰለቀሩት ሲጠይቅ ሕዝቡ መከራ እንደጸናበት፣ የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደፈረሰና በሮቿም በእሳት እንደተቃጠሉ ሰማ፡፡ ነህምያ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ "ሙሴ የገባኸውን ቃል አስብ፡፡ በታላቅ ኃይልና በብረቱ እጅህ የተቤዠሃቸው ሕዝብህ ናቸው፡፡ ጌታ ሆይ ጆሮህ የባሪያህን ጸሎት፣ ስምህንም ይፈሩ ዘንድ የሚወድዱትን የባሪያዎች ጸሎት ያድምጥ፡፡ ዛሬም ለባሪያህ አከናውንለት" አለ፡፡ ነህ. ፩÷፩-፲፩፡፡

www.zoorthodox.org

**2. ነህምያ ከንጉሡ ጋር ያደረገው ውይይት፡-** ነህምያ ተጎሳቁሎ በንጉሡ ፊት ቆመ፡፡ ንጉሡም "ሳትታመም ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብህ ሐዘን ነው፡፡" አለው፡፡ ነህምያም "ንጉሥ ሺሕ ዓመት ንገሥ የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና ፊቴ ስለምን አይዘን?" አለ፡፡ ንጉሥ ፈቀደለት ነህምያም ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ፡፡ ነህ. ፪÷፩-፰፡፡

**3. የጠላት ወሬ፡-** ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ደረሰ፡፡ ወገኖቹን ጠራ፡፡ "ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ" አላቸው፡፡ ሰንባላጥ፣ ጦቢያና ጌሳም በንቀት ሳቁበት፡፡ "በእውኑ በንጉሥ ላይ ትሸፍታላችሁን?" አሉ፡፡ ነህምያ ግን "የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፤ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን" አላቸው፡፡ ነህ. ፪÷፱-፳፡፡

**4. የቅጥሩ መሠራት፡-** ነህምያ እግዚአብሔር ምኞቱን ፈጸመለት፤ ሥራውን አከናወነለት፡፡ የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደገና

ተሠራ፡፡ የነህምያ መንፈሳዊ ቅናት መልስ አገኘ፡፡ የኢየሩሳሌም ቅጥር ተሠርቶ በተጠናቀቀ ጊዜ ሰንባላጥ ተበሳጨ፡፡ በሰማርያ ሠራዊት ፊት "እነዚህ ደካሞች አይሁድ የሚሠሩትን አይታችኋል?" አለ፡፡ ጦብያም "በድንጋይ በሚሠሩት ቅጥራቸው ላይ ቀበሮ ቢመጣበት ያፈርሰዋል" አለ፡፡ ነህምያም "አምላካችን ሆይ ተንቀናልና ስማ ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው በምርኮ አገር ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው፡፡ በደላቸውንም አትክደን፡፡" አለ፡፡ የሕዝቡ ልብ ለሥራው ጨከነ፡፡ ጠላቶች ግን ቅጥሩን ሊያፈርሱ ጦርነት ዐወጁ፡፡ ነህ. ፬÷፩-፲፬፡፡

## ማጠቃለያ

ነህምያ የሃገር ፍቅር የነበረው ሰው ስለነበር ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ አለቀሰ፡፡ ንጉሡን አስፈቅዶ ከወገኑ ጋር ቅጥሩን ሠራ፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ወጣቶች ከባለታሪኩ ምን እንደተማሩ እና የተገነዘቡትን እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡

## *ጥያቄዎች*

- ነህምያ ማን ነው?
- ነህምያ ወደ ፋርስ የሄደው በምን ምክንያት ነበር?
- ነህምያ በፋርስ በነበረበት ጊዜ ስለ ኢየሩሳሌም ሁኔታ ጠይቆ የተረዳው ምን ነበር? በሰማው ነገር ምን ሆነ? ምን ለማድረግስ አሰበ?
- ነህምያ ኢየሩሳሌም ሄዶ ወገኖቹን ጠርቶ ምን አላቸው?
- ነህምያ ወገኖቹን ሲያናግራቸው ተቃውመውት በንቀት የሳቁበት እነማን ናቸው?
- ነህምያስ ምን አላቸው?
- ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር የሠራው በምን ያህል ጊዜ ነው?

www.zeorthodox.org

# ቀናተኛው ነህምያ (ሁለት)

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የነህምያን መልካም ሥራና አርአያነት በመከተል በአንድነትና በመተባበር መልካም ሥራ ለመሥራት የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለመቅረፍ ይነሣሣሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ዛሬ ለጌታችን የተቀደሰ ቀን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ" ነህ. ፰÷፲፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ነህምያ ፩-፲፫

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

**1. የሕዝቡ በአንድነት መሥራት፡-** የጠላት ትንኮሳ የሕዝቡን ልብ አስጨከነ፡፡ ሕዝቡ በቁጭት ተነሣሥተው ለሥራው ክንዳቸው በረታ፡፡ ግማሾቹ ቅጥሩን ይሠራሉ፡፡ ሌሎቹ አፍራሾችን ይከላከላሉ፡፡ መከራ ሲካፈሉት ይቀላልና መንገዱ ተቃና፡፡ ነህምያ በይሁዳ ምድር አለቃ ሆነ፡፡ ነህ. ፬÷፲፮ - ፮÷፲፱፡፡

**2. የሰንባላጥ ተንኮል፡-** ሰንባላጥና ጦቢያ በነህምያ ክፉ ሊያደርጉበት ቀጠሩት፡፡ ነህምያ ግን የጠላትን መልእክት ችላ አለ፡፡ ብዙ አስፈራሩት፤ ነህምያ ግን "አምላክ ሆይ እጄን አበርታ" ብሎ ጸለየ፡፡ ሰንበላጥና ጦቢያ ነህምያ እምቢ እንዳላቸው ባወቁ ጊዜ ሸማያ የተባለውን ነቢይ ገንዘብ ከፍለው የሐሰት ትንቢት አናገሩ፡፡ ነህምያ ግን ውሸት እንደሆነ ዐወቀ፡፡ በሃምሳ ሁለት ቀናት የቅጥሩ ሥራ ተጠናቀቀ፡፡ ነህ. ፯÷፩-፲፱፡፡

- የካህናት ሎሌዎች ዝርዝር ከምዕራፍ ፯-፲፩ ተመዝግቧል፡፡ መጽሐፍም በነህምያ ስም የተጠራ ነበር፡፡ ነህምያ ወደ ንጉሡ ተመለሰ፡፡ ነህምያና ዕዝራ አብረው የኢየሩሳሌምን ቅጥር ይሠሩ ነበር፡፡ ነህምያ የእምነትና የጸሎት ሰው ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

**3. የሕጉ መጽሐፍ መነበብ፡-** የእስራኤል ልጆች ሁሉ ተሰበሰቡ፡፡ ጸሐፊው ዕዝራ መጽሐፉን አወጣ፡፡ የሕጉንም መጽሐፍ አነበበላቸው፡፡ ሕዝቡም ንስሐ ገቡ፡፡ ቃል ኪዳናቸውንም አጸኑ፡፡ ነህምያ፣ ዕዝራና ሌዋውያኑ "ዛሬ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ቀን ነው፡፡ አታልቅሱ እንባም አታፍስሱ፡፡ ሂዱ ጣፋጩን ጠጡ፤ የሰባውንም ብሉ፡፡ የእግዚአብሔር ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ" አሏቸው፡፡ ቀጥለውም "ቀኑ የተቀደሰ ነውና ዝም በሉ" አሉ፡፡ ሕዝቡም እንዳሏቸው አደረጉ፡፡ የተነገረላቸውን ቃል አስተውለው ደስታን ሊያደርጉ ሄዱ፡፡ ነህ. ፰÷፩-፲፪፡፡

ነህምያ ከአሥራ ሁለት ዓመታት የኢየሩሳሌም አገልግሎት በኋላ ወደ ፋርስ ለጊዜያዊ ቆይታ ተመልሷል፡፡ ጠንካራ መሪ፣ ትጉህ ሠራተኛ፣ የጸሎትና የእምነት ሰው ስለነበር መልካም የሆነው ምኞቱና መሻቱ ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሳካለት፡፡

## ማጠቃለያ

ነህምያ ጠንካራ መሪ፣ ትጉህ ሠራተኛ፣ መካሪ አባት፣ ቀስቃሽ ጀግና፣ የጸሎትና የእምነት ሰው ነበር፡፡ ለቅጥረ ኢየሩሳሌም መሠራትና ለሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ነህምያን እንምሰለው፡፡

## ተግባር

☙ መምህር ለተማሪዎችዎ የነህምያን መልካም አርአያነት በመግለጽ ለበጎ ሥራ ያነሣሧቸው፡፡

## *ጥያቄዎች*

☞ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት በተነሣ ጊዜ የሰንበላጥና ጦቢያ ተንኮል ምን ነበር? በተለያየ ዘዴ ሲያስፈራሩት ነህምያ ምን አደረገ?

☞ ከነህምያ ታሪክ ምን ተማራችሁ? በአጭሩ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# ንዴት

**የትምህርቱ ዓላማ**:- ተማሪዎች ስለ ንዴት ምንነተና ጉዳት ይገነዘባሉ፤ ስሜታቸውን በመቆጣጠር የሚናደዱባቸውን እና የሚቆጡባቸውን ነገሮች እየለዩ ራሳቸውን(ስሜታቸውን) የሚገዙበትን ዕውቀት ያገኛሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**:- "ለቁጣ ችኩል አትሁን" መክብብ. ፯÷፱፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት**:- ኤፌ. ፬÷፴፩ እና ምሳሌ ፲፯÷፲፬

## መግቢያ

- ንዴት ምንድን ነው?
- ሰው ለምን ይናደዳል?
- ንዴትን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

## የሳምንቱ ትምህርት:-

ንዴት የከፋ ቁጣ ነው፤ በሚያጋጥሙን አሳዛኝ ክሥተቶች የሚፈጠር ከፍተኛ የጥላቻና የበቀል መንፈስ ነው፡፡ ንዴት የሕይወትን ሰላም ያደፈርሳል፡፡ ንዴታችንን ተቆጣጥረን በተረጋጋ መንፈስ ራሳችንን ካልመራን በከፋ መከራ ውስጥ የሚከትተን የሞት መንገድ ነው፡፡ በክፉ ቃላት ወይም በድብደባ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ንዴት ከክፉው የልብ መዝገብ መራራ ቃል እንዲወጣ የሚያደርግ የሥጋ ፍሬ ነው፡፡ የንዴት (የቁጣ) ሥሮች ኢፍትሐዊነት፣ ግጭት፣ አለመታገሥ፣ ስሜታዊነት፣ ያልተሳካ ምኞት፣ ክርክር፣ ምቀኝነትና መራርነት ናቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ንዴት መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝን የሥጋ ፍሬ ነው፡፡ ኤፌ. ፬÷፴፩፡፡ ንዴት ጥበብ የጎደላቸው ሰዎች ፍሬ ነው፡፡ ምሳ. ፲፱÷፲፩፡፡ ኃጢአት ነው፡፡ ንዴት ጠብና ደም መፋሰስን ያመጣል፡፡ ቁጣችን የማንቆጣጠረው ደረጃ መድረሱንም ያሳያል፡፡ ስለዚህ ንዴትን ሊያመጡ የሚችሉ ምክንያቶችን ማስወገድ አለብን፡፡

በትዕግሥት በፍቅር፣ በልበ ሰፊነት፣ በፍትሕ፣ ራስን በመግዛት፣ በየዋህነት፣ በሰላምና በሰከነ መንፈስ የሚኖር ሰው ቁጣውን መቆጣጠር ንዴቱንም ማቀዝቀዝ ይችላል፡፡ ለቁጣ መቸኮል፣ ስሜታችንን አለመግዛት በተዛባ ግምት ላይ ብቻ ተመሥርቶ ለውሳኔ

መፍጠን ለንዴት ያጋልጡናል፡፡ በተረጋጋ መንፈስ በጥበብና በማመዛዘን እየተመሩ ለእውነት መቆምና ለእውነት መሥዋዕት መሆን የነገሮችን ልክ ስለሚያሳውቅ ከንዴትና ከቁጣ ለመቆጠብ ይራዳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእኛ እንዲኖርና የመንፈስ ፍሬዎችን ለማፍራት እንድንችል መራርነትና ንዴትን፣ ቁጣ፣ ስድብንና ክፋትን ሁሉ ማስወገድ አለብን፡፡ የሚያሳዝኑት ኃጢአቶች ናቸውና፡፡ ኤፌ. ፬÷፴፪፡፡ **በይቅርታ መንፈስ፣ በርህራሄና በቸርነት** መመላለስ ይጠበቅብናል፡፡

ንዴት ጤናን ይጎዳል፤ ሌሎችን ያቆስላል፤ ለድንገተኛ ወንጀል፣ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን የሚጎዳ ለከፉ ሥራ ያጋልጣል፡፡ በዕለታዊ እንቅስቃሴዎቻችን የሚያጋጥሙንን ግጭቶች በተረጋጋና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት አለብን፡፡

# ማጠቃለያ

ንዴት ጥበብና ትዕግሥት ከጎደላቸው ሰዎች ይመነጫል፡፡ ንዴት ለቤዛ ቀን የታተምንበትን መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝን የሥጋ ፍሬ ነው፡፡ በልበ ሰፊነት፣ ራስን በመግዛትና በይቅርታ መንፈስ እንመላለስ፡፡

# ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ የሚናደዱባቸውን ምክንያቶች እና አጋጣሚዎች እንዲናገሩ በማድረግ የመፍትሔ ሐሳቦችን እያቀረቡ እንዲወያዩባቸው ያድርጉ፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ ንዴት ምንድ ነው?
- ☞ ሰው ለምን ይናደዳል?
- ☞ ንዴት የሚያስከትለው ጉዳት ምንድነው? በዝርዝር አብራሩ፡፡
- ☞ ንዴትን ለመቆጣጠር ምን ማድረግ አለብን?

www.zoorthodox.org

# ምስክርነት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ምስክርነት ያውቃሉ፤ የአምላካቸውን በጎነት ለዓለም ይነግራሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ ናችሁ፡፡" ፩ጴጥ. ፪÷፱፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ፩ዮሐ. ፩÷፩-፬፣ ሐዋ. ፫÷፴–፴፪ እና ሉቃ. ፳፬÷፵፰

## መግቢያ

ምስክርነት የምናውቀውን እውነት መናገር፤ ያየነውን መመስከር፤ በጎነቱን መንገር፤ ማዳኑን ማወጅ፤ ምሥራቹን ማውራት፤ ውለታውን መዘከር ነው፡፡ ምስክርነት በቃልም በሕይወትም ይገለጻል፡፡ ምስክርነት ልባችን ያመነበትን እውነት በአደባባይ የምናውጅበት ሕይወት ነው፡፡ ክርስትና የምስክርነት ሕይወት ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

"እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር አልተወምና" በሥጋውያን መካከል መንፈሳውያን ምስክሮች አሉት፡፡ እግዚአብሔር መልካምነቱን በእኛ የሕይወት አደባባይ ማሳየት ይፈልጋል፡፡ ፍጥረት ሁሉ ምስክሮቹ ናቸው፡፡ በሐዲስ ኪዳን "የጠራን የእርሱን በጎነት እንድንናገር መርጦናል" ምስክርነት የተጠራንበት ዓላማና የተመረጥንበት ራእይ ነው፡፡

ሰው በልቡ ያመነውን በአንደበቱ ሊመሰክር ይገባዋል፡፡ ሮሜ. ፲÷፲፡፡ **የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ** በመመስከር ሞትን ደፍረዋል፡፡ የመከራ ዶፍ የወረደባቸው ለስሙ ሕያዋን ምስክሮች ሆነው ስለቆሙ ነው፡፡ የትንሣኤው ምስክሮች የተባሉት ለዚህ ነው፡፡ ሐዋ. ፩÷፳፪፡፡ **ስለተደረገልን ነገር ምስጋና እና ምስክርነት** ይጠበቅብናል፡፡ ምስጋና ለእግዚአብሔር፤ ምስክርነት ደግሞ ለሰዎች እንሰጣለን፡፡

www.zeorthodox.org

ምስክርነት በአንደበት ብቻ ሳይሆን በኑሮም በተግባርም የሚገለጽ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መሆናችንን የምንመሰክረው በቃልም በተግባርም ነው፡፡ የአንደበታችን ዓዋጅ ለጆሮ፤ የሕይወታችን ሽታ ለልብ ይናገራል፡፡ በምድር ሳያፍር ስለክርስቶስ ማዳን የሚመሰክር በሰማይ ይመሰከርለታል፡፡ ራእ. ፫÷፮፡፡ **ምስክርነት ያላመኑትን ወደ እምነት**፤ በጨለማ ግዛት ያሉትን ወደ ብርሃን፤ በሞት ጥላ ያሉትን ወደ ሕይወት ያመጣል፡፡ እግዚአብሔርን የምናሳይበት አደባባይ ነው፡፡ ምስክርነት ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና እውነተኛ እምነት ያሳያል፡፡ ምስክርነት በደም ማኅተም ሊረጋገጥ እና ሕይወትን እስከ መሥዋዕት ሊያደርስ ይችላል፡፡

# ማጠቃለያ

ምስክርነት የእግዚአብሔርን መልካምነት የምናሳይበት አደባባይ ነው፡፡ ምስክርነት ለዘላለማዊው ድኅነታችን (ለመዳናችን) የተደረገልንን ታላቅ ነገር እና የተከፈለልንን መሥዋዕትነት በፍጹም እምነት የምናውጅበት፣ የተጠራንበትና የምንኖርለት ሕይወት ነው፡፡ ክርስትና በዓለም ሁሉ የተስፋፋው በምስክሮች ድምፅ ነው ፡፡ ምስክርነት በቃልም በተግባራዊ ሕይወትም ይገለጻል፡፡

# ተግባር

- መምህሩ የምስክሮችን ታሪክ አብነት በማድረግ ወጣቶች እንዲመሰክሩ ይምከራቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ምስክርነት ምንድነው? አብራሩ፡፡
- ለእግዚአብሔር ምስክሮቹ እነማን ናቸው?
- ምስክርነት በምን እና እንዴት ይገለጻል?
- ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና እምነት የምንገልጸው በምንድ ነው?
- የትንሣኤው ምስክሮች የሚባሉት እነማን ናቸው? በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ ግለጹ፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ሩት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ሩት ታሪክ እምነትና ታዛዥነት ያውቃሉ፤ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ስለማይለወጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ይገነዘባሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች በማብራራት ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል፡፡" ሩት. ፩÷፲፮፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መጽሐፈ ሩት ፩-፬

## መግቢያ

ሩት የመጽሐፉ ዋና ባለታሪክ፤ ሞዓባዊት ቆንጆ፤ የኑኃሚን ምራት፤ የቦኤዝ ሚስት፤ የኢዮቤድድ እናት፤ የዳዊት ቅድመ አያት ናት፡፡ ሩት ቆራጥ፣ ታዛዥ፣ ቅንና ታጋሽ ሴት ነበረች፡፡ መጽሐፈ ሩት የተሰየመው በእርሷ ስም ነው፡፡ መጽሐፈ ሩት "በሴት ስም" ከሚጠሩ መጻሕፍት መካከል አንዱ ነው፡፡ መጽሐፈ ሩት የእግዚአብሔር ፍቅር ለአሕዛብም እንደተረፈ ያሳያል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

መጽሐፈ ሩት የአቤሜሌክና የቤተሰቡ ጉዞ ወደ ሙታን ጉባኤ እንዳደረሳቸው፤ ከሞት የተረፈችው ኑኃሚን በእግዚአብሔር የመንበኘትን ዘመን ለማየት እንደቻለች ይናገራል፡፡ መጽሐፈ ሩት የአማናዊውን ቦኤዝ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛነት ይገልጣል፡፡ መጽሐፈ ሩት አራት ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው፡፡

**ምዕራፍ ፩÷፩-፭ የአቤሜሌክ ቤተሰብ ጉዞና ፍጻሜው**

መሳፍንቱ ይፈርዱ በነበረ ጊዜ በቤተልሔም ረኃብ ሆነ፡፡ በረኃቡ ምክንያት አቤሜሌክ፣ ከሚስቱ ከኑኃሚንና ከልጆቹ ከመሐሎንና ከኬሌዎን ጋር ሆነው ወደ ሞዓብ ሄዱ፡፡ አቤሜሌክ ሞተ፡፡ መሐሎንና ኬሌዎን ከአሕዛብ ጋር ተጋቡ፡፡ የሚስቶቻቸው ስም ሩትና ዖርፋ ነበር፡፡ መሐሎንና ኬሌዎን ሞቱ፡፡ ኑኃሚን ከልጆችዋና ከባልዋ ተለይታ ብቻዋን ቀረች፡፡

www.zeorthodox.org

**ቤተልሔም፡-** ማለት የእንጀራ ቤት ማለት ነው፡፡ የንጉሥ ዳዊት ከተማ ናት፡፡ ቤተልሔም ይሰደዱላታል እንጂ አይሰደዱባትም፡፡ ከቤተልሔም መውጣት የእግዚአብሔርን ማዳን በእምነት ጸንቶ በትዕግሥት አለመጠበቅን ያመለክታል፡፡ **ሞዓብ፡-** ሎጥ ከሴት ልጁ የወለደው ልጅ ነው፡፡ የእርሱ ልጆች የሚኖርበት ከተማ በስሙ ‹‹ሞዓብ›› ተጠርታለች፡፡ ሞዓባውያን የእስራኤላውያን ጠላት ናቸው፡፡ ሞዓብ እግዚአብሔር የማይታወቅባት ከተማ ናት፡፡ ኤቤሜሌክና ቤተሰቡ ከቤተልሔም ወጥተው ወደ ሞዓብ በመሄዳቸው የከፋ መከራ መጣባቸው፡፡ እግዚአብሔርን በማመን በቤተ ልሔም ጸንተው ጊዜያዊውን ራብ በትዕግሥት

ባለማሳለፋቸው ሞት አገኛቸው፡፡ ከእባብ ጉድጓድ ሸሽቶ ዘንዶ ማደሪያ መደበቅ ጉዳቱ የከፋ ነው፡፡ ችግሮቻችንን በመቋቋም የተሻለ መፍትሔ በመፈለግ ጠቃሚውን ውሳኔ መወሰን አለብን፡፡

**ምዕራፍ ፩ ፥፮-፳፪ የቤተልሔም ዜና፣ የኑኃሚን መመለስና የሩት ጽናት**

ኑኃሚን እግዚአብሔር ቤተልሔምን በበረከት እንደጎበኘ ሰማች፡፡ ለመመለስ ስትነሣ ምራቶቿ ሩትና ዖርፋ አብረን እንሂድ አሏት፡፡ “እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችሁ ሂዱ” ብላ መረቀቻቸው፡፡ ዖርፋ ስማት ተመለሰች፡፡ ሩት ግን ተጠግታ “ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምለኬ ይሆናል፡፡ በምታድሪበት አድራለሁ፤ በምተቀበሪበትም እቀበራለሁ፡፡ ከሞት በቀር ከአንቺ ማንም አይለየኝ” ብላት ከኑኃሚን አብራ ጉዞ ጀመረች፡፡ ቤተልሔም ደረሱ፤ በአረንጓዴ መስክ ያጌጡ ኮረብቶቿን አዩ፡፡ የጓሮዋን የወይን ዘለላና የገብስ እሸት ተመገቡ፡፡

የሩት ቆራጥነት ወደ ቤተልሔም የብርሃኑ መንግሥት አስገባት፡፡ እግሮቿ የንጉሡን ከተማ ረገጡ፡፡ መልካም ወደሆነው ፍጻሜ የሚያደርሰን የዓላማ ጽናት (ቆራጥነት) ነው፡፡

**ምዕራፍ ፪፥፩-፳፫ የሩት ውሎ በቦኤዝ እርሻና የኑኃሚን ምስክርነት**

ሩት ኑኃሚንን ለመንከባከብ በእርሻ ማሳ የደረሰው የእህል ሰብል ታጭዶ የተረፈውን ቃርሚያ ልትቃርም ወጣች፡፡ በእርሻ ቦታ ውላ እየቃረመች እንዳለ የእርሻው ባለቤት ቦኤዝ አያትና፤ “ይህች የማን ቆንጆ ናት?” አለ፡፡ አገልጋዮቹም “የኑኃሚን እንግዳ” ናት፤ አሉት፡፡ ቦኤዝ “ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ ገረዶቼን ተጠጊ” አላት፡፡ ሩትም በቦኤዝ እርሻ ቃረመች፡፡ ምሳ ጋበዛት፡፡ ማታ ለኑኃሚን ቀኑን ሙሉ እንዴት እንደዋለች ነገረቻት፡፡ ኑኃሚንም “ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አልተወምና በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፡፡ ይህ ሰው የቅርብ ዘመዳችን ነው፡፡ ሊቤዡን ከሚችሉት አንዱ ነው፡፡” አለቻት፡፡

ቦኤዝ የክርስቶስ፤ እርሻው የመንግሥቱ ምሳሌ ነው፡፡ ሩት የአሕዛብ ሁሉ ምሳሌ ናት፡፡ አሕዛብ በእምነት ሲመጡ ክርስቶስ ተቀብሏቸዋል፡፡ ከቦኤዝ እርሻ (ከክርስቶስ የረድኤት ጠል መራቅ ከኪዳኑ አጥር መውጣት) ይጎዳልና፡፡ አገልጋዮቹን ቅዱሳንን በመጠጋት የሕይወትን ቃል መማር ይጠቅማል፡፡ የኑኃሚን ምስክርነት እውነት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የቅርብ ዘመዳችን ነው፡፡ ከሥጋችን ሥጋ፣ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ፤ በሥጋና በደም ተካፍሎ፤ የአብርሃምን ዘር ይዞ ተዛምዶናልና፡፡ ዕብ. ፪፥፲፩፡፡ **ሊቤዡን ከሚችሉት ከአብ ከመንፈስ** ቅዱስ አንዱ አካል ወልድ እርሱ ነው፡፡ በደም በተደረገ ቤዛነት ከጨለማ ሥልጣን አድኖናልና፡፡ ቆላ. ፩፥፲፫፣ ኤፌ. ፩፥፯፡፡

www.zeorthodox.org

**ምዕራፍ ፫፥፩-፲፰ የኑኃሚን ምክርና የሩት ጥረት**

ኑኃሚን ምራትዋን ወደቦኤዝ እንድትጠጋ መከረቻት፡፡ ሩትም ቦኤዝ በአውድማ በተኛበት ተጠጋችው፡፡ ቦኤዝም ሩትን ቃል ገባላት፡፡ አሕዛብ ክርስቶስን ፍለጋ ቢወጡና ቀሚሱን በእምነት ቢነኩ ወደ ፍቅሩ መንግሥት ያስገባቸዋል፡፡

**ምዕራፍ ፬፥፩-፳፪ የሩት ጋብቻና የኢዮቤድ መወለድ**

ቦኤዝ ሩትን አገባት፡፡ ሩትም ኢዮቤድን ወለደች፡፡ ኢዮቤድ የዳዊት ቅድመ አያት የእሴይ አባት ነው፡፡ ሩት ከክርስቶስ የዘር

ሐረግ ተቆጠረች፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አሕዛብን በምሕረቱ መቀበሉን ጽድቅን በእምነት እንደቆጠረላቸው ያመለክታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "ጽድቅን የተከተሉ አሕዛብ ጽድቅን አገኙ፡፡ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው፡፡ እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም፡፡ ይህም በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ሰላልተከተሉ ነው" በማለት ስለ አሕዛብ ጽድቅ መስክሯልና፡፡ ሮሜ. ፱÷፴፡፡

## ማጠቃለያ

መጽሐፈ ሩት የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር ወሰን እንደሌለው ያስተምራል፡፡ የሩት ታዛዥነት ለክብር እንዳበቃት ይመሰክራል፡፡ አረጋውያንን መንከባከብ፤ መልካም በሆነው የጽድቅ ሥራ በዓላማ መጽናት እግዚአብሔር ወዳሰበልን ያደርሰናል፡፡ መጽሐፈ ሩት የእግዚአብሔርን ጊዜ በእምነትና በትዕግሥት መጠበቅ አለመቻል የሚያመጣውንም መራራ ሞት ይገልጻል፡፡ ለጊዜያዊ መከራ የዘላለም ሕይወትን መራቅ አይገባም፡፡

## ተግባር

መምህር ተማሪዎችዎ፤ መጽሐፈ ሩትን በሌሎች መጻሕፍት ታግዘው እንዲሁም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንንም እየጠየቁ እንዲያጠኑ ያድርጉ፡፡

www.zeorthodox.org

***ጥያቄዎች***

- ☞ ሩት ማን ናት?
- ☞ መጽሐፈ ሩት ስለምን የሚያስረዳ (የሚገልጽ) መጽሐፍ ነው?
- ☞ አቤሜሌክ እና ኑኃሚን ከልጆቻቸው ጋር ይኖሩ የነበረው የት ነው?
- ☞ አቤሜሌክ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ተሰደው የሄዱት ወደ የት ነው? ይህች ተሰደው የሄዱባት ከተማ በምን ትታወቃለች?
- ☞ አቤሜሌክና ቤተሰቡ ቀድሞ ይኖሩባት የነበረውን ቦታ(ከተማ) ትተው ተሰደው በመሄዳቸው ምን ደረሰባቸው?
- ☞ ‹‹ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል›› ብላ ኑኃሚንን ተከትላ የሄደችው ማን ነች? ይህች ሴት ኑኃሚንን ለመርዳት ምን አደረገች? በዚያ ምን አጋጠማት? ማንን አገኘች?
- ☞ ሩት ያገባችው ሰው ማን ይባላል? የወለደችውስ ማን ይባላል?
- ☞ ሩት ይህንን ሰው አግብታ በመውለዷ ያገኘችው በረከት ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን አባቶች

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለ ቅዱሳን አባቶች መልካም ሥራና አርአያነት ይገነዘባሉ፤ በተለይም ስለ ቅዱስ አግናጥዮስ እና ቅዱስ ቀሌምንጦስ ታሪክና መልካም ሥራ ያውቃሉ፤ መምህሩ የሚሰጧቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእምነት ምሰሉአቸው፡፡" ሩት. ፩÷፲፮፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፩÷፩-፵

## መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን ውለታ አታጠፋም፤ ቀድሞው በገዛ ዘመናቸው የደከሙላትን ዛሬ ትዘክራቸዋለችና፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዘመናቸው ለነበረው ትውልድ በቃል፤ ለሚተካው ትውልድ በጽሑፍ የእግዚአብሔርን ቃል አስተላልፈዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጠብቀው ያወረሱ፤ ለጠያቂዎች አግባብነት ያለው መልስ የሰጡ፤ ባፍ በመጣፍ መናፍቃንን ተከራክረው የረቱ ናቸው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚባሉት ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የተነሡና የሐዋርያትን እውነተኛ መንገድ ተከትለው ትምህርታቸውን ያስተማሩ ሥራቸውን በማስፋፋት እንዲቀጥል ያድርጉ ናቸው፡፡ እነዚህ አባቶች ዓለማቀፋዊ ጉባኤያት እየሠሩ የአብያተ ክርስቲያናቱን ችግሮች የፈቱና የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና እና ልዕልና ያስከበሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አባቶች መካከል አግናጥዮስ፣ ቀሌምንጦስ፣ ፖሊካርፕ፣ እለእስክንድሮስ፣ አትናቴዎስ፣ ጢሞቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ዲዮስቆሮስ፣ ያዕቆብ ዘእንበረዲ፣ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስና ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ይጠቀሳሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የአግናጥዮስንና የቀሌምንጦስን ታሪክና ትምህርት እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

### 1. ቅዱስ አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ

ጌታ በክንዱ ስለታቀፈው ቴዎፎሎስ ይባላል፡፡ ክርስቶስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ሲያስተምር በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያቆመው ሕፃን አግናጥዮስ ነበር፡፡ ማቴ. ፲፰÷፩-፬፡፡ **አግናጥዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ** ሆኗል፡፡ ብዙ መልእክታትን ጽፏል፡፡ በመጨረሻም ትራጃን የሚባለው ንጉሥ ሃይማኖቱን እንዲክድ ሲጠይቀው በእምነቱ ጸና፡፡ ትራጃን ወታደሮቹን አዝዞ ወደ አንበሳ ጉድጓድ አስጣለው፡፡ በአንበሳም ተበልቶ ሰማዕትነት ስለተቀበለ "ምጥው ለአንበሳ" እየተባለ ይጠራል፡፡ አግናጥዮስ ለአንበሳ

ከመጣሉ በፊት" እኔ የእግዚአብሔር የመሥዋዕት ስንዴ ነኝ፡፡ በአንበሳ መንጋጋ እፈጫለሁ፡፡ እኔ ለአምላኬ ንጹሕና የተወደደ መሥዋዕት እሆናለሁ፡፡ ክርስቲያን የሆንኩበትን እውነት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር መሥዋዕት ልሆንለት እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ጌታዬ ልሄድ እናፍቃለሁ፡፡ የሚታየውና የማይታየው እስርና ሰንሰለቴ ከጌታዬ ፍቅር ሊለየኝ አይችልም፡፡" በማለት ሰማዕት ሆነ፡፡

### 1.1. የአግናጥዮስ መልእክት

- "በግብዞችና በደካሞች ፊት መልካም አርአያነትህ ይገለጥ፡፡ በፍቅርና በትዕግሥት በፍትሕና በጸሎት የገዥዎችን ኢፍትሐዊነት፣ የክፉዎችን ስም ማጥፋትና የወገኖችህን ጥላቻ ማሸነፍ ትችላለህ፡፡"
- "በሃይማኖት በመጽናት ኃጢአተኝነትን አሸንፍ፡፡ ስለ ክርስቶስ የሚደርስብህን ሁሉ በጽናት እለፍ፡፡ እኔ በክርስቶስ ሁሉን እንደ ጉዳት ቆጥሬአለሁ፡፡ ምድራዊ ስለሆኑ እስራቶችም አልጨነቅም፡፡ ከጸጋው ግምጃ ቤተ ሰላምን እንድቀበል ስለ ክርስቶስም ባለአደራ እንድሆን ጸልይልኝ፡፡"
- "ለክርስቶስ ባለኝ ፍቅር በሰንሰለት ታስሬአለሁ፡፡ ያንተ ፍቅር እንዲጎዳኝ አልፈልግም፡፡ ከሞት እንድታድነኝም አልፈልግም፡፡ ስለ ፍቅርህ ስማዕትነት ባልቀበል ይህንም ዕድል ደግሞ ባጣው እጸጸታለሁ፡፡ ሰማትነት መቀበል የፈለኩት ክርስትናዬን በሕይወት ለመግለጽ ለክርስቶስ ያለኝን ተግባራዊ ፍቅር ለማሳየት ነው፡፡ ለአራዊትና ለአናብስት ምግብ ልሁን፡፡"

## 2. ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም

ቀሌምንጦስ በሮም ከተማ ተወልዶ ያደገና የግሪክን ጥበብ የተማረ ሰው ነበር፡፡ የክርስትናን ትምህርት ከቅዱስ ጳውሎስ ተምሯል፡፡ አብሮትም ሠርቷል፡፡ ፊልጵ. ፬÷፫፡፡ **ከሐዋርያት ቀጥሎ ለወንጌል ዋጋ** የከፈለ አባት ነው፡፡ ብዙ ሃገሮችን በሐዋርያዊ ጉዞው አገልግሏል፡፡ ብዙ ሰዎችን ከጨለማ ግዛትነት አውጥቶ ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር ጠርቷል፡፡ የሮም ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገልግሏል፡፡ ቀሌምንጦስ ብዙ መልእክቶችንም ጽፏል፡፡

በትራጃን ዘመን በጥቁር ባሕር ተጥሎ ሰማዕትነት ተቀብሏል፡፡ ጽናቱም ብዙ አማኞችን ጠርቷል፡፡ ቀሌምንጦስ ከላከው መልእክት መካከል "ስለራስህ አታውራ፡፡ ወንጌልን በመጨከን ለማዳመጥ ትጋ፡፡ ስለሰዎች ይቅር መባባል ጸልይ፡፡ ቅንዓትን፣ ስቃይን፣ ሥርዓት አልበኝነትን፣ ክፋትንና አድመኝነትን አርቅ፡፡ ጽድቅና ሰላም ካንተ ጋር ይሁን፡፡" የሚለው ይታወሳል፡፡

www.zeorthodox.org

# ማጠቃለያ

ዛሬ የምንጓዝበትን የክርስትና ኑሮ ያለፉበት ጉዞውን በድል ያጠናቀቁት አባቶቻችን የሕይወት አርአያዎቻችን ናቸው፡፡ ትምህርታቸውን ማወቅ፣ ያመለኩትን እግዚአብሔርን በጽድቅ ማምለክና በእምነታችን የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን መምሰል ይጠበቅብናል፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ከሁለቱ አባቶች ምን እንደተማሩ ይጠይቋቸው፡፡

### *ጥቄዎች*

- የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚባሉት እነማን (ምን ያደረጉ) ናቸው? በተማራችሁት መሠረት ግለጹ፡፡
- ቅዱስ አግናጥዮስ ማን ነው?
- ‹‹ምጥው ለአንበሳ›› የተባለበት ምክንያት ምንድነው?
- ቅዱስ ቀሌምንጦስ የት ተወለደ? ክርስትናን ያስተማረው ማነው?
- ቅዱስ ቀሌምንጦስ ከሠራቸው መልካም ሥራዎች ውስጥ በተማራችሁት መሠረት ግለጹ? የማን ሀገር ሊቀጳጳስ ነበር?
- የቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ሕይወት ዐውቀን ከትምህርታቸው እና ከሥራቸው በተረዳነው (በተገነዘብነው) መሠረት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

www.zeorthodox.org

# ውበት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች ስለውበት ትክክለኛ ግንዛቤና ዕውቀት ያገኛሉ፤ ውበታቸውን ይጠብቃሉ፤ መምህሩ የሚያቀርቡላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፡፡" መክ. ፫÷፲፩፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** መዝ. ፻፴፰(፻፴፱)÷፲፬፣ መኃ. ፩÷፭፣ ፩ቆሮ. ፫÷፲፮ እና ሮሜ. ፲፫÷፲፬

## መግቢያ

- ውበት ምንድን ነው?
- አንድን ነገር ውብ ነው ወይም አይደለም የምንልበት ትክክለኛ መመዘኛ ምንድ ነው?
- ስለ ውበት ያላችሁን እውቀት ለጓኞቻችሁ አካፍሉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

ውበት የሚለው ቃል "ሥን" ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው፡፡ ውበት ማለት መልክ፣ ደም ግባት፣ ጥራት፣ ጌጥና ጽዳት ማለት ነው፡፡ ውበት ውጫዊና ውስጣዊ ውበት ተብሎ ይከፈላል፡፡ መልካምነት ደግነት፣ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ልበ ሰፊነትና ይቅርባይነት በውስጣዊ ውበት ይጠቃለላሉ፡፡ ውጫዊ ውበት በሰው ፊት፤ ውስጣዊ ውበት በእግዚአብሔር ፊት ይገለጣሉ፡፡ የውጫዊ ውበት ጌጥ ውስጣዊ ውበት ነው፡፡ የውስጣዊ ውበት መገለጫ ደግሞ በእግዚብሔርም ሆነ በሰዎች ዘንድ መልካምና እውነተኛ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ሰው ውጫዊ ደም ግባትን ያያል፤ እግዚአብሔር ልብን (ውስጣዊ ውበትን) ያያል፡፡ ፩ሳሙ. ፲፮÷፯-፲፫፡፡ **ሰው ውጫዊ ውበታችንን ብቻ አይቶ ቢቀርበንም** ውስጣዊ ውበት ከሌለን አብሮን ሊዘልቅ አይችልም፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ለዓለም ጌጥ ሁሉን ውብ አድርጎ ሠርቷል፡፡ መክ. ፫÷፲፩ እግዚአብሔር ሲፈጥረን ልባችንን ንጹሕ፤ ፊታችን ውብ አድርጎ ነው፡፡ ግሩምና ጽድንቅ ሆነን ተፈጥረናል፡፡ ዳዊት "ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ" ብሏል፡፡ መዝ. ፻፴፰(፻፴፱)÷፲፬፡፡ **ልጁ ሰለሞን ደግሞ "ጥቁር** ነኝ ግን ውብ ነኝ" ብሏል፡፡ መኃ. ፩÷፭፡፡ **ሆሜር "ኢትዮጵያዊ እንደ ጎመራ** ወይን ነው፡፡" በማለት ያማረ ደም ግባት እንዳለን መስክሯል፡፡ እግዚአብሔርን ለማመስገን ብዙ የምስጋና አርእስት አሉን፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ ግሩምና ድንቅ፤ ውብና ደመ ግቡ አድርጎ ስለፈጠረን ማመስገናችን ነው፡፡ ዓይኖቻችንን ከፍተን ድንቅ የሆነውን የተፈጥሮ ውበት፣ የፍጥረታትን እንቅስቃሴና የዘመናትን ቀመር በማየት እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል፤ እርሱ ለዓለም ጌጥ ሁሉን አስውቧልና፡፡ ራሳችንንም በማየት የተጠበበብንን ሠሪያችንን ፈጣሪያችንን

እግዚአብሔርን እናመስግነው፡፡

ውበትን ማድነቅ፣ ማክበርና መንከባከብ ይገባል፡፡ ምድራችን የውበት አደባባይ ናት፡፡ ትልቁ ውበት የሌሎችን ማንነት መቀበል ነው፡፡ ፕላኔታችን የቋንቋ፣ የባህል፣ የአመጋገብና የሐሳብ ልዩነት አሰሸብርቋታል፡፡ በአንድነታችን ውስጥ ያሉ ልዩነቶች ድንቅ ውበቶቻችን ናቸውና በጸጋ ልንቀበላቸው፤ በደስታ ልናከብራቸውና ልንከባከባቸው ይገባል፡፡

ውበትን የማያደንቁ፣ ውበታቸውን ለኃጢአት መረብ ያደረጉና ስለ ውበት የተሳሳተ አስተምህሮ የሚያስተምሩ ብዙዎች ናቸው፡፡

ውበት የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራና የምስጋና ርእስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር የጥበቡን ብዛት ማድነቂያ ፤ የእግዚአብሔር ጥበብ ማሳያ ሰሌዳ ነው፡፡ ወጣትነት የውበት አደባባይ ነው፡፡ የውበት ትርጉም የሚኖረን፤ ለውበታችን የምንጨነቀው፤ ራሳችንን ለመቀበልና ላለመቀበል የኅሊና ጦርነት የምንጀምረው፤ በወጣትነት ጊዜ ነው፡፡

ለወጣቶች ትልቁ ውበት ራስን መቀበል፣ ውበትን መንከባከብና በሆነው ማንነታችን መደሰት ነው፡፡ ባለን ስንደሰትና በራሳችን ስንተማመን ሰዎች ያከብሩናል፡፡ ስለዚህ ውጫዊ ውበታችንን በአግባቡ በመጠበቅ፤ ውስጣዊ ውበታችን በእውቀት፣ በትሕትና፣ በፍቅር፣ በመልካምነትና በመንፈስ ፍሬዎች ማስጌጥ አለብን፡፡

የውበታችን ውበት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በሰው ፊት ሞገስ፤ በእግዚአብሔር ፊት ውበት እንዲኖረን ኢየሱስ ክርስቶስን መልበስ አለብን፡፡ ሮሜ. ፲፫÷፲፬፤ ኤፌ. ፬÷፲፯-፳፬፤ ቆላ. ፫÷፭-፲፡፡ **እርሱ ለውበታችን ውበቱን አጥቷል**፤ የነፍስ ደምግባትን ሊሰጠን ደምግባቱን አጥቷል፡፡ ኢሳ. ፶፫÷፪-፬፡፡ **የክርስቲያን ልዩና ድንቅ ውበት** ክርስቶስ ነው፡፡ የተጠመቅን እርሱን ለብሰነዋል፡፡ ገላ. ፫÷፳፯፡፡

## ማጠቃለያ

ውበት የእግዚአብሔር ጥበብ መታያ፣ የድንቅ ሥራው ውጤት፣ የጣቱ ጌጥ አደባባይና የምስጋና ርእስ ነው፡፡ ውበት ውስጣዊና ውጫዊ ነው፡፡ ውስጣዊ ውበት የውጫዊ ውበት ጌጥ ነው፡፡ ውጫዊ ውበት ሰዎች እንዲቀርቡን መንደርደሪያ ነው፡፡ ውስጣዊ ውበት ደግሞ ሰዎች ከእኛ ጋር እንዲቆዩ ዋስትና ነው፡፡ ውበትን እናድንቅ፤ እንከባከብ፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎ ስለውበት አጠባበቅ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ያወያዩዋቸው፡፡

## ጥያቄዎች

- ☞ ውበት ማለት (የቃሉ ትርጉም) ምን ማለት ነው?
- ☞ ውበት በስንት ይከፈላል?
- ☞ ውጫዊ ውበት ምንድነው?
- ☞ ውስጣዊ ውበት ምንድነው?
- ☞ የውጪውንም ሆነ ውስጣዊ ውበታችን ለመንከባከብ ምን ማድረግ አለብን? ውበታችንን በመጠበቅ እና በመንከባከብ የምናገኘው ውጤት ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# የአካል ብቃት እንቅስቃሴ

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ተማሪዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር እንደማይጋጭ ይገነዘባሉ፤ መምህሩ ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ፡-** "በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ፡፡" ፩ቆሮ. ፱÷፳፬-፳፮፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዕብ. ፲፪÷፪

## መግቢያ

- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለምን ይጠቅማል?
- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ የሚከለክል የቤተክርስቲያን አስተምህሮ አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? (ተወያዩበት)

## የሳምንቱ ትምህርት፡-

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለአካል ጥንካሬ፣ የሰውነት ክብደትን ለመቆጣጠር፣ ለአእምሮ መነቃቃት፣ ለአካል ጤንነትና ለሰውነት ቅርጽ መስተካከል ይጠቅማል፡፡ ንቁ፣ ጤናማና ጠንካራ ለመሆን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥራት አለብን፡፡ ሰውነታችንን በአካል ብቃት እንቅስቃሴ የማንቆጣጠር ከሆነ ለተለያዩ በሽታዎች እንጋለጣለን፡፡ ሥራችንንም ለመሥራት የተነቃቃ፣ የጠነከርና ሥራ የለመደ ሰውነት አይኖረንም፡፡ ጤናማና ጠንካራ ካልሆንን አምልኮ ለመፈጸምም አቅም አይኖረንም፡፡ አምልኮ በመንፈስና በእውነት የሚፈጸም ቢሆንም የአካል ጤናማነትንም ይፈልጋልና፡፡ በሱሰኝነት ታስረን ለክብራችን በማይመጥኑ ሥፍራዎች ጊዜያችንን ከምናባክንና ለበሽታዎች ተጋላጭ ከምንሆን በስፖርት ማዘውተሪያዎች ብናሳልፍ ይሻላል፡፡ የትምህርታችንን እና የመንፈሳዊ ሕይወታችንን ጊዜ ሳንነካ በትርፍ ጊዜያችን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥራት እንችላለን፡፡ ከዓለም ክፉ ነገሮች ጋር ሳንነካካ መልካም በሆነው ነገር መጓዝ አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

በመጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ሕይወት ማስተማሪያ በምሳሌነት የቀረቡ የስፖርት ዓይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ ሩጫ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ፡፡ የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፡፡ እነዚያ የሚጠፋውን አክሊል ሲያገኙ ነው፡፡፡ እኛ ግን የማይጠፋውን አክሊል ለመቀበል ነው፡፡›› በማለት በምሳሌ የክርስትናን ጉዞ አሳይቷል፡፡ ፩ቆሮ. ፱÷፳፬-፳፮፡፡

በቆሮንቶስ ከተማ ለሚኖሩ ምእመናን ሩጫና ኢስታሜን ውድድር አዲስ አይደለም፡፡ በግሪክ ከተማ ስለሚኖሩ የአቴንስ ዜና የሰሙ ጆሮዎች አሏቸውና፡፡ የሩጫ ውድድር መነሻ አገር ለሆነችው ለአቴንስ ቅርብ ናቸውና፡፡

በሩጫ ውድድር ብዙዎች ይሳተፋሉ፤ የአበባ ጉንጉንና ሜዳሊያ የሚሰጠው ግን ለአሸናፊው ነው፡፡ በክርስትናም የተጠሩ ብዙዎች ናቸው፤ የተመረጡት እና ሰማያዊውን ዘለዓለማዊ መንግሥት ወራሾች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ የክርስትና ሽልማት ለተጠሩት ሁሉ አይደለም፡፡ እስከሞት በመታመን ለዳኑት ምርጦች የሕይወት አክሊል ይጠብቃቸዋል፡፡ ራዕ. ፪÷፲፩፡፡ በሩጫ ውድድር አሸናፊዎች የሚሸለሙት የሚጠፋውን አክሊል ነው፡፡ በክርስትና መስመር በእምነት የሚሮጡት ምርጦች ሩጫውን በትዕግሥት ሩጠው ሲጨርሱ የሚያገኙት የማይጠፋውን አክሊል ነው፡፡ ስለዚህ ሩጫችን ያለ ዋጋ አይደለም፡፡

ሩጫ፣ ትግል፣ ፈረስ ግልቢያ፣ ዱላ ቅብብልና ኳስ ጨዋታ ለአማኞች ትልቅ ምልከታ አላቸው፡፡ በዘመነ ሰማዕታት አላውያን ነገሥታት አማኞችን እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከአራዊት ጋር ያታግሏቸው ነበር፡፡ ቅዱስ አግናጥዮስ ከአንበሳ ጋር ታግሏል፡፡ ዳንኤልና ዳዊት አንበሳን ታግለው ገድለዋል፡፡ በሚያገሳ አንበሳ ዲያብሎስ ተመስሏል፡፡ ስለዚህ ትግል አለብን፡፡ ትግሉ ደግሞ ከሥጋና ከደም ጋር ብቻ አይደለም፤ ከክፋት ሠራዊትም ጋር እንጂ፡፡ ኤፌ. ፮÷፲፪-፲፫፡፡ ፈረስ ግልቢያን ስናስታውስ በፈረስ የተረገጡና የተጎተቱ ሰማዕታትን እናስባለን፡፡

በኳስ ጨዋታ ተሸላሚዎች ተጨዋቾች እንጂ ተመልካቾች አይደሉም፡፡ በክርስትናም ታዛቢና ተመልካች በመሆን ዳር የቆሙት አይሸለሙም፤ የሚሸለሙት በክርስትናው የትግል ሜዳ እየደከሙ ያሉት ናቸው፡፡ በኳስ ጨዋታ ሕግ  አከፋፋይ፣ ጎል ጠባቂ፣ አጥቂና ተከላካይ አሉ፡፡ ይህ ማለት ኅብረት አለ ማለት ነው፡፡ ክርስትና የፍቅር ኅብረት ነው፡፡ ዲያብሎስን ለማጥቃት፣ ከጠላት ጥቃት ለመከላከል፣ ቃሉንና በረከቱን ለማከፋፈል በአንድነት መሆን ያስፈልጋል፡፡

ዱላ ቅብብል የሁሉንም ተሳትፎ የሚፈልግ የስፖርት አይነት ነው፡፡ የክርስትናም እውነት ቅብብል ነው፡፡ ነቢያት ለሐዋርያት፤ ሐዋርያት ለቅዱሳን አባቶች (ለጠበቆች)፤ ጠበቆች (ለቅዱሳን አባቶች)ለሊቃውንት፤ ሊቃውንት ለሰማዕታት፤ እየተቀባበሉ ነው ለእኛ ያደረሱልን፡፡ አሁንም ይህን መቀባበል በፍቅር እናድርገው፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለጤንነት፣ ለጥንካሬና ለንቃት ይጠቅማል፡፡ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታዩ መንፈሳዊ ተምሳሌቶችን እንማርባቸው፡፡ የአካላዊ እንቅስቃሴን ስፖርት የሚቃወም የክርስትና አስተምህሮ የለም፡፡

## ተግባር

- መምህር ተማሪዎችዎን፤ ዘላቂነት ያለው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዴት መሥራት እንችላለን? በሚል  ርእስ እንዲወያዩ  ያድርጓቸው፡፡

***ጥያቄዎች***

- ☞ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ምንድነው?
- ☞ **የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለምን ይጠቅማል?**
- ☞ **የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ (ስፖርት መሥራት) የሚከለክል የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?**
- ☞ **አለ ካላችሁ ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡**
- ☞ **መልሳችሁ የለም ከሆነ በተማራችሁት መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ አብራሩ፡፡**

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት


- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኝኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፪፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም


www.zoorthodox.org

- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.
- በጠቅላይ ቤተ ክህነት። 2000 ዓ.ም። የኢትዮ. ኦርቶ.ተዋ. ቤ.ክ ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም። አዲስ አበባ ፤ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )። 2000። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ ። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። 1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጎርጎርዮስ(ብፁዕ አቡነ)። 1996 ዓ.ም። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ። አዲስ አበባ። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።
- መሐሪ ትርፌ (በሊቀ ሊቃውንት)። 19 ዓ.ም። የጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ።
- ዳንኤል ተሾመ። 19 ዓ.ም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ስልቶች። አ.አ
- Pulpet ; 19 A.D; Bible commentary The Epistle of paul to the ROMAN;
-
-Tadros Yakob Malaty (Father); 2007-2008 A.D; The Epistle of Saint Paul to the Romans; Alexandria,Egypt.

www.zeorthodox.org

- መብራቱ ኪሮስ (ዲያቆን)፡፡ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያልታተመ መማሪያ፡፡
- ጎርጎርዮስ (በብፁዕ አቡነ):: 1981 ዓ.ም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ቀሲስ ፤ ዶ/ር )፡፡ 2001፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ 1ኛ እና 2ኛ፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- Lule Melaku (Asst. Professor); 2010; History of the Ethi. Orthodox Tewahido Church; A.A ; Elleni p.p.plc.
- ሰሎሞን መላኩ(ዲያቆን)፡፡ 2001ዓ.ም፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ባናዊ ማተሚያ፡፡
- Syrian Sunday school curriculum.
- Introduction to Coptic orthodox Church ; Father Tadros Y Malaty
- Ian Gillman,Hans-Joachim Klimkeit ; Christian in asia before 1500 ;
- ዜና ሐዋርያት
- ገድለ ቅድስት አርሴማ
- ሺኖዳ(ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ) ቅንዓት
- የኢትዮፕያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ ፤ ስንክሳር ፤ በትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ
- ያረጋል አበጋዝ (ዲ/ን)፡፡ ቅዱስ ዩሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ ፤ አዲስ አበባ
- በጌታቸው ኃይሌ(ፕሮፌሰር)፡፡ 1997 ዓ.ም፡፡ የአባ ባሕርይ ድርሰቶች
- ዳንኤል ክብረት(ዲ/ን)፡፡ 1998ዓ.ም፡፡ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡፡
- ………፡፡ አዋልድ መጻሕፍት፡፡ ሐመረ ተዋሕዶ፡፡
- Douglas J.D and Tenney M.c (1987) New International BIBLE DICTIONARY. ZONDERVAN'S.Grand Rapids,MICHIGAN USA
- Holy Trinity College.(2004) Patrology፡ Holy Trinity College module/ unpublished./


www.zeorthodox.org

- Malaty T.Y( Father)Patrology ;
- Malaty T.Y( Father).(199). Tradition and Orthodoxy. Alexandria .Egypt.
- ማኅበረ ቅዱሳን፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ የማዕረግ ቃል ማተሚያ ቤት፡፡
- ነገረ ማርያም
- Shenoda - Pope (1999). The Holy virgin Saint Mary. Cairo,Egypt.
- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (1988) ወንጌል ቅዱስ ትርጓሜ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
- የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት መማሪያ ፤ ካናዳ
- ሺኖዳ ሰው ምንድነው ፤ በብጹዕ ወቅዱስ ፤
- ክርስቲያን አንትሮፖሎጂ
- ሺኖዳ (ብጹዕ ወቅዱስ ፤ አቡነ)፡፡ መንፈሳዊው ሰው
- John Mark (Father). 19 . Ascending the heights ; A lay man guide to the ladder of divine ascent
- አበራ (በሊቀ ጉባዔ ፤ አባ)፡፡ 1996 ዓ.ም፡፡ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 200 ዓ.ም፡፡ መሽኮርመምና ማሽኮርመም፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ሰሎሞን ሙሉጌታ (ቀሲስ)፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ቅድመ ጋብቻ፡፡ በቦሌ ደብረ ሳሌም የረቡዕ ጉባዔ የተሠጠ ስብከት በzeorthodox.org የተለቀቀ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ
- ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ 1988፡፡ መጽሕፍተ መነኮሳት፡፡ አዲስ አበባ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት፡፡
- ጥዑመ ልሳን፡፡() ያሬድና ዜማው፡፡ አዲስ አበባ፡፡
- ሙሳ (ሊቀ ጳጳስ)፡፡ ወጣትነትና የቅድስና ኑሮ፡፡ በመምህር ወንድወሰን ሶርሳ የተተረጎመ፡፡


www.zeorthodox.org